“በፖለቲካ ትግሉ ውስጥ እንደ አሉባልታ ከባድ ነገር የለም”

ገፅ 3

# አዲስ ጉዳይ

ከአብደላ ዕዝራ ሒሣዊ ዳሰሳ ያልገቡኝ ነገሮች

ገፅ 15

ቅፅ 14 ቁጥር 786 | ቅዳሜ ጥር 30 ቀን 2007 ዓ.ም | ብር 8.00

# የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር፤ በፓርቲዎች ክፍፍልና በፖለቲካ ውዝግቦች ዙሪያ

ውህደት ለመፈፀም ተደጋጋሚ ድርድሮችን ሲያካሂዱና ስምምነት ሲፈፀሙ የቆዩት አንድነት ፓርቲ እና መኢአድ፣ የውህደት ጅምራቸው ካለመሳካቱም በተጨማሪ በየፊናቸው ለሁለት ለሁለት ተከፍለው ሲወዛገቡ ነው የከረሙት:: በመጨረሻም የምርጫ ቦርድ፣ ከመኢአድ ፓርቲ በአቶ አበባው መሃሪ ለሚመራ ቡድን፣ ከአንድነት ፓርቲ ደግሞ በአቶ ትዕግስቱ አወሉ ለሚመራው ቡድን እውቅና ሰጥቻለሁ ብሏል:: እውቅና ያልተሰጠው በአቶ በላይ የሚመራው የአንድነት ቡድን ብዙም ሳይቆይ፣ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር ተቀላቅሏል::

ዝርዝሩን በገፅ 2 ይመልከቱ



## አሜሪካ በተወሰኑ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የጣለችውን የበረራ እገዳ አነሳች

### እገዳው ለ15 አመታት ተግባራዊ ሆኖ ቆይቷል

የአሜሪካ ፌዴራል አቪየሽን ባለስልጣን የአገሪቱ አውሮፕላኖች በተወሰኑ የኢትዮጵያ የድንበር አካባቢዎች የአየር ክልል ውስጥ እንዳይበሩ የጣለችውንና ለ15 አመታት ተግባራዊ ሆኖ የቆየውን እገዳ ማንሳቱን አስታወቀ::

ባለስልጣኑ የበረራ እገዳውን የጣለው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በተቀሰቀሰበት ወቅት እንደነበር አስታውሶ፣ እገዳው በተጣለባቸው አካባቢዎች የደህንነትና የጸጥታ ሁኔታ እየተሻሻለ መምጣቱንና የአደጋ ስጋት የሌለበት መሆኑን በጥናት በማረጋገጡ እገዳውን ማንሳቱን ባለፈው ረቡዕ ይፋ ባደረገው መረጃ አስታውቋል::

በወቅቱ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል

በረራ ወደ ገፅ 2 ዞሯል

# በግማሽ ዓመት 47 ሺ ኢትዮጵያዊያን ወደ የመን ተሰደዋል

- ሰሞኑን 35 ስደተኞች የያዘ ጀልባ የመን ሳይደርስ ሰጥሟል
- በዓመት 200 ገደማ ኢትዮጵያውያን በበረሃ እና በባህር ጉዞ ላይ ሞተዋል
- “በህጋዊ ምዝገባ የስራ ጉዞ መታገዱ ህገወጥ ስደትን አባብሷል”

በህጋዊ ምዝገባ ወደ አረብ አገራት የሚደረግ ጉዞ ከታገደ ወዲህ፣ በየመን በኩል እየተሰደዱ ለአደጋ የሚጋለጡ ኢትዮጵያዊያን መበራከታቸውንና ባለፉት ስድስት ወራት 47ሺ ያህል ስደተኞች የመን እንደገቡ RMMS ሰሞኑን ገለፀ::

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን እና ሌሎች አለማቀፍ ድርጅቶች በጋራ ያቋቋሙት ይሄው ተቋም እንደሚለው፣ ዘንድሮ የስደተኞቹ ቁጥር ከአምናው በእጥፍ ይበልጣል:: ባለፉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ 250 ስደተኞች የመን ለመግባት ሲሞከሩ፣ በባህርና በበረሃ ጉዞ ላይ መሞታቸውን ተቋሙ ጠቅሶ ከስደተኞቹ መካከል ሰማኒያ በመቶ ያህሉ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን ገልጿል::

ሰሞኑን በባህር ጉዞ ላይ በተፈጠረ አደጋ አንድ ጀልባ መስመጡን የዘገበው ኤኤፍፒ፤ ጀልባዋ 35 ስደተኞችን አሳፍራ ነበር ብሏል:: ከጉዞ አደጋ በተጨማሪ ስደተኞቹ የመን ከገቡ በኋላም ግማሽ ያህሉ በወሮበላ ቡድኖች እንደሚታገዱ የገለፀው RMMS፤ ከእገታ ለመለቀቅ ከቤተሰብ ገንዘብ እንዲያስልኩ ይገደዳሉ ብሏል::

ለስደት የሚገፋፉ ዋና ዋና ምክንያቶችን ለማወቅ በሺ በሚቆጠሩ ስደተኞችና በትውልድ አካባቢዎቻቸው ላይ ጥናት ያካሄደው ይሄው ተቋም፤ በኢትዮጵያ ዋናዎቹ መንስኤዎች የኑሮ ችግር እንዲሁም ህይወትን የሚያሻሽል ነገር ፍለጋ ናቸው ብሏል:: የፖለቲካ ችግርም የተወሰነ ጫና እንደሚፈጥር ተቋሙ ጠቅሶ፣ የደላሎች ድርሻ ግን ብዙዎች እንደሚያስቡት አይደለም፤ ከመቶ ስደተኞች መካከል በደላላ ግፊት ለስደት የሚነሳሱት ከሁለት ወይም ከሦስት አይበልጡም ብሏል::

ብዙ ወጣቶች ወደ ስደት የሚያቀኑት አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ባለማወቃቸው ነው ለማለት እንደሚያስቸግር ተቋሙ ሲያስረዳ፤ በአመት ውስጥ ወደ የመን ከገቡት ኢትዮጵያዊያን መካከል ሩብ ያህሉ ከሳዑዲ አረቢያ ወደ አገራቸው የተባረሩና ካሁን በፊት ስደትን የሞከሩ ናቸው ብሏል::

ከቅርብ ወራት ወዲህ የስደተኞቹ ቁጥር የተባባሰበት ሌላው ምክንያት፣ በህጋዊ ምዝገባ ወደ ሳዑዲ አረቢያና ወደ ኩዌት ሲደረግ የነበረው የስራ ጉዞ በመንግስት መታገዱ ነው ብሏል - የተቋሙ ጥናት::

በሌላ በኩል ሶማሊያ ውስጥ ከድህነት በተጨማሪ የሰላም እጦት ወጣቶችን ለስደት እንደሚገፋፋ ተቋሙ ገልፆ፤ በኤርትራ ደግሞ ከኑሮ ችግር ሌላ ዋነኛው ግፊት የመንግስት ከፍተኛ የፖለቲካ አፈና ነው ብሏል:: በሊቢያና በግብጽ በኩል ወደ አውሮፓ ለመግባት ከሚሞክሩ ስደተኞች መካከል ከሶሪያዊያን በመቀጠል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት ኤርትራዊያን መሆናቸውን የጠቀሰው ይሄው ተቋም፤ ባለፉት አራት ወራት 15ሺ ኤርትራዊያን ወደ ኢትዮጵያ እንደተሰደዱ ገልጿል::

ስደት የተባባሰው በድህነትና በአፈና ምክንያት አይደለም በማለት የኤርትራ መንግስት ሲያስተባብል፤ ወጣቶች እንዲሰደዱ በማድረግ አገሪቱን ኦና ለማድረግ አለማቀፍ ሴራ እየተካሄደብኝ ነው ብሏል::

# የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ም/ቤት ፕሬዚዳንት፤ ከስልጣኔ አልወረድኩም አሉ

### የመፈንቅለ መጅሊስ ሙከራው ስርዓት አልበኝነት ነው ብለዋል

መታሰቢያ ካሳዬ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ኪያር ሼህ መሃመድ አማን አህመድ፤ ከስልጣናቸው አለመውረዳቸውንና በቅርቡ በኦሮሚያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የተሰጠውን መግለጫ በጥብቅ እንደሚቃወሙ ገለፁ::

በቴሌቪዥን “የኦሮሚያ ክልል የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚዎች በህገ ወጥ መንገድ ስርዓት አልበኝነትን ተላብሰው፣ ‹እኛ የኢትዮጵያ ፌደራል መጅሊስ ፕሬዚዳንቶች ነን› በማለት በመንግስት ሚዲያዎች መግለጫ መስጠታቸው ህገወጥ ድርጊት ነው” ብለዋል- ፕሬዚዳንቱ ሰሞኑን በፅ/ቤታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ::

የአንድ ክልል ሥራ አስፈፃሚ በፌደራል ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ እከሌን አባረናል፣ እከሌን አግደናል ማለቱ ከህግና መመሪያ ውጪ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በህገወጥነት ህጋዊ መሆን ስለማይቻል ግለሰቦቹ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳስበዋል::

የህዝበ ሙስሊሙ ትልቅ ተቋም የሆነውን መጅሊስ ጥቂት ስርዓተ አልበኞች ሊያምሱትና ሊያተራምሱት እንደማይችሉ የተናገሩት የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት፤ “እኔ ለሥራ ጉዳይ ከአገር በወጣሁ ቁጥር መፈንቅለ መጅሊስ ለማድረግና በህገወጥ መንገድ ስልጣን ለመያዝ ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርጉም ሳይሳካላቸው ቀርቷል” ብለዋል:: ከዚህ ቀደም ኦሮሚያን ጨምሮ ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ የስራ አስፈፃሚ አባላት ተመሳሳይ የመፈንቅለ መጅሊስ ሙከራ አድርገው ከሃላፊነታቸው መታገዳቸውን ፕሬዚዳንቱ አስታውሰዋል::

“ከሁለት ዓመት በፊት በህዝብ ተመርጠን፣ ህዝበ ሙስሊሙን ለማገልገልና መንግስትን ለመርዳት ወደ ስልጣን መጥተናል” ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህንን

እስልምና ወደ ገፅ 2 ዞሯል

# የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ከ90 ሚሊዮን አላለፈም ተባለ

### አለማቀፍ ተቋማት ወደ 100ሚ. ይጠጋል ይላሉ

አለማየሁ አንበሴ

የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ወደ 100 ሚሊዮን ተጠግቷል ቢሉም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሃገሪቱ ህዝብ ከ90 ሚሊዮን አላለፈም ብሏል::

ኤጀንሲው ትናንት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ከህዝብ ቆጠራ የተገኘ መነሻ የህዝብ ብዛት፣ ከስነ ህዝብና ጤና ጥናቶች የተገኙ የውልደትና የሞት መጠን፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትና የፍልሰት መጠን ስሌትን ጨምሮ የተባበሩት መንግስታት ስነ ህዝብ ተቋም የህዝብ ትንበያ አሰራርን በመከተል በተዘጋጀው ስሌት የዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ህዝብ

ህዝብ ወደ ገፅ 2 ዞሯል

ምንጩ ያልታወቀ ትኩሳት አለብዎ?

ታይፎይድ፣ ፌቨር መሆኑን ተጠራጥረዋል? ወይስ ወባ?
በጥቂት ደቂቃ በሽታው እንዳለብዎ ወይም እንደሌለብዎ ማረጋገጥ ይችላሉ:: ልዩ መመርመሪያ አዘጋጅተናል!! በኢንተሮቼክ ቴስት እና በማላስካን ስትሪፕ ወዲያውኑ ውጤቱን ያገኛሉ!!

LNB

አድራሻ ቸርችል ጎዳና ቴዎድሮስ አደባባይ ከፍ ብሎ ኤሌክትሪክ ወርልድ ሕንፃ አጠገብ
ስልክ 011-1-550336
ዩኒቨርሳል ከፍተኛ ክሊኒክ

# የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር፤ በፓርቲዎች ክፍፍልና በፖለቲካ ውዝግቦች ዙሪያ

*ውህደት ለመፈፀም ተደጋጋሚ ድርድሮችን ሲያካሂዱና ስምምነት ሲፈፅሙ የቆዩት አንድነት ፓርቲ እና መኢአድ፣ የውህደት ጅምራቸው ካለመሳካቱም በተጨማሪ በየፊናቸው ለሁለት ለሁለት ተከፍለው ሲወዛገቡ ነው የከረሙት። በመጨረሻም የምርጫ ቦርድ፣ ከመኢአድ ፓርቲ በአቶ አበባው መሃሪ ለሚመራ ቡድን፣ ከአንድነት ፓርቲ ደግሞ በአቶ ትዕግስቱ አወሉ ለሚመራው ቡድን እውቅና ሰጥቻለሁ ብሏል። እውቅና ያልተሰጠው በአቶ በላይ የሚመራው የአንድነት ቡድን ብዙም ሳይቆይ፣ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር ተቀላቅሏል። የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎች ቀደም ሲል አንድነት ፓርቲ ውስጥ እንደነበሩና በክፍፍል ምክንያት ወጥተው ፓርቲ እንዳቋቋሙ የሚታወስ ሲሆን የፓርቲው ሊቀመንበር ኢ/ር ይልቃል ጌትነት፤ በፓርቲዎች ክፍፍል እና በወቅታዊ የፖለቲካ ውዝግቦች ዙሪያ ለጋዜጠኛ ናፍቆት ዮሴፍ የሰጡትን አስተያየት አቅርበናል።*



የምርጫ ሰሞን የፓርቲዎች ክፍፍል

በየምርጫው የፓርቲዎች ግጭትና ክፍፍል የተለመደ ቢሆንም የዘንድሮው ይለያል። በመንግስት አቋም ተወስዶበት የተሰራ ነው። ገዢው ፓርቲ በራሱ ስራና ብቃት መመረጥ እንደማይችል አውቋል። ስለዚህ ህዝቡን አማራጭ ማሳጣት ይፈልጋል። በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ጥቃቅን ስህተቶችን በማጉላት እንዲሁም ሬዲዮ ፋናን፣ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንንና ምርጫ ቦርድን በመጠቀም፣ "የተቃውሞው ጎራ እርባና ቢስ ነው፤ ብትወደኝም ባትወደኝም ከእኔ ጋር ትኖራለህ" በሚል ህዝቡ ላይ ጫና ለማሳደር የመጫን ስራ ሆን ብሎ እየሰራ ይገኛል።

ለዚህም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአንድነት ላይ የወሰደውን ውሳኔና የሰጠውን መግለጫ ማየት ይቻላል። "የእነ ትዕግስቱ ቡድን ለእኛ ስለሚታዘዝና በእኛ ሃሳብ ስለሚስማማ እንጂ የራሱ ድክመት አለበት" በማለት አንድነትን ለእነሱ አፅድቆላቸዋል። ሌላው በእኛ በሰማያዊ ፓርቲ ላይ ቦርዱ የጀመረው ዘመቻ ነው። ይቅርታ እንድንጠይቅ ደብዳቤ ፅፎብን ነበር። እንደ ጥፋት ያቀረባቸው ነገሮች ግን እዚህ ግባ የማይባሉና ጥፋት ያልሆኑ ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በትብብር ለምን ሰራችሁ፣ ያልተመቸንን ስብሰባ ትተን መውጣት መብራታችን ሆኖ ሳለ እንዴት ረግጣችሁ ትወጣላችሁ በሚል ነው የመጨረሻ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ የፃፈልን። ሬዲዮ ፋናንና ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ብንመለከት፣ እንደሌሎቹ ፓርቲዎች እኛ ላይ ፕሮፓጋንዳ ለመስራት ጠሩኝ። አክብሬ ሄድኩኝ፤ እዚያው ሬዲዮ ፋና ስቱዲዮ ውስጥ ለሁለት ሰዓት ከተቀረፅኩኝ በኋላ መጨረሻ ላይ ፊልሙ ተበላሽቷል አይተላለፍም አሉኝ። እኛ የቀረፅነው ስላለ እንስጣችሁ አልናቸው፤ አልፈለጉም። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተመሳሳይ ጥያቄ ይዞ የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት አቶ ዮናታንን ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል አነጋገራቸው፤ ግን በቴሌቪዥን አልተሰራጨም። ይህ የሆነበት ምክንያት ለእነሱ ፕሮፓጋንዳ የሚመች መልስ ስላልሰጠን ነው። ይህን ሁሉ ስመለከተው መንግስት ሆን ብሎ ፓርቲዎችን ጥላሸት ለመቀባት ለህዝብ ለማሳየት እየተደረገ ያለ ጥረት መሆኑን እገነዘባለሁ።

ውዝግብ ወደ ገፅ 4 ዞሯል

# የለቡ አካባቢ ነዋሪዎች የተጣለባቸውን የመሬት ግብር ተቃወሙ

## *"ክፍያውን በቀድሞ ታሪፍ መቀጠል ይችላሉ፤ ቤታቸው ግን መለካት አለበት" - የወረዳው አስተዳደር*

ናፍቆት ዮሴፍ

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1፣ በተለምዶ ለቡ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ከ25 ሺህ በላይ ነዋሪዎች በካሬ ሜትር 0.50 ሳንቲም ሲከፍሉ የቆዩት የመሬት ግብር ወደ 3 ብር ማደጉ አግባብ አይደለም ሲሉ ተቃወሙ። ከ1990 ዓ.ም አንስቶ የመኖሪያ ቤት በማህበር ለመስራት ከመንግስት በሊዝ ቦታ መመራታቸውን ያስታወሱት ቅሬታ አቅራቢዎቹ፤ ቦታውን ሲወስዱ በካሬ ሜትር 0.50 ሳንቲም ሊከፍሉ መስማማታቸውንና እስከ 2005 ድረስ በተመሳሳይ ክፍያ መቀጠላቸውን ጠቁመው ከዚያ በኋላ በካሬ ሜትር ሶስት ብር እንዲከፍሉ መደረጋቸውን ይናገራሉ።"ይህን ክፍያ የከፈልነው በአስሩም ክፍለ ከተማ መመሪያ የወጣ መስሎን ነበር" ያሉት የቅሬታ አቅራቢዎቹ ተወካይ፤ በኋላ ጉዳዩን ሲያጣሩ ግን ከ1996 ዓ.ም በፊት ቦታ የተመሩትን የሶስት ብሩ ክፍያ እንደማይመለከታቸው ማወቃቸውን ለአዲስ አድማስ ተናግረዋል። ላለፉት ሁለት ዓመታት ያላግባብ የከፈሉት ክፍያ እንዲመለስላቸውና በ0.50 ሳንቲም ክፍያቸውን እንዲቀጥሉ በየተዋረዱ ላሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አቤት ቢሉም ምላሽ ማጣታቸውን የተናገሩት ቅሬታ አቅራቢዎቹ፤ ከጥቂት ወራት በፊት ችግራቸውን ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት መናገራቸውንም አስታውሰዋል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎችም በሬዲዮ ፋና ቀርበው፣ ከ1996 በፊት በሊዝ ቦታ የወሰዱትን በካሬ ሜትር 3 ብር ክፍያ እንደማይመለከታቸው ማረጋገጣቸውን ጠቅሰው፤ እነዚሁ ኃላፊዎች ወረዳው በአስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጣቸው እንደሚገባ መግለፃቸውንና ለወረዳው መሬት አስተዳደር የትዕዛዝ ደብዳቤ መፃፉን ነገር ግን እስካሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን ይናገራሉ። የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሌሎች ክፍለ ከተሞች ተመሳሳይ ስህተት ተፈፅሞ ከሆነ እንዲታረም በፃፈው ደብዳቤ፤ ከ1996 ዓ.ም በፊት በእጣና በምደባ ቦታ ተሰጥቷቸው በሊዝ ውል የገቡ ነዋሪዎች አዲሱ ታሪፍ እንደማይመለከታቸው መግለፁንም ጠቅሰዋል።

"እኛ ቤቱን የሰራነው መንግስት በሰጠን ፕላንና መመሪያ ነው፤ ከአፈር ግብር በተጨማሪም ጣሪያና ግድግዳ አስለክተን የከፈልንበት ደረሰኝ አለን" ያሉት ተወካዮቹ፤ የፕላንና የካርታ ለውጥ ሳያደርጉና ቤት በፎቅ መልክ ሳይቀጥሉ ይለካ መባሉ ግራ እንዳጋባቸው ነዋሪዎቹ ገልጸዋል። መንግስት አስለካሁ ካለ ማስለካት እንደሚችል፤ ነገር ግን ለመሃንዲስ 500 ብርና ለታክሲ 300 ብር ክፈሉ መባላቸውን እንደማይቀበሉት ነዋሪዎቹ በአፅንኦት ተናግረዋል።

ጉዳዩን በተመለከተ ያነጋገርናቸው የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣ የወረዳ አንድ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ታሪክ ፍቅሬ፤ የነዋሪዎቹ ቅሬታ ተገቢነት እንዳለው አልካዱም። ወደ ኃላፊነቱ ከመጡ ገና 15 ቀናት ብቻ እንዳስቆጠሩ የጠቆሙት ዋና ስራ አስፈፃሚው፤ 0.50 ሳንቲም መክፈል እያለባቸው በካሬ ሶስት ብር መክፈላቸው ስህተት መሆኑን አምነው፣ እስከዛሬ የከፈሉት እላፊ ሂሳብ በወደፊት ክፍያቸው ላይ ይታሰብ ወይስ ይመለስላቸው በሚለው ላይ ከሌሎች ኃላፊዎች ጋር ተነጋግረው ምላሽ ለመስጠት ለፊታችን ረቡዕ ቀጠሮ መያዙን ገልፀዋል።

ከአሁን ጀምሮ ነዋሪዎቹ ክፍያቸውን በ0.50 ሳንቲም መቀጠል እንደሚችሉ የተናገሩት አቶ ታሪክ፤ ነገር ግን የቤቱን ግድግዳና ጣሪያ የማስለካት ግዴታ እንዳለባቸው ገልፀዋል። ቅሬታ አቅራቢዎቹ በበኩላቸው፤ አሁን ክፍያ እንድንፈፅም ጠይቀን ካላስለካችሁ መክፈል አትችሉም ስለተባልን ግራ ገብቶናል፤ ለቅጣትም ልንዳረግ ነው ብለዋል።

አቤቱታቸውን ለወረዳው ገቢዎች ፅ/ቤት ሊያቀርቡ ገብተው በጽ/ቤቱ ኃላፊ ዘለፋና ስድብ እንደደረሰባቸው የገለፁት ተወካዮቹ፤ ህዝብን ሊያገለግሉ የተቀመጡ ሰዎች አያቶቻቸው የሚሆኑ ሰዎችን መሳደብና ማዋረዳቸው አግባብ አይደለም ሲሉ ነቅፈዋል።

የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ፤ የቤት ማስለካቱ ጉዳይ ተገቢ ነው አይደለም፣ በሶስት ብር ሂሳብ የከፈሉት ክፍያ ልዩነቱ ታስቦ ይመለስ ወይስ በወደፊት ክፍያቸው ላይ ታሳቢ ይሁን፣ ለመሃንዲስና ለታክሲ ይከፈል የተባለው 800 ብር ተገቢ ነው አይደለም የሚለውንና ተያያዥ ጉዳዮችን ከሌሎች የስራ ኃላፊዎች ጋር መክረው የፊታችን ረቡዕ ምላሽ እንደሚሰጡ ለአዲስ አድማስ ተናግረዋል።

### በረራ ከገፅ 1 የዞረ

የተከሰተውን የድንበር ግጭት በድርድር ለመፍታት የተጀመረው ጥረት መስተጓጎሉን ተከትሎ፣ በአካባቢው የነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው በሚል የበረራ እገዳው እ.ኤ.አ በ2000 ግንቦት ወር መጣሉን የጠቀሰው የባለስልጣኑ መረጃ፣ እገዳው መነሳቱ በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት መጽደቁን ተከትሎ፣ የአሜሪካ አውሮፕላኖች በየትኛውም የኢትዮጵያ የአየር ክልል ውስጥ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ አስታውቋል።

### እስልምና ከገፅ 1 የዞረ

ህጋዊ አሰራር ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆኑ ጥቂት ህገወጥ ግለሰቦች የሚፈፅሙት ስርዓት አልበኝነት መቀጠል እንደማይችል ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በየዓመቱ በየካቲት ወር የሚካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፤ በጉባኤው ላይ አሉ የተባሉ ችግሮችን በማንሳት ውይይት ተደርጎበት ውሳኔ እንደሚተላለፍ ተናግረዋል። በህገወጥነት ታግደው የቆዩት ሥራ አስፈፃሚዎች ጉባኤው ከፈቀደላቸው ብቻ በጠቅላላ ጉባኤው እንደሚሳተፉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት በቅርቡ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሰጠው መግለጫ፤ የፌደራሉ መጅሊስ ፕሬዚዳንት፤ ያለአግባብ የስራ ኃላፊዎችን በማገዳቸውና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ከስልጣናቸው መውረዳቸውንና ክልሉም ውክልናውን ማንሳቱን ማስታወቁ ይታወሳል።

# የ500ሺ. ብር ናፍጣ ሸጦ ቦቴ መኪናውን ያቃጠለ ሾፌር ተፈረደበት

አለማየሁ አንበሴ

ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ 36 ሺህ ሊትር ናፍጣ ከሸጠ በኋላ እንዳይታወቅበት የነዳጅ ማመላለሻ መኪናውን በእሳት አጋይቷል ተብሎ የተከሰሰ ሾፌር ሰሞኑን በፍ/ቤት ጥፋተኛ ተባለ።

ተከሳሹ ከጅቡቲ 44ሺህ ሊትር ናፍጣ የጫነ መኪና ወደ ጅማ ማድረስ እንደነበረበት የገለፀው አቃቤ ህግ፤ በመሃል የቦቴ መኪናውን እሽግ በመፍታት ከ36 ሺህ በላይ ሊትር በድብቅ ሸጧል ብሏል። ተከሳሹ ሹፌር ነዳጅ መስረቁና መሸጡ እንዳይታወቅበት፤ የተፈታውን እሽግ መልሶ በማያያዝ መኪናውን በእሳት አቃጥሎታል ብሏል - የፀረ ሙስና አቃቤ ህግ።

በጂማ ስኮሩ ወረዳ አካባቢ ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ.ም ማለዳ መኪናውን ከነተሳቢው ያቃጠለው በድንገተኛ አደጋ ቃጠሎ የደረሰበት ለማስመሰል ነው ሲልም ክሱን አስረድቷል። ሹፌሩ ሁዱሽ ገብረክርስቶስ በአቃቤ ህግ የተጠቀሰበትን ወንጀል እንዳልፈፀመ በመግለፅ፤ የተከራከረ ሲሆን፤ አቃቤ ህግ ግን ተከሳሽ መኪናውን ሲያቃጥል ታይቷል በማለት ምስክሮችን አቅርቧል። የተሸጠውና የተቃጠለው ነዳጅ ከ600 ሺ ብር በላይ እንደሚያወጣ አቃቤ ህግ ገልፆ፤ ከመኪናው ዋጋ ጋር የ2 ሚሊዮን ብር ንብረት ወድሟል ብሏል።

ጉዳዩን የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ወንጀል ችሎት፣ ሰሞኑን ተከሳሽ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ የሰጠ ሲሆን፤ የቅጣት ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት የቅጣት አስተያየት ለማድመጥ ለየካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል።

### ህዝብ ከገፅ 1 የዞረ

ብዛት 90 ሚሊዮን ነው ብሏል።

ከጠቅላላው የህዝብ ብዛት ውስጥ 45 ሚ. 250 ሺ. ወንዶች ሲሆኑ 44 ሚ. 825 ሴቶች መሆናቸውን የኤጀንሲው ትንበያ ያስረዳል። በኢትዮጵያ በአሁን ሰዓት አንድ እናት በአማካይ 4 ልጆች ትወልዳለች ተብሎ እንደሚገመትም ሪፖርቱ ይፋ ያደረገ ሲሆን የህዝብ ብዛቱ ከቁጥጥር ውጪ እንዳይሆን ዘመናዊ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ግንዛቤን በመፍጠር ለህብረተሰቡ ተደራሽ እየተደረገ ነው ተብሏል። የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ሽፋኑም ወደ 40 በመቶ መድረሱን ሪፖርቱ አመልክቷል።

የሃገሪቱ የህዝብ ብዛት ከክልሎች አንፃር በተቀመጠው መረጃ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ ሶማሌ እና ትግራይ በቅደም ተከተላቸው ከ1-5 ያለውን ደረጃ የያዙ ሲሆን በ1999 ዓ.ም በተደረገው የቤትና የህዝብ ቆጠራ 2.7 ሚሊዮን እንደነበር የተገለጸው የአዲስ አበባ የህዝብ ብዛት ወደ 3.2 ሚሊዮን ከፍ ማለቱ በሪፖርቱ ተመልክቷል።

ኢትዮጵያ በህዝብ ቁጥሯ ከአፍሪካ ሃገሮች ከናይጄሪያ ቀጥላ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትቀመጥ ከ50 ዓመት በኋላ ከአፍሪካ 1ኛ ትሆናለች የሚለው የተለያዩ ተቋማት ትንበያ ትክክል እንዳልሆነና የስታትስቲክስ ኤጀንሲው የትንበያ ቀመር፣ የህዝብ ቁጥር እድገት አማካይ መጠኑ እየቀነሰ እንደሚሄድ የኤጀንሲው የስራ አመራሮች ገልፀዋል።

ኤጀንሲው የመረጃ ክፍተቶችን ያስወግዳል ያለውን 4ኛውን የህዝብና ቤት ቆጠራ ከ3 ዓመት በኋላ በ2010 ዓ.ም ለማካሄድ የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶችን እያደረገ መሆኑም ተመልክቷል። የሃገሪቱ የህዝብ ብዛት ከ5 ዓመት በኋላ 100 ሚሊዮን እንደሚደርስና ከ20 ዓመት በኋላ ወደ 136 ሚሊዮን እንደሚጠጋ የኤጀንሲው የህዝብ ብዛት ትንበያ ያመላክታል።

በሌላ በኩል የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት በዘንድሮው ዓመት ከ98 ሚሊዮን ልቋል የሚል ሪፖርት ያወጣ ሲሆን ከ150 በላይ የሚሆኑ የዊኪፒዲያ ተቋማት እንደመረጃ ምንጭ የሚጠቀሙትና አለማቀፍ አጥኚዎችን በስሩ ያሰባሰበው "ዎርልድ ሜትር" በበኩሉ፤ የህዝብ ብዛቱ 98 ሚሊዮን 942 ሺህ መድረሱን ይፋ አድርጓል። የተባበሩት መንግስታት ሪፖርት ደግሞ የህዝብ ብዛቱ 92 ሚሊዮን ደርሷል ብሏል።

# “በፖለቲካ ትግሉ ውስጥ እንደ አሉባልታ ከባድ ነገር የለም”

- አቶ ልደቱ ከ15 ዓመት በፊት የትጥቅ ትግል አስበው ነበር
- ኢህአዴግ እያዳከመን ነው ማለት፣ የራስን ድክመት መናገር ነው
- ህብረት መፍጠር የአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን አልጠቀመም

*የፖለቲካ ተሳትፎ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በተለይ ከ97 ምርጫ በኋላ በተፈጠሩ አሉባልታዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን “ቴአትረ ቦለቲካ፤ አሉባልታና የአገራችን የፖለቲካ ገመና” በሚል ርዕስ አዲስ መጽሐፍ ያወጡት የቀድሞው የኢዴፓ ፕሬዚዳንት አቶ ልደቱ አያሌው፤ በመፅሐፋቸው ጭብጥና በአጠቃላይ በአገሪቱ ፖለቲካ ዙሪያ ከጋዜጠኛ ኤልሳቤት ዕቁባይ ጋር አውግተዋል፡፡*


አቶ ልደቱ አያሌው

*ከፖለቲካው ብዙ ርቀዋል -- አሁን ምን እየሰሩ ነው?*

በፖለቲካው ያለኝ ሚና ቢቀንስም አልራቅሁም። አሁን የስራ አስፈፃሚ አባል ስላልሆንኩ የእለት ተእለት ስራ ውስጥ የለሁም፡፡ በዚህ ምክንያት ከመገናኛ ብዙኃን ጋር አልገናኘሁም፡፡ የኢዴፓ የላዕላይ ምክር ቤት አባል ነኝ፡፡ በፓርቲው ውስጥ ባለኝ የኃላፊነት መጠን መስራት ያለብኝን እየሰራሁ ነው፡፡ በሚዲያ ስለማልቀርብ ከፖለቲካው መራቅ ብቻ ሳይሆን የተውኩ ሁሉ የሚመስላቸው አሉ፤ እውነታው ግን ያ አይደለም፡፡ በእርግጥ ሙሉ ጊዜዬን ለፖለቲካው ስለማላውል ሌሎች ስራዎችን እሰራለሁ፡፡

*“ቴአትረ ቦለቲካ” የተሰኘው አዲሱ መፅሃፍህ በዋናነት በአሉባልታ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን ነው--*

እዚህ መፅሀፍ ላይ ማስቀመጥ የፈለግሁት በአብዛኛው ሂደት ውስጥ የነበረውን ነገር ነው፤ አልፎ አልፎ የራሴን ጉዳይ ባስቀምጥም፡፡ ብዙ ጊዜ “ፖለቲካል ኮሬክትነስ” የምንለው ነገር አለ፡፡ ጉዳዩ እሱ አይደለም፤ ያለፍኩበትን ሂደት በነበረበት ሁኔታ አስቀምጬ፣ ሰዎች ሌላ ጊዜ እንደ እኔ ፖለቲካ ውስጥ ሲገቡ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ፈተና አስቀድመው እንዲያውቁት ነው፡፡ ሳያውቁት ገብተው በኋላ ላይ ችግር ከሚገጥማቸው... ምናልባትም ወደ ተስፋ መቁረጥ ከሚገቡ፣ ራሳቸውን አዘጋጅተው መቋቋም እንዲችሉ ለማድረግ ትንሽ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል ብዬ ነው የፃፍኩት። መፅሀፉ ላይ እንደገለጽኩት፤ መጀመሪያ ላይ አሉባልታ ብዙም አያስጨንቀኝም ነበር፤ “የሆነው ሆኗል፤ ያመንኩበትን አድርጌያለሁ፤ ሌላው ሰው የፈለገውን ቢል የኔ ችግር አይደለም፤ ነገሩ እየታወቀ ሲመጣ ሰዎች ሁኔታውንም እኔንም ይረዱኛል” የሚል አስተሳሰብ ስለነበረኝ፣ በጣም ጠንካራ በሆነ ሁኔታ ነው ተቋቁሜው የሄድኩት። ነገር ግን አንድ ቦታ ላይ ከዚያ አስተሳሰብ የተለየ፣ ምናልባትም ሰው መሆኔን በደንብ የሚነግረኝ ስሜት ተፈጠረ፡፡

ይህ በህይወቴ ላይ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶኛል። ሁላችንም ሰዎች እስከሆንን ድረስ የሚወጣ የሚወርድ፣ የሚፈራረቅ ስሜት አለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሳታውቂው በውስጥሽ የተከማቸ ነገር እንደዚያ አይነት ሁኔታ ሲያገኝ ሊወጣ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ ይህንን ማስቀመጡ ተገቢ ነው በሚል እንጂ ያለፈ ነገር ነው፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ ማለፍ ምን ማለት ነው የሚለውን ለመረዳት እድል የሰጠኝ አጋጣሚ ነው፡፡ በፖለቲካ ትግሉ ያለኝን ተሳትፎ እንዳቆም ወይም እንዳለዝብ አሊያም ወደ ተስፋ መቁረጥ እንድሄድ ያደረገ ነገር አይደለም፡፡ በትግሉ እቀጥላለሁ፡፡ በእርግጥ የእድሜም ጉዳይ አለ፤ ለአዲሱ ትውልድ ቦታ መልቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ግን ይህን ምክንያት አድርጎ ከትግል መራቅ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ፖለቲካ ፈቅጄ፣ ወድጄ፣ አምኜ የገባሁበት ስለሆነ፣ ያሳለፍኩት ሂደት በጣም ከባድ ቢሆንም ወደፊትም የምርቀው ነገር አይደለም፡፡

*በኢትዮጵያ ፖለቲካ አሉባልታን በመኮትኮት ተሰሚነት እንዲያገኝ ያደረጉት ራሳቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የመገናኛ ብዙኃን ናቸው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እርስዎስ በዚህ ይስማማሉ?*

ለእኔ አንዱ ለሌላው ያቀበለው ባህል አይመስለኝም፡፡ ችግሩ ሁሉም ላይ የነበረና ያለ በመሆኑ ተመጋጋቢ ነው፡፡ ሁላችንም የዚህ ህብረተሰብ ውጤቶች ነን፡፡ በእኔ እምነት አሉባልታ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ወይም የፕሬሱ ብቻ አይደለም፤ በአጠቃላይ እንደ ህብረተሰብ ያለብን ችግር ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የአሉባልታ ሰለባ ቢሆን ወይም አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የአሉባልታ አራማጅ ቢሆን የጉዳቱ መጠን ብዙ ላይሆን ይችላል፡ ፡ ግን ህብረተሰብን ለማስተማር፣ የህብረተሰብን አስተሳሰብ ለመቅረፅ የተቋቋመ መገናኛ ብዙኃን የአሉባልታ ሰለባ ሲሆን ጉዳቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ ነው የፕሬሱን ጉዳይ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመጽሃፌ የጠቃቀስኩት። በጋዜጣ የተፃፈ፣ በራዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የተነገረ ነገር ሁሉ እውነት መስሎ የሚታየው የህብረተሰብ ክፍል አለ፡፡ በአፍሽ ስትነግሪው ውሸት የሚመስለው ነገር፣ በመገናኛ ብዙኃን ሲገለጽ፣ እውነት የሚመስለው ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍል አለ፡፡ ችግሩ ፕሬሱ ውስጥ አለ፣ ፓርቲዎቹ ውስጥ አለ፣ ህብረተሰቡ ውስጥ አለ፡፡ አሉባልታውን የማቀባበሉ ሚና፣ ከአንዱ ወደ አንዱ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን የመገናኛ ብዙኃን ከዚህ ካልፀዱ፣ አንድ አገር ትልቅ አደጋ ውስጥ ነው ማለት ነው፡፡

*በአገሪቱ ያለውን ፕሬስ እንዴት ያዩታል?*

እንግዲህ ሁሉ ነገር እኛ አገር ላይ ገና ነው፡፡ ያለን የፖለቲካ ባህል በጣም ኋላቀር ነው፡፡ በዚህ ኋላቀር ባህል ውስጥ ሆነን ሚዲያው ለብቻው ተለይቶ፣ ከችግር ነፃ ሆኖ ሊያድግ አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ሚዲያ ከችግር የፀዳ ሆኖ እንዲወጣ አልጠብቅም፡፡ ቁጥሩ አነሰም በዛም በሚጠበቀው ደረጃ ላይ አይደለም፡፡ ይህን ስል ሁሉም ፕሬሶች ተመሳሳይ ድክመትና ችግር ነበረባቸው ማለት አይደለም፡፡ በአንፃራዊነት የተሻለ የሚሰሩ ነበሩ፤አሁንም አሉ፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዳይሸጋገር፣ የፖለቲካ ባህላችን እንዳያድግ በማድረግ ረገድ መገናኛ ብዙኃን፣ በተለይ ነፃው ፕሬስ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የፕሬሱ ሚና መረጃ ማቀበልና መቀበል ብቻ አልነበረም፤አጀንዳ ቀርፆ ለፖለቲካ ሀይሎች የማቀበልም ሚና ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡

*አሁን የፕሬስ ውጤቶችን ያነባሉ?*

አልፎ አልፎ አነባለሁ፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቼ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ዙሪያ ያሉ ሰዎች እንዲህ አይነት ፅሁፍ ወጥቷል አንብብ ቢሉኝ እመርጣለሁ፡፡ እንደ በፊቱ ሰፊ ጊዜ ወስጄ አላነብም፡፡ መፅሀፌ ላይ እንደገለፅኩት፣ እኔን ጨምሮ አብዛኞቻችን፣የፖለቲካ አስተሳሰባችን የተቀረፀው ኢህአዴግ እንደገባ በነበሩት የግል ፕሬሶች ነው፡፡ ያኔ ሁሉንም ትክክል ነው ብሎ የመውሰድ አዝማሚያ ነበረኝ፤ ትክክል እንዳልሆነ የተማርኩት በሂደት ነው፡፡

*በፖለቲካ እንቅስቃሴው ውስጥ “ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?” ያስባልዎት የተለየ ክስተት ምንድነው?*

አሉባልታ በዚህ መጠን ችግርና ተፅዕኖ ይፈጥራል ብዬ አስቤ አላውቅም፡፡ የተወሩብኝ ነገሮች እውነት እንዳልሆኑ እየታወቀና እየታየ እንኳን አልቆመም ነበር፡፡ የተወራው ነገር ውሸት ለመሆኑ አንደኛ ምስክር ቅንጅት ውስጥ የነበሩ ሰዎች ናቸው። አንዳቸውም ግን ምንም አላሉም፡፡ ህብረተሰቡም

ፖለቲካ ወደ ገፅ 11 ዞሯል



ርዕሰ አንቀፅ

# ዛፉ ሲወድቅ ዝንጀሮዎቹ ይበተናሉ - የቻይናዎች አባባል

የተረት - አባት የሆነው ኤዞፕ እንዲህ ይለናል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ተኩላዎች ተመካከሩና መልዕክተኞች ወደ በጐች ላኩ፡፡

የተኩላዎቹ ልዑካን እበጐች መንደር ደረሱ፡፡ በጐች ተኩሎች መጡብን ብለው ተሸሸጉ፡፡ አድፍጠው ጋጣቸው ውስጥ አድብተው ተቀመጡ፡፡ ተኩሎቹ ግን ረጋ ብለው፣ አደብ ገዝተው፤ "በጐች አትደናገጡ" "እንደምና ዋላችሁ" አሉ፡፡

"ድርድር ነው የመጣነው" አሉ ተኩሎቹ፡፡ በጐቹ ቀስ በቀስ ከተደበቁበት ወጡ፡፡

"እኛ በድርድር እናምናለን፡፡

እህስ? ምን እግር ጥሏችሁ መጣችሁ? ምን የድርድር ሃሳብ ይዛችሁ መጣችሁ?" አሉ በጐች፡፡

"አንድ የቸገረ ነገር ገጥሞን ነበርና ልናዋያችሁ ፈልገን ነው"

"ምንድነው? ከተመካከርን የማይፈታ ምንም ነገር አይኖርም፡፡ ዋናው ተቀራርቦ መነጋገር ነው ንገሩን፡፡"

ተኩሎችም፤

"እግዚአብሔር ይስጥልን፡፡ የቸገረን ነገር ምን መሰላችሁ? ይኸው ከተፈጠርን ጀምሮ ከውሾች ጋር ነጋ - ጠባ እንታገላለን፡፡ የችግራችን መነሻም መድረሻም ውሾች ናቸው፡፡ እርኩስ ውሾች እኛን ባዩ ቁጥር ይጮሃሉ፡፡ ይተነኩሱናል፡፡ ሠፈር ይረበሻል! ለእኛ ለእናንተ ወዳጅነትና ሰላም ዋናዎቹ እንቅፋቶች ውሾች ናቸው፡፡"

በጐችም፤

"ታዲያ ምን እናድርግ? ምን ዘዴ ብንፈጥር እንቅፋቶቹን ማስወገድ እንችላለን?"

ተኩሎችም፤

"እናንተ እሺ ካላችሁማ ዘዴ አይጠፋም ነበር"

"እኮ ዘዴ ካለ ነገሩና?"

"ለጌታችሁ ንገሩ፡፡ ውሾች እንዳልተመቿችሁ፣ ሰላምም እንደነሷችሁ አስረዱ፡፡ ይባረሩልን በሉ!"

"ይሄማ ቀላል ነው፡፡ እንነግረዋለን፡፡"

በዚህ ተስማሙና ተኩሎቹ ሄዱ፡፡

በጐቹ፤ ውሾቹ እንዲባረሩ ለጌታቸው አመለከቱ፡፡ ጌታቸውም ስንት ዘመን ቤት - ደጁን ይጠብቁ የነበሩትን ውሾች ከቤት አስወጥቶ አባረራቸው፡፡

ከዚያን ቀን በኋላ፣ የዋሆቹ በጐች የዘመናት ጠባቂዎቻቸውን አጡ፡፡ ተንኮለኞቹ ተኩሎች እየተዝናኑና በጐቹን አንድ በአንድ እየለቀሙ፤ በሏቸው፡፡

* * *

የድርድርን ትርጉም አለማወቅ እርግማን ነው፡፡ ከማን ጋር ነው የምደራደረው? ተደራዳሪዬስ ሊደራደረኝ ያሰበው ምን አስቦ ነው? ጠላቴ እንኳ ቢሆን ድርድሩ ያዋጣኛል ወይ? ከቅርብ ጊዜ ግቤ አንፃር ምን እጠቀማለሁ? ከዘለቄታ ግቤ አንፃርስ ምን እጠቀማለሁ? ትላንትና ምን ዓይነት ግንኙነት ነበረኝ፡፡ ዛሬስ? ዛሬን በዛሬው ክስተት መዳኘት እንዴት እችላለሁ? ብሎ ማሰብ የአባት ነው፡፡

በሁለኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአሜሪካው ጄኔራል ማካርተር በፊሊፒንስ የአሜሪካ ጦር አዛዥ ተደርጐ ሲሾም አንድ ረዳት መኰንን አንድ መጽሐፍ ይሰጠዋል፡፡ መጽሐፉ ከዚህ ቀደም የነበሩት አዛዦች የዋሉባቸውን ጦርነቶች ዝርዝር የያዘ ነው፡፡ ማካርተር "የዚህ መጽሐፍ ስንት ቅጂ አለ?" ብሎ ጠየቀው፡፡ ረዳቱም "ስድስት አሉ" አለው፡፡ ጄኔራሉም "መልካም፡፡ በል ስድስቱንም መጽሐፍት ሰብስበህ አቃጥልልኝ፡፡ እኔ የትላንትና ውሎዎች ባሪያ መሆን አልፈልግም፡፡ ችግር ሲከሰት እዛው ወዲያውኑ መፍትሔ እሰጠዋለሁ፡፡ መጽሐፍቱን በሙሉ አቃጥልና ሁኔታዎች በተከሰቱ ሰዓት እንደ ሁኔታው ግዳጅህን ፈጽም" አለው፡፡ ታሪክ የራሱ ዋጋ ቢኖረውም ያንን እንደ ተመክሮ መውሰድ ተገቢም፣ ደንብም ነው፡፡ በትላንት ለመመካት ከሆነ ግን የግብዝ አመድ - አፋሽ መሆን ነው!

"ነበርን ማለት ግን ከንቱ ነው፣ ተው ነው መጀነኑ በቅቶን

ጉራ መንዛት መዘባነን፣ የሚያዛልቅ ዘዴ ባይሆን!" ይለናል ኦቴሎ የሼክስፒሩ፤

በፀጋዬ ገ/መድህን ብዕር ልሣን! ስለታሪክ፣ ስለትላንት ማውራት ሳይሆን ዛሬን ማሸነፍ ነው የፖለቲካ ፋይዳው! ይሄን ያወቁ ላቁ! ይሄን የናቁ ወደቁ! እንደማለት ነው፡፡

ከ1966 ጀምሮ የተከሰቱ የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች አበሳዎች፤ እከሌ ከእከሌ ሳይባል በትንሹ አሥር መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የተንተራሱ ይመስላሉ፡፡ ከአበሳዎቹ፤ አንደኛው/ በትንሽ በትልቁ መከፋፈል፣ ያለመስዋዕትነት ድል መመኘት፣ ውሎ አድሮ ጧት የማሉበትን ማታ መካድ፡፡ "ዕምነት ሲ.ታመም፣ ሺ ወረቀት መፈራረም" ነው፡፡ 2ኛው/ ለባላንጣቸው ሠርጐ - ገብነት መጋለጥ ነው፡፡ 3ኛው/ እርስ በርስ አለመከባበር፣ አለመተሳሰብ 4ኛው/ የመስመር ጥራት አለመኖር ርዕዮተ - ዓለማዊ ብስለት ማጣት 5ኛው/ በትንሽ ድል መወጣጠርና በትንሽ ሽንፈት መፍረክረክ 6ኛው/ ተጋጣሚን መናቅና ወሬን/አሉባልታን እንደ አቋም ወሱድ 7ኛ/ የጊዜን ፋይዳ በትክክል መረዳት፣ ባልፈውስ? አለማለትና የኃይል ሚዛን የማን ነው አለማለት፣ ከተፈፀመም አለመመዘን፣ ይሄ ዓላማ ባይሳካ ምን ሁለተኛ ዘዴ ቀይሻለሁ? ብሎ አለመዘጋጀት፡፡

8ኛው/ ባለፈው ያረግነው የት አደረሰን? ታሪኩ ተተንትኖ ተገምግሞ ሳያልቅ በነዚያው ተዋንያን ተውኔቱ መቀጠሉ 9ኛው/ እምቢ አላረጅም ማለት ነው፡፡ አዲሱ ያሸንፈኛል አለማለት The new is invincible የሚለውን መርሳት "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ማለት፡፡ 10ኛው/ እኔ ባልሆንስ መፍትሔው? ሌላ ቢኖርስ ከኔ የተሻለ አለ ብሎ ፈጽሞ አለማሰብ...

ከነዚህ ሁሉ ይሰውረን፡፡ እነዚህን ሁሉ ከልብ ከመረመርን ፓርቲዎቹ ሁሉ የቆሙት በአንድ ወይም በጥቂት ቡድን ሐብለ ሠረሠር (Spinal cord) ዙሪያ ነው፡፡ ይሄ እንግዲህ የሚሆነው፤

"ከተኳሾቹም - አሉ በልዩ

ማህል - አገዳ የሚለያዩ"

በምንልበት አገር ነው፡፡ ከፖለቲካ ንቃተ - ባህሉ (ትምክህቱ ጥበቱ፣ ዕምነቱ፣ የፖለቲካ ጥንቆላው፣ ሟርቱ ወዘተ) ባለበት አገር ልማድን አለመመርመር ጦሱ ብዙ ነው፡፡ አጠቃላይ የፖለቲካ ተመክሮአችን ገና አልተፈተሸም፡፡ "ዳሩ ሲነካ መሀከሉ ዳር ይሆናል" ይላል ያበሻ አባባል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን ግንዱ ሲመታ ቅርንጫፉና ቅጠሉ መርገፉ አይቀሬ ነው፡፡ ቻይናዎቹ "ዛፉ ሲወድቅ ዝንጀሮዎቹ ይበተናሉ" የሚሉን መሠረታዊ ነገር የሚሆነው ለዚህ ነው! "ቁልቋል የወደቀው ቅርንጫፍ ስላበዛ ነው" የሚለውም የትግሪኛ ተረት አዙረን ስናየው እንደቻይናዎቹ ነው!!

## ፖለቲካ ከገፅ 3 የዞረ

"አንድነት" ለሁለት ስለመሰንጠቁ

እኔ በበኩሌ አንድነት ለሁለት ተሰነጠቀ ለማለት እቸገራለሁ፡፡ ምክንያቱም ቅር ተሰኘን የሚሉ ጥቂት ሰዎች ሄደው ለምርጫ ቦርድ ቅሬታ አቀረቡ፡፡ ከስራ አስፈፃሚው እስከ ታች ያለው የፓርቲው መዋቅር ግን በእነ አቶ በላይ ፍቃዱ የሚመራ ነው፡፡ የፓርቲው የብሔራዊ ም/ቤት አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ፣ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሰብሳቢ፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች ኃላፊ... ከእኛ ጋር የተቀላቀሉት ናቸው፡፡ ሌላው አንድነት የት አለ? ከእኛ ጋር ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት የፓርቲው ትልቁን የኃላፊነት ቦታ የያዙት ስለሆኑ እኔ አንድነት ተሰነጠቀ አልልም፤ ከኛ ጋር ተዋሃደ እንጂ አልተሰነጠቀም፡፡ በአሁኑ ሰዓት እዚህ እየመጡ እየተመዘገቡ ነው በክልልም ለምርጫው እጩ እስከማቅረብ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ እስካሁን ከእኛ ጋር የተቀላቀሉትን ብዛት በቁጥር ለመግለፅ እቸገራለሁ፡፡ በአጠቃላይ በአቶ በላይ ፈቃዱ ሲመሩ የነበሩት እውነተኛዎቹ የአንድነት አባላት ከነመዋቅራቸው ወደ እኛ መጥተዋል፡፡

"አንድነት በሰማያዊ ሴራ ፈረሰ" ስለመባሉ

በብዕር ስም ተፅፎ የወጣው፤ ዘገባ ሃሰት ነው፡፡ ምክንያቱም በእስር ላይ ያሉትን እነ ሃብታሙ አያሌውን ሁልጊዜ እናገኛቸዋለን፡፡ እንደውም ወደፊት አብረን ስለምንሰራበት ሁኔታ በየጊዜው እንወያያለን፡፡ ከሃብታሙም ሆነ ከየሺዋስ ጋር ጓደኛሞች ነን፡፡ የአንድነት ከፍተኛ አመራሮችና አባላት ወደ ሰማያዊ ፓርቲ በመግባታቸው ኢህአዴግ በደረሰበት ድንጋጤ ሆን ብሎ የሚያስወራው ነው፡፡

እዚያ ዘገባ ላይ ከተፃፈው አንድ ምሳሌ ልንገርሽ፡፡ በበላይ ፍቃዱ የሚመራው ቡድን በዶ/ር ያዕቆብ ሽምጋይነት ከሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ጋር በተናጠል ሲደራደር ቆይቷል ተብሎ ተፅፏል፡፡ ይሄ አይን ያወጣ ውሸት ነው፡፡ እኔና በላይ ፍቃዱ ከጓደኝነታችን የተነሳ ለመገናኘት ሽማግሌ አያስፈልገንም፤ ሁልጊዜም ቢሆን እየተገናኘን በአገራችን ወቅታዊ በጎና መጥፎ ጉዳዮች ላይ ሌት ተቀን የምንነጋገር የምንከራከር ነን፡፡

እኔና ዶ/ር ያዕቆብ አንድ ላይ ሆነን ሻይ ጠጥተን እንደማናውቅ ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ፡፡ ይሄ ሁሉ የሚመራብን ወሬ የኢህአዴግን ድንጋጤ የሚያሳይ ነው፡፡

እንደ ክፍፍሉ ውህደቱ መፍጠኑ

አሁን ጥቃቅንና አነስተኛ የፕሮግራም ልዩነቶችን እያነሳን ጊዜ የምናባክንበት ወቅት ላይ አይደለንም፡፡ በመሰረቱ አንድነትና ሰማያዊ በአብዛኛው ፕሮግራሞቻቸው ላይ ልዩነት የላቸውም፡፡ ስለዚህ ዋና ዋናዎቹ ላይ ከተስማማን በጥቂትና ጥቃቅን የፕሮግራም ልዩነቶች ላይ በሂደት በውይይትና በክርክር የምንስማማባቸው ይሆናሉ፡፡ አብረን ለመስራት የሚከለክሉን ስላልሆኑ ይሄ አያስጨንቀንም፤ በአሁኑ ሰዓት እንደ ቁምነገር የምናነሳው አይደለም፡፡

የአንድነት አባላት በሰማያዊ ፓርቲ ውስጥ የሚኖራቸው የአመራር ቦታ

ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት ወደኛ የመጡት የአንድነት ሰዎች በትልልቅ የአመራር ቦታ ላይ የነበሩ ናቸው፡፡ በፓርቲው ስልጣንና ሹመት ውስጥ ብቻ ሳይሆን አሁን አዲስ አበባ ላይ በምናቀርባቸው እጩዎች ላይ ጥሩ ጥሩ ተፎካካሪዎችን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የመመረጥ መብታቸው እስከ ከፍተኛ አመራር ድረስ ክፍት ስለሆነ መብታቸው ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በተደጋጋሚ ተነጋግረንበታል፡፡ አሁን ከተቀላቀሉን ውስጥ ብዙዎቹ ጥሩ ጥሩ የአመራር ብቃት ያላቸው ስለሆኑ ለፓርቲያችን ያስፈልጉናል፡፡ በፓርቲው ወሳኝ ወሳኝ ቦታ ላይ ገብተው የመስራት መብት አላቸው፡፡ በቀሪው አንድ ሳምንት ውስጥ በእጩነት እንዲገቡም እናደርጋለን፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሁሌም "ፓርቲዎች ትከፋፈላላችሁ፤ አትግባቡም" እንባለለን፡፡ ይሄ ቁጭት በውስጣችን እያለና ገዢው ፓርቲ ሆን ብሎ "ተጣልተዋል፤ ተከፋፍለዋል" የሚለውን ስራዬ ብሎ በተቆጣጠራቸው ሚዲያዎች እያናፈሰ ባለበት አስቸጋሪ ሰዓት ፓርቲያችንን የሚያግዝና የሚያጎለብተን ኃይል ሲመጣ እንዴት አንደሰትም፡፡ ከዛ በተረፈ በሁለቱም ፓርቲዎች በኩል ያለን ሰዎች የምንተዋወቅና የምንግባባ ስለነበርን እንደ አዲስ አንተያይም፤ አብረን ለመስራት ሁሉንም ነገር ያቀልልናል፡፡

ለምርጫ ስላቀረቧቸው እጩዎች ብዛት

እስካሁን ፓርቲያችን በአገር አቀፍ ደረጃ ወደ 400 የሚጠጉ እጩዎችን አስመዝግበናል፡፡ አሁን ደግሞ እጩ የማስመዝገቡ ሂደት ለአንድ ሳምንት ተራዝሟል፡፡ በዚህ በቀረን አንድ ሳምንት አዲስ ከተቀላቀሉን ሰዎች ውስጥ የምናስመዘግባቸው ይኖራሉ፡፡ በአጠቃላይ የእጩዎቻችን ቁጥር ወደ 500 ከፍ ሳይል እንደማይቀር እገምታለሁ፡፡ መጀመሪያ ላይ ልናስመዘግብ ያቀድነው የእጩዎች ብዛት 300 ነበር፡፡

በምርጫ ዘመቻ የፓርቲዎች ስህተትና ትኩረት

ምርጫው እየቀረበ እንደመሆኑ መጠን በውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው የምንገኘው፡፡ በትናንሽ ጉዳዮችና በእርስ በርስ ፉክክር ላይ ከማተኮር ይልቅ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ትልቁን የአገራቸውን ምስል እንዲያዩ እመክራለሁ፡፡ ልዩነትም ቅራኔም ቢኖር መቻቻልና ቅራኔን በጥበብ በመያዝ ለውጤት ወደሚያበቃ ትግል ተጠናክረን መግባት አለብን፡፡ ዛሬ የምንሰራው ስህተት ልብ የሚሰብርና ህዝቡን ተስፋ የሚያሳጣ እንዳይሆን በመጠንቀቅ በጥበብ መጓዝና ለምንታገልለት ህዝብ የተስፋ ብርሃን መፈንጠቅ ይኖርብናል፡፡ ፓርቲዎች የገዢውን ፓርቲ ከፋፋይ ሴራ በማወቅ፣ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

አዲስ አድማስ

ሥራ አስኪያጅ:- ገነት ጎሳዬ
(ልደታ ክ/ከ ቀበሌ 04/06 የቤ.ቁ.581) ስልክ 0911-936787
ዋና አዘጋጅ:- ነቢይ መኮንን
(ቂ/ክ/ከ ቀበሌ 08/09 የቤት.ቁ.213)
ም/ዋና አዘጋጅ:- ኢዮብ ካሣ
ከፍተኛ አዘጋጅ:- ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር
አዘጋጅ:- ኤልሳቤት ዕቁባይ

ታኅሣሥ 29 ቀን 1992 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡ ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ
አሣታሚ ፡- አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃየተ.የግ.ማ.
አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 / የቤት ቁ.984

ከፍተኛ ሪፖርተሮች:- መንግስቱ አበበ፣ ግሩም ሠይፉ፣
አበባየሁ ገበያው ፣ መታሰቢያ ካሳዬ፣ናፍቆት ዮሴፍ፣ አለማየሁ አንበሴ
ሌይ አውት ዲዛይነር :- ኮከ አሰፋ፣ ንግሥት ብርሃነ
አርቲስት :- ሠርፀድንግል ጣሰው
ሽያጭና ስርጭት :- ሰለሞን ካሣ
ፎቶግራፈር :- አንተነህ አክሊሉ
ዌብፔጅ :- አስቴር ጎሳዬ
ኮምፒውተር ጽሑፍ :- የወብዳር ካሣ፣ ሃና ገ/ሚካኤል

አድራሻ:- ካዛንችስ፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ገባ ብሎ፣ ከጤና ጣቢያው ጀርባ
ቂርቆስ ክ/ከ ቀበሌ 31 ፤ የቤት ቁ.376
ስልክ፡- 0115-155-222/ 0115-153-660 ሞባይል፡- 0921-622-040/
0911-201-357 / **0935-98-74-44 / 0118699024**
ፋክስ፡- 0115-547373 ፖ.ሳ.ቁ 12324
E-mail :- admassadvert@gmail.com/ addisadmass@ethionet.et
website www.addisadmassnews.com

## የጉዞ ማስታወሻ

# ከውሃ እስከ ውሃ

ነቢይ መኮንን

አሁንም አሶሳ ነኝ፡፡ የመጨረሻው ሰዓት ላይ! ስንጓዝ ውለን ደርሰን፤ በግድቡ ዙሪያ ምሣ አለ የተባለበት ቦታ ሰልፍ አለ፡፡ ረሀብ አለብን፤ ግርግር አለ፡፡ ምሬት በሽበሽ ነው፡፡ ምሳ ግን የለም፡፡ ሰው ወዲያ ወዲህ ይላል፡፡ በሚቀጥለው ፕሮግራም ይሄ ይሄ ነው የሚል አንዳችም ሰው አልተገኘም፡፡ (ብሄር ብሄረሰቦች ትናንት ማታ አምሽተን ስለገባን ራት አልበላንም እያሉ ነው፡፡ አይዟችሁ የሚል አላገኙም፡፡) እኔና ኃይሉ ፀጋዬ ከብዙ መንገላታት በኋላ የግዢ ምግብ ፍለጋ መንገድ ጀመርን፡፡ አንድ የአገሬው ወጣት "ኑ ምግብ ያለበት ላሳያችሁ" ብሎን የጀማውን የሰልፍ ትርምስና ምግብ ቦታ ጥለን ልጁን ተከተልነው፡፡ የግድቡ ሰራተኞች መኖሪያ በሚመስሉ ቤቶች እያቆራረጥን ሄደን አንድ ትልቅ መዝናኛ ክበብ መሰል አዳራሽ ደረስን፡፡ የአዳራሹን ግማሽ የእንግሊዝ ፉትቦል ተመልካቾች ይዘውታል፡፡ ወደ ቲቪው ፊታቸውን መልሰው፣ ጀርባቸውን ለእኛ ሰጥተውናል፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን ከእናት ክፍላችን ተነጥለናል፡፡ እኛም የት አሉ? አንል፡፡ እነሱም የት ደረሱ አይሉን! ለነገሩ ቀድሞም ቅጥ አልነበረን፣ አሁምን ቅጥ የለንም!

ባለ ክበቦቹ ሽሮና ጥብስ አለን ይላሉ፡፡ መክፈያውና መስተናገጃው የተለያየ ቦታ ነው። ምግቡ እስኪመጣ ቢራ አዘዝን፡፡ በመጨረሻ፤ የተገኘውን፣ ቤት ያፈራውን ቀመስን፡፡ ቀጥሎ የማታ መኝታ ድልድል፤ አልጋ ወደሚሰጥበት ሄድን፡፡ እግዜር ይስጣቸው፡፡ እነዚህ ወዲያው አልጋችንን ሊሰጡን ቃል ገቡ፡፡ አንድ ሰው ተመደበልን። ይዞን ሄደ፡፡ ሳሙና፣ ሶፍት ከአዲስ አንሶላ ጋር ሰጠን። ለነገሩ የሚነግረን ጠፍቶ ነው እንጂ ስማችንና ክፍላችን በቢሮው ግድግዳ ላይ ተለጥፎ ነበር አሉ፡፡ አንዳንድ፤ አመራር ውስጥ ጭምር ያሉ ወዳጆቻችንጋ፣ ስንደውል እነሱ ጥሬ ስጋ ጭምር ተመግበው እንደነበርና አሁን እየተዝናኑ መሆኑን አወቅን፡፡

"ዓለም አላፊ ነው - መልክ ረጋፊ ነው - ፎቶግራፍ ቀሪ ነው!" ተባባልን - እኔና ወዳጄ! በየአልጋችን አረፍ አልን፡፡ በኋላ የተባለውን ክለብ አገኘነው፡፡ ይብላኝ ገንዘብ ለሌላቸው ለምስኪኖቹ ባለ ጉዳዮች እንጂ ላለው ምን ጠፍቶ?

ኢትዮጵያ እንደዚህ ናት!

አመሻሹ ላይ፤ ወደ ግድቡ ከነንዋይና ከነአረጋኸኝ ጋር በመኪና ሄድን፡፡ ብዙ ሳንቸገር ለጥበቃዎቹ እነንዋይ እያስረዱ ግድቡ ፕሮግራም ደጃፍ አፍ ድረስ ገባን፡፡

ከአፋፉ ላይ ሆነው ግድቡን ማየት ትንፋሽ ያሳጥራል፡፡ (Breath - takingly - beautiful እንደሚሉት ፈረንጆቹ) የብሔር ብሔረሰብ የባህል ቡድኖች ከእግር ጉዞ በኋላ ደረሱ፡፡ (እኛ በመልካም መኪና ቀድመናቸዋል፤ ታድለናል!) ሲገቡ ይታዩናል፡፡ (ሁሌም ይሄ ትርዒት ያሳዝነኛል፡፡ አሁን እኛ ምን ቤት ነን? ዋናዎቹ?! እነሱ እያሉ የሚል ስሜት አለኝ)

መድረኩ በትልቁ ተገንብቷል (gloriously)፡፡ ከመድረኩ ጀርባ ታላቁን ግድብ የሚሰሩ በክሬንና በተለያዩ መሳሪያዎች ሌት ተቀን የሚታትሩ ትጉህ ባለሙያዎች ይታያሉ፡፡ በጣም ይማርካሉ። የመድረኩን ግርማ ሞገስ ለማድመቅ የበሩት ባውዛዎች አገር ምድሩን አፍክተውታል፡፡ ከአየር ላይ የተጠመደ ካሜራም ይታየኛል፡፡ የብሔር ብሔረሰቦች ባህል ቡድኖች ማህሉን ሜዳ በደማቅ ዳንስ ማጀብ የበለጠ ሽብረቃ ሆኖታል፡፡

ከመድረኩ በታች ማዶ የሚታዩት ታዳሚዎች (ክቡሮቹም ጭምር) ከሩቅ ይታዩናል፡፡ በመድረኩና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ሜዳ ላይ ነው ጨዋታው የደራው፡፡ መላ - ነገሩ፤ ንዋይና አረጋኸኝን ጨምሮ የተለያዩ ድምፃውያን፣ "የ8100-ሌ" ኮሜዲያንና፤ ገጣሚያን የተካፈሉበት ፕሮግራም ነበር፡፡ ሁለት የመድረክ አስተዋዋቂዎች አሉ፡፡ እኔ ከብዙ አርቲስቶች ጋር ከመድረኩ ጀርባ ነኝ፡፡ ከእኛ ጀርባ ደግሞ ሌት ተቀን ስራቸውን የሚያቀርቡት የግድብ ስራ ባለሙያዎች በሰማይ በክሬን ላይ፤ በመሬት በትናንሽ የሥራ መኪናዎች ወዲህ ወዲያ ሲሉ ነው የሚታየው፡፡

የግድቡ ጉድጓድ ዟ ብሎ አፉን ከፍቶ ተኝቷል። ያለጥርጥር ግዙፍ ግድብ ነው፡፡ በማታ እጅግ ደማቅ እጅግ ውብ ነው፡፡ ዐባይ ባንድኛው ወገን ሲንፎለፎል ይታያል! ለተወሰነ ደቂቃ መንፈሴን ሰቅዞ ይዞታል፡፡ ወዳጆቼን ሁሉ ኑ እዩት! አልኩ፡፡ ዐባይን ማሰብና፣ ቀርቦ ማየትና መንካት፣ ፈሊጡ ለየቅል ነው! ስለግድቡ ያለንን መንዲስ ምኞትና ሰፊ ምናብ ከጨመርንበት ልዩ ስሜት ይሰማናል! ከአፎቱ ተርፎ ሲፈስ 262 ኪ.ሜ ግድም (ከአዲስ አበባ እስከ ዝዋይ) እንደሚንሰራፋ ለሚያውቅ፤ ግዙፍነቱ ይህ ወሰንህ ይህ ዳካህ የማይሰኝ፣ እጅግ ሰፊ መሆኑን ለማየት አያዳግትም፡፡ እኛማ ገና ስንመጣ አውቀነዋል፡፡ ገና መንገድ ላይ ሳለን፤ ለምን ዛፉ ይመነጠራል? ስንል፤ "ዐባይ የት ይተኛ?" አሉን፡፡ "እንኳን መተኛ ማንኮራፊያም አለው!" ብለን ተሳሳቅን! አያ - አዎ ነው ነገሩ - paradox፡፡ ድህነትን ለማጥፋት ምንም ከማድረግ አንመለስም!

መድረኩ፤ ከታዳሚው መካከል ያሉ አርቲስቶች ጓደኞቻችን ደማቅ እይታ እንደነበር አጫውተውናል። በጭፈራው አቧራው ሲጨስ እኛም ከመድረክ ኋላ ሆነን ይታየናል፡፡ ለአርቲስት ጓደኞቻችን፤ እኛ ስለቀኑ የምሳ ረሃብ ስናወራላቸው ግን፤

"እናንተ ሰፊውን ህዝብ ትላላችሁ፡፡ እዚያ ከታደምነው መካከል፤ ካሉን ጥቂት ሴት ሚኒስትሮች ውስጥ አንዷ፤ እራት ፈልጉልኝ ብለው ብንፈልግ አጥተናል!" አሉኝ፡፡ "ገደደ!" አልን፤ የባሰ አታምጣ እንደማለት!

እኔ እስካየሁት ድረስ የብሔር ብሔረሰቦች ምግብ አለማግኘት አንጀቴ ውስጥ ገብቶ ስለነበር፤ የሚኒስትሮቹ አለማግኘት አላስገረመኝም፡፡ አላስጨነቀኝም፡፡ እንደፌዝ "የሚኒስትሮች ቀን ቢኖርና ዛሬ ቢሆንስ? ምን ሊሉ ነው!?" ብዬ ከጓደኞቼ ጋር ተሳስቀናል፡፡

በተለያዩ ባለስልጣናት ተገቢ ናቸው የተባሉ ንግግሮች ተካሄዱ፡፡ የመድረክ ምስቅልቅል መጠነኛ ችግር እዚህም ታይቷል፡፡ የዘፋኞች ዓይነተኛ ምሬትም አልጠፋም፡፡ እኔም ግጥሜን አላነበብኩም። በኋላ እንደተነገረኝ ከሱዳን የመጡ ሙዚቀኞች Last Minute ላይ መጥተው አጨናንቀውን ፕሮግራሞች ተዛብቶብን ነው ያሉት፡፡ ዞሮ ዞሮ ያው የ Disorganization አካል ነው፡፡ ፕሮግራሙን በአንክሮ አለማቀናጀት! ከዚህ ብዙም ተለይተን ስለማናውቅ ብዙ አልገረመኝም፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙዎች ሥራዎቻቸውን አልቀረቡም፡፡

ወደ መኝታችን አምሽተን ነው የሄድነው፡፡ የምሽቱን ፕሮግራም ለመወያየትም ጊዜም አቅምም አልነበረም፡፡ እንደተለመደው ነገ በጠዋት እንነሳለን ስለተባለ በጊዜ እንተኛ ብለን ወደ ማረፊያችን ሄድን!

* * *

በነጋታው አሶሳ ደርሰን ልዩ ልዩ ሲምፖዚየሞች ሲካሄዱ ውለዋል፡፡ እኔ ከዘነበ ዎላና ከጓደኛው ጋር በ1959 ዓ.ም ብርሃነ መስቀል ረዳ (ከኢህአፓ መሪዎች አንዱ) በአሶሳ ከተማ አቋቁሞታል ወደተባለው መጽሐፍት ቤት ለጉብኝት ልሄድ ጓጉቻለሁ፡፡ በስዩም ወልዴ ራምሴም የግለ - ታሪክ መጽሐፍ "ኩርፊያ የሸፈነው ፈገግታ" ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ አንብቤያለሁ፡-

"በ1959 ዓ.ም መጀመሪያ ወደ ባህር ዳር በኋላም ወደ አሰብ ተጉዣለሁ፡፡ የባህርዳሩን የፈለገ ሕይወት ሆስፒታል ጉብኝት አዘጋጅቶ "ጋዜጠኞችን" የጋበዘው አዲስ አበባ የሚገኘው የጀርመን ኤምባሲ ነው። ቡድኑ በብዙ አንቱ በተባሉ አንጋፋ "ጋዜጠኞች" የተሞላ ነበር፡፡ ከብስራተ - ወንጌል የሄድኩት እኔ ስሆን በዕድሜና በስራ ጀማሪነቴ ታናሽ እኔው ነበርኩ፡፡ ለዕድሜዬ ቀረብ የሚለኝ ያገኘሁት አንድ ሰው ብቻ ነበር፡፡ እርሱንም ዘጠነኛ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በተዘጋጀ "ካፒቴን ትስዊት" በተሰኘ ቴአትር ውስጥ ሲካፈል ያየሁት የዩኒቨርሲቲው አንደኛ ዓመት ተማሪ ነበር። ባንተዋወቅም በተዋናይነት ስላየሁት በቅርብ እንደማውቀው ሰው ተጠጋሁት። በጉዞአችን ወቅት በነበረው እንቅስቃሴ ሁሉ አንድ ላይ ስለታየን ባህር ዳርም እንደደረስን የሆቴል ድልድል ሲደረግ ከእርሱ ጋር አንድ ክፍል ተሰጠን፡፡ ለእኔ ከእርሱ ጋር መሆኑ አስደስቶኛል። ሌሎቹ ጋዜጠኞች ግን እርሱ አጠገብ መቆምም፣ መታየትም አይፈልጉም ነበር፡፡ "እናንተ ጎረምሶች ታዲያስ?" ይሉናል፡፡ በአውሮፕላን ደርሶ መልስ ውሎ አዳር በነበረው ጉዞ ሙሉ የሁለታችን ውይይት ከጉብኝቱ ጋር እምብዛም የተያያዘ አልነበረም፡፡ በሁለታችንም ዘንድ በጎ የመንፈስ መቀራረብ ይሰማ ነበር፡፡ ወጣቱ ጋዜጠኛ የሔራልድ ጋዜጣ ዘጋቢ ሲሆን ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነቱ ለተወሰነ ጊዜ በቅጣት ተገልሏል፡፡ ጋዜጠኞቹ የሚሸሹት

ውሃ ወደ ገፅ 12 ዞሯል



# “24 አመት ሙሉ የዲሞክራቲክ ተቋማት መጠናከር አልቻሉም”

## …ነ አንድነት ጉዳይ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ተችቷል

*ከምርጫ 97 በኋላ የተከሰተውን የፖለቲካ ቀውስ ተከትሎ “ሦስተኛ አማራጭ” በሚል የትግል ስልት ብቅ ያለው ኢዴፓ፤ በግንቦቱ አገራዊ ምርጫ ከሚወዳደሩ 60 ፓርቲዎች አንዱ ነው፡፡ የፓርቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጫኔ ከበደ፤ ከአዲስ አድማስ ጋዜጠኛ አለማየሁ አንበሴ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ዶ/ር ጫኔ ከበደ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በዴቨሎፕመንታል ኢኮኖሚክስ፣ ዶክትሬታቸውን ደግሞ በዴቨሎፕመንት ስተዲስ ያገኙ ሲሆን በአማካሪነት በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡*




ዶ/ር ጫኔ ከበደ

*በቅርቡ ምርጫ ቦርድ በአንድነትና በመኢአድ ላይ የወሰነው ውሣኔ “ከተፈቀደለት የህግ አግባብ ውጪ የፈፀመው ጣልቃ ገብነት ነው” የሚሉ ወገኖች አሉ፤ ኢዴፓ አቋሙ ምንድን ነው? ውሳኔውንስ እንዴት አየው?*

በእውነት የሆነው ነገር በጣም አሳዛኝ ነው፡፡ በሁለቱም በኩል ያለውን ክፍተት አይተናል፡፡ ምርጫ ቦርድ አጣብቂኝ ውስጥ የገባበት አሠራር ላይ ነው የደረሰው፡፡ ምርጫ ቦርዱ ህጉን መሠረት አድርጐ ያወጣቸውን ህጐች መከተል ያለበት፡፡ ከዚያም በላይ ህገ-መንግስቱ የሠጣቸውን መብት መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ እንዲህ አይነት ችግሮች ሲፈጠሩ የማስተካከል፣ እርምት የመውሰድ፣ የማሠልጠን ግዴታ አለበት - ቦርዱ፡፡ መጀመሪያ ላይ ቦርዱ፣ አንድነትና መኢአድ ሊዋሃዱ ሲሉ የአቶ አበባው መሃሪን አመራር አላውቅም ብሎ ነበር፡፡ የሁለቱ ውህደት እንዳይፈፀም የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚያ በኋላ አንድነት ውስጥ በተፈጠረው ችግር በእነ ኢ/ር ግዛቸው በኩል የነበረውን ሂደት ውስጣዊ መተዳደሪያ ደንባችሁን ተግባራዊ አላደረጋችሁም፣ እውቅና አልሠጣችሁም --- ብሎ ምን ያህል ሲያስቸግር እንደነበር ይታወቃል፡፡ በኋላም የእነ አቶ በላይ ቡድን ሲመጣ፣ ለእነሱም እውቅና ላለመስጠት ይሄኛው ህግ አልተከበረም፣ያኛው አልተከበረም ሲል ታዝበነዋል፡፡ ቦርዱ ሃላፊነቱን ለመወጣት ያኔ ነው መሸምገል የነበረበት፡፡

አሁን ለመኢአድ አቶ አበባውን አጽድቆ፣መኢአድን ማስቀጠል የሚለው በኛ በኩል አያስኬድም፤ ተቀባይነትም የለውም፤ የአንድነትም ቢሆን አንዱን ጥሎ ለሌላኛው ቡድን መስጠት ለአባላቶቹ ፌዝ ነው፡፡ ስለዚህ ቦርዱ መጀመሪያ በአግባቡ ሃላፊነቱን አልተወጣም፡፡ ይህ ባለመሆኑም ቦርዱ የወሰነው ውሣኔ ገለልተኝነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሆኖ ቁጭ አለ፡፡ የፓርቲዎቹን ስናይ ደግሞ ለአሉባልታና ለሌላ ነገር በራቸውን ክፍት አድርገው የሰጡት ራሳቸው ናቸው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ አወቃቀር ከድሮዎቹ ፓርቲዎች አስተሳሰብና ከኢሠፓ አመለካከት ያልተላቀቀ ነው፡፡ ከዚያም ባሻገር ኢህአዴግ ከሚከተለው ፅንፍ ያልተላቀቀ አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦች ፓርቲው ውስጥ ተሠግስገው በራቸውን ከፍተው ሰጡ፡፡ እድሉን ከፍተው የሠጡት ፓርቲዎቹ ራሣቸው ናቸው፡፡ መግቢያ በር የለም ቢሉ ኖሮ ማንም አይደፍራቸውም ነበር፡፡ የአንድ ግለሰብ አስተሳሰብ ተጽዕኖ እንደሚፈጥርም አልተገነዘቡም፡፡ ስለዚህ በምርጫ ቦርድ ብቻ ማሳበብ ሳይሆን እነሱም ሃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡

*የቦርዱ ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?*

ቦርዱ ችግሮች ሲፈጠሩ የመፍታት ሃላፊነት አለበት፡፡ ካግባባቸውና ካነጋገራቸው በኋላ የአብላጫውን ድምጽ ይዞ ውሣኔ መስጠት ይችላል፡፡ አሁን ችግሩ የተፈጠረው ያንን ባለመስራቱ ነው፡፡ እኛ እንጠብቀው የነበረው ቦርዱ ከወሰነው በተቃራኒ ነው፡፡ ሁለቱ ቡድኖች አንድ ሆነው ተጠናክረው እስኪመጡ ድረስ ጊዜ አራዝሞ እድል ይሰጣቸዋል ብለን ነበር፡፡ ምናልባት የሚያጡት ይሄን የምርጫ ጊዜ ይሆናል፡፡ ከዚያ ውጪ ግን ተግባብተው የሚመጡበትን እድል ይሰጣቸዋል ብለን ነበር የጠበቅነው፡፡ አሁን የወሰነው ውሣኔ ገለልተኝነቱንም ጥያቄ ውስጥ ያስገባው ከዚህ አንፃር ነው፡፡

*ኢዴፓ ቅንጅት ለመፍረሱ ምክንያት ነበር የሚሉ ወገኖች አሁንም ኢህአዴግን ለማሸነፍ ወይም ለመግራት የሚደረገውን ትግል ፓርቲው እያኮላሸው ነው እያሉ ይወቅሳሉ---*

ኢዴፓ ከምርጫ 97 በፊት በጣም ጠንካራ የነበረ ፓርቲ ነው፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ፅ/ቤቶችን ከፍቶ ብዙ አባላትን ያደራጀና አስተሳሰቡን ወደ ህብረተሰቡ እያሰረፀ የነበረ ፓርቲ ነው፡፡ ያንን መሰረት አድርጐ ቅንጅት በመፈጠሩ ምክንያት ያየነው ውጤት ተከተለ፡፡ ከዚያ በኋላ በነበረው ሂደት የተከሰተው የግለሰቦች አለመግባባት ግን ሁሉንም ፓርቲዎች አደጋ ላይ ጥሎ ነው ያለፈው፡፡ የግለሰቦች አለመግባባት ፓርቲዎችን አደጋ ላይ ሲጥል ህብረተሰቡንም አሳዝኖ አልፏል፡፡ ነገር ግን ፓርቲዎች እንደ ፓርቲ መቀጠል ስላለባቸው ኢዴፓም የራሱን ህልውና ለማስጠበቅ ከቅንጅት ተለይቶ የራሱን ስራ መስራት ጀመረ፡፡

እኔም በሂደቱ ስለነበርኩ መጀመሪያውኑ ውህደት እንዴት ይፈፀም የሚለው አለመግባባት ፈጥሮ ነበር፡፡ ያ ሁኔታ ፓርቲዎቹን እንዲበታተኑ ሲያደርጋቸው፣ ኢዴፓ ጠቅላላ ጉባኤውን ጠርቶ ሌላ ሥራ አስፈፃሚ መርጦ፣ አዲስ የማዕከላዊ ም/ቤት በማቋቋም እንደ አዲስ ስራው እንዲሠራ ተደርጓል፡፡ ከዚያ በኋላ “የቅንጅት መንፈስ የኔ ነው” እየተባባሉ እርስ በእርሣቸው ሲሻኮቱ፣ “ቅንጅት ከተወሰደብኝማ አንድነትን አቋቁማለሁ” ተባለ፡፡ “አንድነት” ተቋቋመ፡፡ “አንድነትም” መሃል ላይ “መርህ ይከበር” በሚል ለሁለት ተሰንጥቆ “ሠማያዊ ፓርቲ” ተፈጠረ፡፡ አሁንም እያየነው፣ አንድነት ለሁለት ተሠነጠቀ፡፡ መኢአድም ውስጣዊ ችግሩ አልፈታ ብሎ ሲንከባለል ቆይቶ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ ኢዴፓ ግን በተረጋጋ መንፈስ፣ ንቁ ተሣታፊ በሆኑ አባሎቹ፣ በቁርጠኛ የሠላማዊ ትግል መንፈስ፣ ዛሬ ሣይሆን ነገ ይደርሣል ብሎ ስለተነሣ ብቻ፣ ውስጠ ዲሞክራሲውን አጠናክሮ፣ አሁን ላይ ደርሷል፡፡

በፖለቲካ አሠራር የአንድም ግለሰብ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ይፈጥራል የሚል መርህ አለን፡፡ ስለዚህ ውስጠ ዲሞክራሲያችን መጠናከር አለበት የሚል እምነት አለን፡፡ በዚህ ምክንያት አሁን ያለው የኢዲፓ ስራ አስፈፃሚ ሣይሸረሸር፣ በፍላጐት በቁርጠኝነት፣ፓርቲውን ወደ አንድ ምዕራፍ ለማሸጋገር እየሠራ ነው ያለው፡፡

ከዚህ አንፃር ኢዴፓ በትግል ስልቱ ገዥው ፓርቲ እየተጠናከረ እንዲሄድ እድል እየከፈተ ነው የሚለው አያስኬድም፡፡ እንደውም እኛ መንግስትን ልንገዳደር እንደምንችል ብቻ ሣይሆን በሠላማዊ የስልጣን ሽግግር ተሣትፎ ለማድረግ የምንችል ብቃት ያለን ፓርቲ ነን ብለን ነው የምናስበው፡፡ በተቃራኒው ገዥው ፓርቲ ቆሞ እንዲሄድ እድል እየከፈቱ ያሉት አሁን እየፈራረሱ ያሉ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ በር ከፍተው እየሠጡ ሲፈራርሱ እያየን ነው፡፡ ይሄ ሁሉ የመጣው የትግል ስልታቸውን ባለመፈተሻቸውና ባለማስተካከላቸው ነው፡፡ መከባበር ባለማሣየታቸውና የግለሰብ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ያመጣል ብለው ባለማሰባቸው ነው፡፡ እኛ ቆም ብለን እየገመገምናቸው ነው የምንጓዘው፡፡ ስለዚህ ገዥው ፓርቲ ቆሞ እንዲሄድ እድል የሠጡት እነዚህ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ገዥው ፓርቲ የኛን አካሄድ የሚያከብረውን ያህል የኛን አሠራር በጥንቃቄ የሚያየው መሆኑን በእርግጠኝነት እናገራለሁ፡፡ ሂደቱ ጨኸት እየበዛበት የሚሄድ ከሆነ፣ ህብረተሰቡንም እያሳዘነ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ይወስደዋል፡፡

*የፓርቲው የአባላት ቁጥር ስንት ደረሰ?*

ሪፖርቱ ስላልተጠናከረ በቁጥር መግለጽ ባይቻልም በጣም በርካታ አባላት ናቸው ያሉት፡፡ አሁን ለምርጫ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ላይ እጩዎችን አስመዝግበናል፡፡ እስካሁን ድረስ (ቃለ ምልልሱ የተደረገው ረቡዕ ነው) ወደ 270 የሚደርሱ እጩዎችን አስመዝግበናል፡፡ እቅዳችን እስከ 450 ለማስመዝገብ ነው፡፡ እቅዳችንን አሁን በተጨመረው ጊዜ ውስጥ እናሣካለን፡፡

*ኢዴፓ “3ኛ አማራጭ” በሚል የጀመረው የትግል ስልት አዋጥቶታል ይላሉ?*

የሊበራል አስተሳሰብ የሚገዛን እንደመሆኑ፣ በምክንያት መደገፍ፣ በምክንያት መቃወም የሚለውን አቅጣጫ ነው የምንከተለው፡፡ ገዥው ፓርቲ ፈጽሟል የምንለውን ስህተት በምክንያት አስደግፈን እንቃወማለን፣ጥሩ ሠርቷል የምንለውንም እንደዚያው፡፡ ገዥው ፓርቲ ያልሠራባቸውንና ህዝብ እየበደለባቸው ያሉትን በመረጃ ላይ መሠረት አድርገን እንቃወማለን፡፡

*በምክንያት ከምትቃወሟቸውና ከምትደግፏቸው የገዥው ፓርቲ ተግባራት መካከል ቢጠቅሱልን?*

በምክንያት የምንቃወማቸው… ገዥው ፓርቲ መንግስት እንደመሆኑ መጠን የሚሠራቸው ስራዎች አሉ፡፡ ለምሣሌ የኢኮኖሚ ፖሊሲውን እንቃወማለን፡፡ ሊያሠራ የሚችል ፖሊሲ አይደለም፡፡ ስለዚህ መንግስት ፖሊሲውን ሊያሻሽል ይገባል ብለን እናስባለን፡፡ መንግስት ይሄን ማድረግ ካልቻለ ወደ ሊበራል ኢኮኖሚ ዘዴ በመግባት፣አጠቃላይ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ይሆናል እንላለን፡፡ መንግስት የፖሊሲ ሣይሆን የአፈፃፀም ችግር አለብኝ ነው የሚለው፤ 24 አመት ሙሉ የአፈፃፀም ችግር ሊኖር አይችልም፡፡ ሌሎችም የዲሞክራሲ ተቋማት በብቃትና በቴክኖሎጂ እየተደራጁ አይደለም፡፡ ክፍተት እየተፈጠረ ነው፡፡ በመንግስት የተዋቀሩ ቢሆንም ከገዥው ፓርቲ ነፃ እየሆኑና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረጉ አይደለም፡፡ ህብረተሰቡም በዚህ ምክንያት መብቱን ማስከበር አልቻለም፡፡ 24 አመት ሙሉ የዲሞክራቲክ ተቋማት መጠናከር አልቻሉም፡፡ በአጠቃላይ ቢሮክራሲው ችግር አለበት፡፡ ከዚያም ባሻገር ችግሩ ወደ ሙስና ሄዷል፡፡ እያንዳንዱ የመንግስት ስራ የሚሰራው በእጅ መንሻ ሆነ፤ ግልጽነት ጠፋ፣ አሠራሩም አልተዘረጋም፤ የፍትህ አካሉ በትክክል እየሠራ አይደለም፡፡ የፍ/ቤቶች ነፃነት ጥያቄ ላይ ነው ያለው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉትን እየተቃወምን፣ የፖሊሲ ለውጦች እንዲመጡ መታገል አለብን ብለን እናምናለን፡፡ ህብረተሰቡ ደግሞ በድምጽ እውቅና ከሰጠን፣ መንግስት ሆነን መፍትሔ እናመጣለን ብለን እናስባለን፡፡

በመረጃ ተንተርሰን የምንደግፋቸው ደግሞ አሉ፡፡ አሁን ያሉት የመንግስት መዋቅሮች ትክክል ናቸው፡፡ እኛም መንግስት ብንሆን ይሄን መዋቅር ነው የምንከተለው፡፡ እነዚህን ተቋማት በሰው ሃይልና በሎጅስቲክስ ማጠናከር ከተቻለ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ተቋማት እውቅና ሰጥተን እንጓዛለን፡፡ ነገር ግን የተቋማቱን ችግሮች ነቅሰን አውጥተን እንዲሻሻሉ እናሳስባለን፡፡ በዚህ ዙሪያ መንግስትን እንደግፋለን፡፡ በልማት እና በመሠረተ ልማት ዙሪያ የሚከናወኑ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እንደግፋለን፡፡ እኛም መንግስት ብንሆን የምናደርገው ነው፡፡ ውጤቱ ለህብረተሰቡ ይጠቅማል ብለን ስለምንገምት የአባይ ግድብ መሠራቱን፣ የመንገድ መሠረተ ልማቱን እንደግፋለን፡፡ ወረዳ ከወረዳ እየተገናኘ ነው፤ በአሁን ሰአት መንገድ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ዋስትና ነው፡፡ የባቡር ፕሮጀክቱ ከጅቡቲ አዲስ አበባ የሚገባው ትልቅ

ዲሞክራት ወደ ገፅ 21 ዞሯል



# ‘በሁለቱም ወገን የሚለበስ ጃኬት…’

ኤፍሬም እንዳለ

## እንጨዋወት

እንዴት ሰነበታችሁሳ!

ስሙኝማ...እንበልና ከሆነ የምታውቁት ሰው ጋር ከረጅም ጊዜ በኋላ ትገናኛላችሁ፡፡ እናማ... ገና ስታዩት እሱዬው የሆኑ... አለ አይደል...‘የሆኑ’ ለውጥ የሚመስሉ ነገሮች ታዩበታላችሁ፡፡ ገና ሲጨብጣችሁ... “ይሄ ሰውዬ በሦስት ጣቶቹ ብቻ መጨበጥ ጀመረ እንዴ!” ያሰኛችኋል፡፡ ልክ ነዋ... (አምስቱ ጣቶችማ ወይ ‘ፈራንካ’፣ ወይ ‘ወንበር’ ምናምን ለፈቀዱለት ነዋ!)

እናላችሁ...እሱዬው ነገርዬው ሁሉ ግራ፣ ግራ ነገር ይሆንባቸዋል፡፡ ቃላቱን እየቆጠበ... “ደህና ነህ?” ይላችኋል፡፡ የ“ደህና ነህ?” ቃናዋ...አለ አይደል...“እንደው ቺስታነቱን ችለኸው እስካሁን ቆየህ!” አይነት ነው፡፡ እናላችሁ... “... ድሮ ጋዜጣ ላይ ምናምን ትጽፍ ነበር!...” ይልና አንጠልጥሎ ይተወዋል፡፡ እናንተም የውሸት የ‘ዲፐሎማት’ የሚመስል ፈገግታ ታሳዩና... “አዎ...” ትሉታላችሁ፡፡ ያው ትንሽ ‘ስማርት ፎን’...ምናምን ነገር ብቅ፣ ጥልቅ ያደርግባችሁና በሰላምታ ትለያያላችሁ፡፡

ታዲያላችሁ...ያንኑ ሰው በአሥራ አምስተኛው ቀን ታገኙታላችሁ፡፡ የተለመዱትን ሰላምታ የሚመስሉ ነገሮችን ትለዋወጡና ምን ይል መሰላችሁ... “ሁልጊዜ ጽሁፍህን አነባለሁ...” በእሱ ቤት ‘ጮካ’ መሆኑ ነው! ዘንድሮ መቼም የማናየው ‘ጉድ፣ የጉድ ጉድ’ የለም አይደል... በሁለት በኩል እየተገለበጠ እንደሚለበስ ጃኬት አንዴ ያወራነውን የሚቀጥለው ጊዜ ገልብጠን የምናወራ የበዛን አይመስላችሁም! ለምን መሰላችሁ...ዘመናዊ ለመምሰል! ቂ...ቂ...ቂ... አሪፍ ድራማ ጸሀፊ... “ድንቄም ዘመናዊ ተሆነ!” የምትል ገጸ ባህሪይ ያለችበት ድራማ ይጻፍልንማ!

እኔ የምለው... አንዳንድ ወዳጆቼ ....ስማ “አሁንም ትጽፋለህ!” የምትሉኝ... እና ጦሜን ልደርላችሁ! ወይስ ‘ሙያ’ ለውጬ “አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ...” ልሁን! ቂ...ቂ...ቂ...

ስሙኝማ...እንግዲህ ጨዋታን ጨዋታ ያነሳው የለ...አለ አይደል...ገና ሲ.ፒ.ኤ. ምናምን ደረጃ ውስጥ ያልገቡ መአት ሙያዎች የተፈጠሩ ይመስለኛል፡፡

ደግሞ አለላችሁ... እንዲሁ እንደ እኔ በ‘ራጂ’ እንኳን የማትታይ ደረቱን እያሳበጠ... ድምጹን ‘ነጎድጓዳማ’ ለማድረግ እየሞከረ... “ይገርምሀል፣ የዚህ አገር ጋዜጦች ስለማይጥሙኝ ማንበብ ካቆምኩ ብዙ ጊዜ ነው፡፡ በቃ...ያለ ጭቅጭቅ ምንም የለባቸውም፡፡...ምን እንደሚሉም አይገባኝም ...” ምናምን ይላል፡፡ በተዘዋዋሪ እኮ... “ከአንተ ጀምሮ ምን እንደምትሉ አትገቡኝም...” ማለቱ ነው፡፡

እግረ መንገዴን... “አማርኛ መጽሐፍ አላነብም...” የሚሉ ሰዎች ገጥመዋችሁ አያውቅም! ለእነሱ አማርኛ መጽሐፍ ማንበብ... አለ አይደል... ‘ቅሽምና’ ምናምን ይመስላቸዋል፡፡ የምር ግን... ወደፊት ልናደርገውም፣ ላናደርገውም በምንችለው ‘የዳሰሳ ጥናት’ የሚደረስበትን ውጤት በቅድሚያ እነግራችኋለሁ...“አማርኛ መጽሐፍ አላነብም...” ከሚሉት ሰዎች አብዛኞቹ ከምግብ ሜኑ ባለፈ ሌላ ነገር አያነቡም፡፡ አሀ...ምልክቶች ስናይስ!

ታዲያላችሁ...ያ “የዚህ አገር ጋዜጦች ስለማይጥሙኝ ማንበብ ካቆምኩ ብዙ ጊዜ ነው...” ያለውን ሰው በሆነ ቅዳሜ ቀን ምናምን ወይ አራት ኪሎ ወይ የሆነ ቦታ አንድ ካፌ ቁጭ ብሎ ፊት ለፊቱ አምስት ጋዜጦችና አራት መጽሔቶች ደርድሮ ሲያገላብጥ ታዩታላችሁ፡፡ በቃ...የሆነ ቀሺም ነገር አይደለም! ሁለት ጋዜጣ በሚገዛበት ፍራንክ ስምንት ጋዜጣና አምስት መጽሔት ሲያገላብጥ እየዋለ...“የዚህ አገር ጋዜጣ አላነብም... ቅብጥርስዮ ምን አመጣው!

እናላችሁ... እንደዚህ ያልሆነውን ነገር በአደባባይ ለመምሰል የምንጥር በዝተናል፡፡ ህዝቤ ሰልፍ ኮንፊደንሱን ሁሉ በወለድ አግድ አስያዘው ማለት ነው! ያሰኛላ... በዚህ የሁላችን ዓይኖችና ጆሮዎች በሥራ በተጠመዱበት ዘመን... “አጎቴ በሄሊኮፕተር ሲያልፍ እንዳያያኝ...” አይነት እንደ ባቡሩ መቶ ዓመት የሞላው አራድነት አይሠራም፡፡ (‘ያኛውን ባቡር’ ማለቴ ነው፡፡ አሀ... ግልጥና ግልጥ መሆን አለበታ!)

ደግሞላችሁ የእኔ ቢጤዎች አለን... “ድራፍት! ደግሞ ድራፍት ልጠጣ!” ምናምን የምንል፡፡

“ድራፍት ብትጠጣ ምን አለበት!”

“ስማ እኔ ገና ሳየው ምን እንደሚመስለኝ ታውቃለህ...ገና ተጣርቶ ያላላቀ ዘይት ነገር፡ ሞቼ ነው ቆሜ ድራፍት የምጠጣው!

እናላችሁ... በሆነ አጋጣሚ እግር ጥሏችሁ በሆነ አካባቢ ስታልፉ... የሆነች ‘አይቅርብኝ፣ እኔስ ከማን አንሼ!’ ቀበሌ ከበብ በረንዳ ላይ እንደ ስዊስ በረዶ መንሸራተቻዎች ያጋደለች አግዳሚ ወንበር ላይ ‘ተጣብቆ’ ድራፍቷን በሁለት እጁ ጨብጦ ታገኛላችሁ፡፡ ፒያሳ ላይ ቢሸውዱ...ጀሞ ላይ ገልጦ የሚያይ አይጠፋም፡፡

ቂ...ቂ...ቂ... እኔ የምለው...ገና እኮ ችስት ያለች አገር ውስጥ ነን ያለነው! ልጄ ድራፍቱስ ተገኝቶ ነው! ልክ ነዋ...ሹሮ ሰማንያና ዘጠና ብር ስትገባ... ሆዳችን ውስጥ ያለውን ‘ክፍት መሬት’ በምን እንሙላው!

እንግዲህ ጨዋታን ጨዋታ ያነሳው የለ...የሹሮ ነገር ከተነሳ ይቺን ስሙኝማ... ባለፈው ዓመት ጾም ጊዜ ከአንድ ወዳጄ ጋር ተጋሚኖአችንን ልንበላ የሆነች ቤት ገባን፡፡ እስከዛ ድረስ ‘የተቀለመ ሹሮ’ አይቼ አላውቅም ነበር፡፡ እናላችሁ...ተጋሚኖ የተባለው ነገር ቀረበ፡፡

የምር...በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሹሮ መልክ ያለው እንጀራና ግራጫ መልክ ያለው ሹሮ ወጥ ያየሁት ያኔ ነው። ድራፍቱ እንኳን ተጣርቶ ያላለቀ ዘይት መሰለ፡፡ ቂ...ቂ...ቂ...

እንትናዎች...ስሙኝማ... ዊግ የምታደርግ እንትናችሁን ‘ቴምፕሬቸር’ ለመጨመር ስትፈልጉ ‘ጸጉሯ’ን ሰላም ስጡትማ፡፡ (የ‘ሲክስ ታውዘንድ’ ረብጣ ዕቃ የምን ማጨማደድ ነው! ቂ...ቂ...ቂ...) እናላችሁ... የእናንተ የደም ስርጭት እየጨመረ ሲሄድና መዳበሱ ጠንከር ሲል እሷዬዋ ልትሳቀቅ ትችላላቻ! “ወይኔ ጉዴ! ምን ያንቀዠቅዣዋል! ስንትና ስንት ዓቢይ ጣቢያ እያለለት ጸጉሬን ነቅሎ ሊጥልብኝ ነው እንዴ!” (‘ዓቢይ ጣቢያ’ ተመችታኛለች፡፡)

ሀሳብ አለን... ዊግ የምታደርጉ እንትናዬዎች ቦርሳችሁ ውስጥ “ለሚመለከተው ሁሉ...” በሚል ርዕስ ‘የተግባር መመሪያ’ ምናምን የምትል ብጣሽ ወረቀት መያዝ አትርሱማ! ከሥሩ ‘አክሴፕት’ ‘ሪጀክት’ የሚሉ ሁለት ሳጥኖች ማስቀመጥ ነው። ልክ ነዋ... አንጀታችሁን አስራችሁ የገዛችሁትን ‘የአደባባይ መዋቢያችሁን’... አለ አይደል... “ነቀለብኝ...” “አወረዛብኝ...” (ቃሉን ካወቃችሁት ለማለት ነው...) ምናምን ብሎ ከመሳቀቅ...ከአንገት በላይ የሚደረግ ዳበሳ...ከአሥራ አምስት ሴከንድ በላይ መቆየት የለበትም፡፡ አሀ...አሥራ አምስት ደቂቃ ብዙ ነዋ! (‘ደመ ቀዝቃዛው’ እንትና...አሥራ አምስት ሰዓት ይበቃሀል?” በአንድ ወቅት አንዲት ‘ግልጥ’ የሆነች ወዳጃችን በወቅቱ ስለነበረው እንትናዋ ምን አለችን መሰላችሁ...“ሳሙና ቀብቶኝ እሱን የሚፈትግልኝ ነው የሚመስለው!” ቂ...ቂ...ቂ... ለዚህስ አንድ ቁና የአጃ እህል መስጠት ነበር!

ስሙኝማ...ሌላ ሀሳብ አለን፡፡ ሁኔታዎች እስኪጣሩ... “ዞማ ጸጉርሽ ልቤን ምናምን አድርጎት...” አይነት ግጥሞች ላይ ማዕቀብ ይጣልልን፡፡ የምር ግን...ይሄኔ ግን ስንት ዕድለኛ ‘ዊግ’... “ጸጉሯ ዘንፈል ብሎ ትከሻዋ ላይ...” ምናምን ተብሎ ተዘፍኖለት ይሆናል!

ስሙኝማ...ይሄ ቫለንታይን ምናምን የሚሉት ቀን ደረሰ አይደል... አገር ‘ሊቀላ’ ነዋ! ገና ከአሁኑ ‘ቢዙ’ እየሞቀ ነዋ!

ይቺን ስሙኝማ...እሱዬው ብልጥ ነበር። እናማ... እሷዬዋን ምን ይላታል...“እንዲች አድርጌ ሳልነካሽ ልስምሽ እችላለሁ፡ በአሥር ብር እንወራረድ፡፡”

“ሳትነካኝ ልትስመኝ አትችልም፣ እንወራራድ።”

ከዚያም ደጋግሞ ይስማታል፡፡ “ይኸው ስትስመኝ ነካኸኝ አይደል፣ ተሸንፈሀል... አለችው። እሱዬው አሥር ብሩን አውጥቶ ምን ቢል ጥሩ ነው... “በውርርድ መሸነፍ አዲስ ነገር አይደለም...” ብሎ ቀዩዋን ብር ሰጣታ፡፡ ለ‘ቫለንታይን ቀን አክባሪዎች’... ይቺ ዘዴ የኮፒራይት ጥያቄ የለባትም።

የመሳም ነገር ካነሳን...ይቺን እንጨምርማ...

“ትናንት ግብዣ ላይ አንዱ ልሳምሽ አይለኝ መሰለሽ!”

“ሰው ባለበት ግብዣ ላይ! የሆነ ጥሬ ነገር መሆን አለበት፡፡”

“ኧረ ጥሬ አይገልጸውም...”

“አታጮይውም ነበር!”

“ስሞኝ እንዳበቃማ አጮልኩት፡፡”

አሁንም ለ‘ቫለንታይን ቀን አክባሪዎች’... ከጥፊውና ከኪሶሎጂው ማን ሚዛን እንደሚደፋ ማስላት ነው፡፡

እናማ...በሁለቱም ወገን እንደሚለበስ ጃኬት ወሬያችንን የምንገለባብጥ... ከ‘ግልበጣ’ ያድነንማ ቂ...ቂ...ቂ...

ደህና ሰንብቱልኝማ!

## በጥሩ የሥራ አፈጻጸም የሚወደሰው ግን በገሃድ የሌለው ቤተ መጻሕፍት

ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ አስተዳደር የተገኘሁት በጠዋት ነበር፡፡ ጉዳዬም በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሥር ያለውን በጥሩ የሥራ አፈጻጸም የተወደሰውን የወረዳ አንድን የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ማግኘት ነበር፡፡ ጠየቅኩ፤ ሦስት አራት የሚሆኑ የወረዳ ሰዎችን ጠየቅኩ፤ ከጥበቃ እስከ ቢሮ ሠራተኛ፡፡ ነገር ግን የቤተ መጻሕፍቱን መገኛ የሚያውቀው አንድም አልተገኘም፡፡

‹‹እዚህ ወረዳ ውስጥ ቤተ መጻሕፍት አለ እንዴ! እንጃ!›› የሚለው ይበዛል፡፡

የዛሬ ሰባት ወር አካባቢ የጎበኘሁት በአራዳ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ አንድ ቤተ መጻሕፍት ነበር፡፡ በቅርቡ ታዲያ በቤተ መጻሕፍቱ ደጃፍ ሳልፍ የምርጫ ካርድ መስጫ ጣቢያ ሆኖ አግኝቼው ነበር፡፡ ‹‹ይህም ቤተ መጻሕፍት የምርጫ ጣቢያ ሆኖ ይሆን?›› ራሴን የጠየቅኩት ጥያቄ ነበር፡፡

‹‹ቢሆንስ ታዲያ በአካባቢው ነዋሪዎች መታወቅ አልነበረበትም!?›› ለራሴ ጥያቄ መልስ ሰጠሁ፡፡

‹‹እሺ የወጣት ማዕከሉን ልታሳዩኝ ትችላላችሁ?›› ሲጨንቀኝ ያቀረብኩት ጥያቄ ነበር፡፡

አንድ የተባረከ ሰው የወጣት ማዕከሉን ወስዶ አሳየኝ፡፡ ህንፃው አዲስ ነው፡፡ ገና በአግባቡ ሥራውን የጀመረ አይመስልም፡፡ ለማንኛውም ሥራ አስኪያጁን አግኝቼ ማነጋገር ነበረብኝና ግቢው ውስጥ ያገኘኋቸውን ሁለት ወጣት ሴቶች ጠየቅኩ፡፡ ‹‹ወደ ሁለተኛ ፎቅ ውጣ!›› ተባልኩ፡፡ ወጣሁ፡፡ ወደ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ፡፡ አገኘሁት፡፡ ሠላምታ ተለዋወጥን፡፡ ከየት እንደመጣሁ ነገርኩት፡፡ ለምን እንደመጣሁም ጭምር፡፡

‹‹ቤተ መጻሕፍታችሁን ለመጎብኘት ፈልጌ ነበር!›› ስለው ፈገግ አለ፡፡

‹‹ምነው?›› አልኩት፡፡ ህንፃው ከተመረቀ ገና አንድ ወር እንደሆነው ነገረኝ፡፡

‹‹እናስ?››

‹‹ለጊዜው ቤተ መጻሕፍት የመክፈት እቅድ እንጂ ቤተ መጻሕፍት የለንም! ለቤተ መጻሕፍት የሚሆነው ክፍል ግን ተዘጋጅቷል፡፡ ሦስት ባዶ የመጻሕፍት መደርደሪያዎች አሉን፡፡›› አለኝና ቀጠለ ወጣቱ፤ ‹‹ህንፃው ብዙ ነገሮች ገና አልተሟሉለትም፡፡ መብራት የለውም፤ ውሃም ገና አልገባለትም፡፡ የቢሮ እቃዎችም ገና አልተሟሉም፡፡ ከሁሉም በፊት ግን መብራት ቢገባልን ያሰብነውን ለመሥራት ደፋ ቀና እንል ነበር፡፡ ክፍለ ከተማም ሆነ መብራት ኃይል እየተመላለስን እየጠየቅን ነው፡፡ አፋጣኝ መልስ ግን ልናገኝ አልቻልንም!››

‹‹ታዲያ በልደታ ክፍለ ከተማ የወረዳ አንድ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት የት ነው ያለው?››

‹‹አንድ ቤተ መጻሕፍት ነበር!›› አለ ሥራ አስኪያጁ እንደማሰብ ብሎ፤ ‹‹ከተዘጋ ግን ቆይቷል!››

‹‹የት ነው ያለው?››

ነገረኝ፡፡ ከልደታ ፍርድ ቤት ወደ ብሥራተ ገብርኤል የሚወስደውን ቁልቁለታማ መንገድ ይዘው ጥቂት እንደተጓዙ ድልድዩ ጋር ሳይደርሱ በቀኝ በኩል ጀርባውን ለአውራ መንገዱ የሰጠ አረንጓዴ ቤት ነው፡፡ እንደተባልኩት አገኘሁትና የቆርቆሮ በሯን ከፈት አድርጌ ገባሁ፡፡

‹‹አቤት!›› አለኝ አንድ ድምፁ ወፈር ያለ ወጣት፡፡

‹‹ቤተ መጻሕፍት ፈልጌ ነበር፡፡››

‹‹የሉም!›› ቆጣ ባለ ድምፅ፡፡

‹‹የት ሄዱ?››

‹‹መጥተው አያውቁም!››

‹‹ከመቼ ጀምሮ?››

‹‹ምንድን ነህ አንተ? አለቃቸው ነህ?›› ከሚያስፈራ መኮሳተር ጋር፡፡

‹‹አይ አይደለሁም፤ ቤተ መጻሕፍቱን ለመጎብኘት ፈልጌ ነው፡፡›› እየተሽቆጠቆጥኩ፡፡

‹‹መጽሐፉን እዛ ቤት ዘግተውበታል›› አለኝ አንዲት አነስተኛ ሰርቪስ ቤት እያሳየኝ፤ ‹‹አዳራሹን ግን ወጣቶች የራሳቸውን መጽሐፍ ይዘው እየመጡ ያነቡበታል!››

ግራ ተጋባሁ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ጥሩ የሥራ አፈፃፀም አሳይተዋል ተብለው ከተሰጡኝ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ይሄ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ከተዘጋ ሁለት ወር አልፎታል፤ ከሁለት ወር በፊትም ቢሆን ከሚከፈትበት የሚዘጋበት ጊዜ ብዙ እንደሆነ የአካባቢው ወጣቶች ነግረውኛል፡፡ ታዲያ መልካም የሥራ አፈፃፀሙን ከየት አመጡት? ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

በባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሥር ያሉ አብያተ መጻሕፍት አያያዝ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ቤተ መጻሕፍቱን በመረጃ ሐብት አበልፅገው፣ በሥርዓት አደራጅተው፣ የንባብ ከበባትን አዋቅረው የሃያ አራት ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ እንዳሉ ሁሉ፤ በራቸውን በመጋዘን ቁልፍ አሽገው የሚጠፉ፣ ደመወዝ የሚበሉበትን ሥራቸውን የሚረሱ፣ የሥራ ሪፖርታቸውን እቤታቸው ቁጭ ብለው የሚጽፉ አሉና ክትትል እና ቁጥጥር ቢያደርግ መልካም ነው እንላለን፡፡ (ይህን ሐሳብ ከዚህ በፊትም ማንሳታችንን ልብ ይሏል፡፡)

የጀርመን ባህል ተቋም ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የቀረበ


## በድጋሚ የተጠራ ስብሰባ

አልዋኖ አጠቃላይ እንጨት ስራ አ/ማ ጠቅላላ ጉባኤውን እሁድ የካቲት 08 ቀን 2007 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ስለመያካሂድ ሁሉም የአልዋኖ አ/ማ አባላት እንዲገኙ ሲል የአስተዳደር ቦርዱ በአክብሮት ጥሪውን እያስተላለፈ በተገኙ የአ/ማ አባላት የዕለቱን አጀንዳ ያፀድቃል፡፡

የመሰብሰቢያ ቦታ በማህበሩ አዳራሽ

# የግዕዝ ፊደልና ቋንቋችን የማንነት ታሪካዊ ቅርሳችን

ግፍታሔ ገኃተ

ባለፈው ሳምንት ጽሑፌ ስለ ቋንቋ በመጠኑ እንዲሁም የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ለካም የተሰጠ ጥንታዊና መሠረታዊ ሃብታችን እንጂ ሴማውያን ለአፍሪካ ማለትም ለኢትዮጵያ የሰጡት እንዳልሆነ በአጭሩ ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ ይህም ሀሳቤ ምሑራኑ በስፋት ተመራምረውበት ፈር የሚያሲዝና ከዘርፉ ጋር ያለንን ታሪካዊ ቁርኝት የሚያሳይ የጥናት ውጤት እንደሚያቀርቡልን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በዓለማችን ላይ በርካታ ቋንቋዎች አሉ፡፡ በአገራችን እንኳን ከ80 በላይ ናቸው፡፡ ፊደል ደግሞ የጥቂት አገሮች ሀብት ነው፡፡ እዚህ ላይ ሊሠመርበት የሚገባው ጉዳይ እጅግ በርካታ ቋንቋዎች ለጽሑፍ ተግባራቸው ከነዚህ ባለፊደላት አገሮች ፊደልን እንደሚወስዱ ነው፡፡ እንግሊዝኛ ከላቲን ቋንቋ ፊደሎችን እንደወሰደው ማለት ነው፡፡

ከቋንቋ አኳያ ነገሮች በጥልቀት ከታዩ ለአንድ ቋንቋ ማንኛውንም ተስማሚ ፊደል እንዳለ ወይም መጠነኛ ማሻሻል በማድረግ መውሰድ ነውር አይደለም፡፡ አማርኛም ከግዕዝ የወሰደውን ፊደል በሚገባ ተጠቅሞበታል፡፡ ከዚህ አኳያ የብዙ አፍሪካ አገራት ልሒቃን የግዕዝን ፊደል ባለማወቃቸው አፍሪካዊውን ትተው የአውሮፓ ፊደል መዋሳቸው ይቆጫቸዋል፡፡ ነገሩን ከቅኝ ግዛት ጋር ሲያዛምዱት ደግሞ የባሰ ይንገበገባሉ፡፡

ግዕዝ የኢትዮጵያ ታላቅ የታሪክ ቅርስ ከመሆኑ ባሻገር የአገሪቱ የማንነት ምስጢራት ተመዝግበው የሚገኙባቸው ጥንታዊ መጻሕፍትና ጽሑፎች በዚሁ ቋንቋ በመሆኑ ታሪክ ለመደምሰስ ሕዝቡን ከመሠረታዊ ቋንቋው የመነጠል ተግባር እንደተከናወነ ማየት አይከብድም፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ የተጀመረበትንና ግዕዝ ወደ ገዳማትና አድባራት እንዲመንን የተፈረደበትን ታሪካዊ ወቅት (ጊዜ) በአግባቡ ማጥናት ምስጢሩን ገሐድ ማውጣት ነው፡፡ እንደሚመስለኝ "የዓባይ ወንዝ ምንጭን ለመቆጣጠር" ከፍተኛ ፍላጐት የነበራቸው ወገኖች በተለይ "ሃይማኖትን" ተገን በማድረግ የፈጸሙት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ ከዋናውና ከመሠረታዊ ቋንቋው በመነጠሉ በአገሩ ውስጥ የሚካሄዱ ተግባራትን ለሌሎች (ለአዋቂዎች) አሳልፎ መስጠቱ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በሁሉም የሰው ልጅ የሥራ እንቅስቃሴ ዘርፎች፣ በሥነ - ከዋክብት፣ በሳይንስ፣ በፍልስፍናና በዓለም ሕዝቦች ፊት በሚቀርብ የማንነት ጉዳይ በግዕዙ ተጽፈው የነበሩ ሀብቶች ቀስ በቀስ ተዘረፉ ማለት ነው፡፡ በግዕዝ መጻሕፍት ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያውያን ባሕረ ዕውቀት፣ ምልአተ ጥበባትና የታሪክ ትውፊቶች ከዐይኑ ሥር ሲመዘበሩ ሕዝቡ "የቄስ ቋንቋ" ከሚለው ግዕዝ ጋር ስለተፋታ እንደዋዛ አለፈው፡፡ እናም የኢትዮጵያን ክብርና ልዕልና ለማኮሰስ የፈለጉ ወገኖች በረጅም ጊዜ ሂደት እንደተሳካላቸው ማየት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያን ጥንታዊ ኃያልነትን /በዕውቀት ላይ የተመሠረተ/ ዝቅ በማድረግ በአካባቢው ኮስሳ እንድትታይና እነርሱ የልባቸውን ያደርሱ ዘንድ በፊደልና በቋንቋችን ዘርፍ (አእምሮአዊና ልባዊ ትውፊቶች) በሦስት ዋና ዋና መንገዶች መጉዳት ችለዋል፡፡ የመጀመሪያው መንገድ አስረስ የኔ ሰው እንደሚገልፁት፤ የተዛባ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለአገራችን ማውረስ (መስጠት) ነው፡፡ በካም መታሰቢያ መጽሐፋቸው ላይ (ገጽ 57) "...አይሁድ ይህን የተቀደሰ መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስን) ለዓለም ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሲሰጡ ረቂቅ ምክር ጨምረው ነው፡፡ ምክሩም "ሌላ መጽሐፍ ያገኛችሁ እንደሆን እንዳትቀበሉ" የሚል ነው፡፡ የዓለም ቤ/ክርስቲያናት ይህ ተንኮል መሆኑን ሳያውቁ ተሸክመውት ይኖራሉ፡፡ ...አይሁድ ሌላ መጽሐፍ እንዳትቀበሉ ማለታቸው መጽሐፍተ ብሉያት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ስላወቁ ነው፡፡" የሚል ሠፍሯል፡፡ ይህን ቃል የጠቀስኩት ትልቅ እንደሆነ ያመንኩበትን ምስጢር ለመግለጽ ፈልጌ ነው፡፡

ሁሉም የግዕዝ ሆሄያት ወይም ፊደላት የራሳቸው የቁጥር ቀመር አላቸው፡፡ በቁጥሩ ቀመር መሠረት ያለፈ፣ የዛሬውና የወደፊቱ በዓለም ላይ በየትኛውም ሥፍራ /ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅ/ የሚከወኑ ጉዳዮች በጊዜያት ማለትም ከሰከንድ እስከ ዘመናት ባሉት ተቀንብበው ይታወቃሉ፡፡ ይህ ረቂቅ ምስጢራዊ ጥበብ ደግሞ በኢትዮጵያውያን ጥንታዊ ቤ/ክርስቲያን የግዕዝ ሊቃውንት በመጽሐፍ ተዘጋጅቷል፡፡ ኢትዮጵያ ከሙሴም ጋር ቅርርብና ዝምድና ስለነበራትም ሙሴ በጻፈው ኦሪት ላይ በአግባቡ ተመዝግባለች፡፡ ሥነ - ልሳኗም ጭምር፡፡ በነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የታሪኩን የበላይነት ቀምቶ የራሳቸው ለማድረግ የተጠቀሙበት አንዱ መንገድ እንደ መጽሐፈ ሄኖክ፣ ሙሴ የጻፈው ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ ጦቢያ፣ መጽሐፈ ዮዲት ወዘተ. ያሉትና ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳይካተቱና የኢትዮጵያውያን ምልአተ ጥበብ እንዳይገለጥባቸው ማድረግ እንደሆነ አስረስ በማስረጃ ተንትነው ገልፀውታል፡፡ የተከለከሉት መጻሕፍት ደግሞ ታላላቅ ምስጢራትን ያጨቁ ናቸው፡፡

ሁለተኛው ታሪክን የመዘርጠጫና የራሳቸውን ታላቅነት ለማመቻቸት የጠቀማቸው ኢትዮጵያውያን ከመሠረታዊው ከአባታቸው ከካም በመውረስ የማንነታቸውን ታሪክ የገነቡበትን ግዕዝን በአማርኛ መተካት ይመስለኛል፡፡ የዚህን ዋነኛ ጭብጥ ከላይ ገልጨዋለሁ፡፡ ሦስተኛው መንገድ ሃይማኖትን አሳቦ በወዳጅነትና በሥልጣን ትልቁን የሹመትና የቅድስና መድረክ በመረከብ መጽሐፍቱን መዝረፍና ታሪኩንም የራስ ማድረግ ነው፡፡

ከላይ የዘረዘርኳቸው ብሉያት መጻሕፍት ያዘሏቸው ምስጢራትን ለማወቅ ግዕዝን ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ ብዙዎቹ ምስጢራት የያዟቸው አበይት ቀመሮች ጽንፈ ዓለሙን (Universe) በአጠቃላይ ይመለከታሉ፡፡ እዚህ ላይ የግዕዝ ፊደላት እያንዳንዳቸው በቁጥር መለያ (Code) የተሰጣቸውና የጽፈት ዓለሙን ኩነቶች ሁሉ በቀመር እንዲታወቅ ማድረጋቸው ብቻ አይደለም ምስጢራቱ፡፡ የፊደላቱ ሆሄያት እያንዳንዳቸው በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ አንድን ነገር እንደሚወክሉ ከትውፊት ወይም ከልቦና መንጭተው እስከ ዘመናችን የዘለቁ ነገሮች አሉ፡፡ ይህ እጅግ ጥልቅና ምጡቅ የሆነ የፊደላት ሚና እስካሁን ምንም ዓይነት ምርምር የተደረገበት አይመስለኝም፡፡ ጉዳዩ ግን እንዲህ በቸልታና በቀላሉ ታይቶ የሚታለፍ አይደለም፡፡

በዚህ በኩል የግዕዙ ልሒቃን ምርምሩን አጠንክረው ቢይዙት የግዕዝ አኃዞችም ደረጃና ምስጢራት በአግባቡ ይታወቁ ዘንድ እግረ መንገዱን ይረዳል የሚል ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡ **መዝገበ አኃዝ ዘኢትዮጵያን** (ገጽ 73) የጻፉት መሪጌታ በፈቃዱ፤ "ይህ አኃዝ የቤ/ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሀብት ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሀገሩን አኃዝ ማወቅ ይገባዋል፡፡" ሲሉ ያሳሰቡትም ከጠቀስኩት አቢይ ሃሳብ ጋር የሚሄድ ነው፡፡ በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ ያላቸው ውክልና መጠናት እንዳለበት ያሳሰብኩት ጉዳዩ ፊደሉ ይቀነስ ወይስ እንዳለ ይቀጥል? የሚለውን የክርክር ሃሳብ ስለሚፈታም ጭምር ነው፡፡ ለመሆኑ ፊደላቱ በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ ምንን ይወክላሉ? ለሚለው ጥያቄ አጭር ምሳሌያዊ መልስ ይሆን እንደሆነ በማሰብ በጥቂቱ ልዘርዝር። በእኔ ያልታወቀው ጉዳይ የትኛው ሆሄ የምን ውክልና አለው? የሚለው ነው፡፡ በተረፈማ ፊደላቱ ለመዘርዘር የሚያታክቱትን ሁሉ ይወክላሉ ይባላል።

**በምድር** - ምድርንና በላይዋ ያሉትን ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን፣ መናፍስትንም ጭምር። ሰውንና አራቱ የሥጋና ሦስቱን የነፍስ ባሕሪያቱን

**በአየር** - ነፋሳትን፣ ውሃዎችን፣ ሌሎች ረቂቆችን፣ ብርሃናትን

**በሰማያት** - ሰባቱ መሳክዎ ሰማያትን፣ 24ቱን ካሕናተ ሰማያትን፣ ከዋክብትን (ሚልክዌ፣ ጋላክሲ ወዘተ) የትየለሌ (Infinitive) የሚባሉትን፤ አምላክን፣ መላዕክታትን...፣ ፕላኔቶችን፣ ጨረቃዎችን፣ ሌሎች ዓለማትን-- ወዘተ፡፡

ለምሳሌ ከሰው የሥጋ ባሕርያት አንዱ እሳት ነው፡፡ እሳት ደግሞ ብዙ ዓይነት ነው፡፡ ስንጉረ፣ ሰናስለ እና መሐፒለ እሳት የሚባሉት እያንዳንዳቸው 5 ሚሊዮን እሳቶች ሲኖራቸው፣ ሦስቱ 15 ሚሊዮን እሳቶች አሏቸው ማለት ነው፡፡ ውሃዎች፣ ነፋሳት፣ መናፍስት እንደ ከዋክብቱ ሁሉ የትየለሌ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ ፊደሎቻችን እነዚህን ሁሉ ወክለው እንደተቀመጡ ይነገራል፡፡ የሆሄያቱ መጀመሪያ ሀ-ለ-ሐ ወዘተ ግዕዝ ይባላሉ፡፡

እነዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡ ምናልባትም የውክልና መነሻ ይሆን? ስለዚህ ጉዳይ መሪጌታ ፈቃዱ ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፋቸው (ገጽ 73)፤ የግዕዝ ፊደላትን ትርጉም "ሀ" ማለት "የአብ አኗኗር ከዓለም በፊት ነው" የሚል ሠፍሮ የሁሉም ትርጉም እስከ "ፐ" ቀጥሏል። እዚህ ነጥብ ላይ አንድ የቅርብ ጓደኛዬ የፊደላቱን የተናጠል ውክልና በተመለከተ ሁለት ነገሮችን ነግሮኛል፡፡ አንደኛው የፊደላት ውክልና ሲሆን ሌላው ደግሞ የኩነቶች የጊዜ ቀመርን ይመለከታል። በዚህ ጽንፈ ዓለም ውስጥ "ጸ" የሚባለው ሆሄ ጸሎቱ በሚል ይታወቃል፡፡ ጸሎቱ "ጸ" ከሰባቱ ዘሮቹ ጋር ለመላዕክታትና ለመለኮት ውክልና የተሰጣቸው መሆኑን በአንድ ሊቅ እንደተነገረው ጓደኛዬ አስረዳኝ፡፡ ለምሳሌም ግዕዙ "ጸ" በምድር ላይ ሰዎችን ለማጥቃት ሰይጣን የሚያሰማራቸውን ርኩስ መናፍስትን ለሚዋጉ የመላዕክት ተዋጊዎች በአርማነት ማገለገል አንዱ ውክልናው እንደሆነ፤ በአሁኑ ወቅትም በዓለማችን ሕዝብ ዘንድ በስጋትነት የተንሰራፋውን ኤችአይቪ ቫይረስን ለመከላከል የወጣው ምልክት ቅርፁ "ጸ" መሆኑ ትክክለኛ የፊደላችን ውክልና እንደሆነ ሊቁ እንዳስረዱት ነግሮኛል፡፡ ይህን ምልክት ያመጡ ሰዎች በመላዕክቱ መንፈሳዊ ወይም ልባዊ ምክር እንደሆነም ጨምሮ ገልፆልኛል፡፡ በዚህም እጅጉን ተገርሜያለሁ፡፡

እኚሁ ሊቅ ለጓደኛዬ እንደነገሩት ከሆነ፣ በዓለማችን ላይ በሥልጣኔ የገዘፈች ሀገር ሁለት መንትያ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች በክፉ ሰዎች ተነሳሽነት የሚፈርሱበት ጊዜ በግዕዝ የፊደልና የአኃዝ ጥምረት ተቀምሮ በኢትዮጵያ አቆጣጠር መስከረም 1 ቀን 1992 መሆኑ ይታወቅ እንደነበር ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉትንና ሌሎችንም ዘበት የሚመስሉ ትውፊቶች ንቆ ለማለፍ ይቻል እንደሆነ በእውነቱ መናገር ይከብደኛል፡፡ ለማንኛውም የግዕዝ ፊደላት ከነሙሉ ክብራቸው ግዕዝንና አማርኛን ማገልገል እንደሚኖርባቸው በጠቃቀስኳቸው ሃሳቦች መሠረት ማመን ይቻላል፡፡ ፊደላቱ እንዳይሸራረፉ ሌላው አሳማኝ ጉዳይ በሞክሼ ፊደላቱ የተጻፉ ጥንታውያን መጻሕፍት ያሰፈሯቸው ቃላት እንደየአገባባቸው ትርጉማቸው ስለሚለያዩ፣ የተመዘገበውን ታሪክ መጭው ትውልድ እንዲያውቀውና እንዲመራመርበት ሙሉውን ፊደላት

ፊደል ወደ ገፅ 14 ዞሯል


## Brave Hearts
## ብሬቭ ኸርትስ

### የኦዲት ሥራ ጨረታ ማስታወቂያ

መሟላት ያለባቸው ሰነዶችና መስፈርቶች፡-

1. የኦዲት ስራ ህጋዊ ፈቃድ ለ2007ዓ.ም. የታደሰ
2. የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው
3. በኦዲት ስራ ላይ የሰራችሁበትን ማስረጃ ማቅረብ የምትችሉ
4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Tin Number) ያለው
5. የኦዲት ስራውን የሚያጠናቅቁበትንና ሪፖርቱን የሚያስረክቡበት ጊዜ ገደብ
6. የኦዲት ስራውን ለመስራት የሚያስከፍለው ገንዘብ መጠን (Audit fee)
7. ሰርቶ የሚያጠናቅቅበት ጊዜ
8. የኦዲት ስራው የሚሰራው እ.ኤ.አ ከJune 2014 እስከ Dec. 2014 ያለውን የ7 ወር ይሆናል

የድርጅቱ አድራሻ፡- ግንፍሌ ድልድይ፣ ሎሚ እንግዳ ማረፊያ አጠገብ

ስልክ ቁጥር

0913-86-99-29 / 0911-17-62-27 / 0118-69-50-50

የመልእክት ሳጥን ቁጥር 35452



## "ሥነ አእምሮ" - አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

የጭንቀት፣ ውጥረት፣ ድብርትና የሌሎች የአእምሮ ህመሞችን ምንነት በጥልቀት ይዳስሳል፣ ችግሮቹን ለመቆጣጠርም መንገዱን ያመላክታል፣

***ሥነ አእምሮ***ን ካነበቡ በሁሉም የአእምሮ ጤና የጤና ጉዳይ ላይ የራስዎና የቤተሰብዎ አማካሪ እንዲሆኑ ያስችልዎታል፣

በዘመኑ የተደረሰባቸውን ሣይንሳዊ የሥነ አእምሮ እውነታዎች መሠረት አድርጎ ለአገራችን አንባቢያን በሚስማማ መልኩ በመጽሐፉ አቅርቧል፣

ማንኛውንም አሉታዊ ስሜትን መቆጣጠር እንዲችሉ የሚያግዝ በመሆኑ መጽሐፉ የሁሉም ነው፣

***ሥነ አእምሮ***፤ መጽሐፍ ብቻ አይደለም መመሪያም እንጂ፣



# እየራባቸው የሚማሩ ህፃናትን መታደግ...

## "ምሳቸውን እያሰቡ እንዲማሩ አንፈልግም"

*በቅዱስ ሚካኤል ት/ቤቶች ለሰባት አመታት ያስተማረው ሳሙኤል ተስፋዬ፣ የት/ቤቱ ዳይሬክተር እንደነበረም ይናገራል፡፡ በመምህርነት ዘመኑ በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቀው ምሳ ሳይመገቡ የትምህርት ገበታ ላይ የሚቀመጡ ህፃናትን ባያስተውልም ተወልዶ ባደገበት አራት ኪሎ ግን በድህነት የሚማቅቁና ሳይመገቡ ት/ቤት የሚሄዱ ህፃናት ተማሪዎችን መመልከት የዕለት ተዕለት ተግባሩ እንደነበር አይዘነጋውም ፡፡ የወደፊት እጣፋንታቸው እረፍት ይነሳው እንደነበር የሚናገረው ሳሙኤል፣ መምህርነቱን ትቶ እነዚህን ህፃናት በተቻለው ሁሉ የመደገፍ ስራ እንደጀመረ ይገልፃል፡፡ ከጓደኛ፣ ከዘመድ ወዳጅና ከበጐ ፈቃደኞች አምስት እና አስር ብር እየለቀመም ለችግረኛ ተማሪዎች በሳምንት አንድና ሁለት ቀን ዳቦና ወተት ማቅረብ ጀመረ፡፡ ፈቃደኛ የሆኑ መምህራንን በማስተባበርም ቅዳሜ ቅዳሜ ልጆቹን እያስጠና ምሳ ያበላቸዋል፡፡*

*ይህን በጐ ሥራውን አጠናክሮ ለመቀጠልም በ2005 ዓ.ም "Friends Ethio - Students Support (Fess) የተሰኘ የበጐ አድራጐት ድርጅት አቋቋመ፡፡ የአዲስ አድማስ ጋዜጠኛ ናፍቆት ዮሴፍ ከድርጅቱ መስራች ሳሙኤል ተስፋዬ ጋር ያደረገችው ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*


ፎቶግራፍ አንተነህ አከሊሉ

ሳሙኤል ተስፋዬ

*እስቲ ፍሬንድስ ኢትዮ ስቱደንትስ ሰፖርት (FESS) የሚያከናውናቸውን ስራዎች ንገረኝ?*

በዋናነት የምንሰራው የህፃናት ተማሪዎች የነገ ተስፋ ላይ ነው፡፡ ማናችንም ብንሆን ዛሬ ላለንበት ማንነት መሰረታችን ህፃንነታችን ነው፡፡ ዛሬ ኪስ አውላቂ፣ ተሳዳቢ፣ ጋጠወጥ ... የሆኑ ሰዎችን የኋላ ህይወት ብንፈትሽ፣ በአብዛኛው የልጅነት ዘመናቸው የተበላሸ ነው፡፡ ከነዚህ ሰዎች ጀርባ በጥሩ ስነ - ምግባር ለማነፅና ለማሳደግ ሃላፊነት የወሰደ ቤተሰብ ወይም ማህበረሰብ አልነበረም ማለት ነው፡፡ እኔም መምህር እንደመሆኔና ከህፃናት ጋር በነበረኝ ቀረቤታ፣ በግል ት/ቤት የሚማሩ የባለፀጋ ልጆችንና በመንግስት ት/ቤት የሚማሩ የችግረኛ ቤተሰብ ልጆችን ልዩነት እያየሁ የሚያሳስበኝ ጉዳይ ነበረ፡፡ ስለዚህ በአቅሜ በምችለው መጠን ወላጅ የሌላቸውን ወይም በእናት ብቻ የሚያድጉ ልጆችን የወደፊት ህይወት ብሩህ ለማድረግ፣ ከምግብና ከትምህርት መሳሪያዎች ድጋፍ በተጨማሪ የስነ - ልቦና ድጋፍ ለማድረግ ነው (FESS)ን የመሰረትኩት፡፡

*ምን ያህል ተማሪዎች ድጋፍ ያገኛሉ? የድጋፍ ትኩረትህስ?*

ህፃናቱ የአንድ ት/ቤት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስንጀምር በ10 ተማሪዎች ነበር፤ አሁን ወደ 60 ከፍ ብለዋል፡፡ የምንመርጥበት መስፈርት ያሉበት የኑሮ ደረጃ ነው፡፡ ግማሾቹ ሁለቱም ወላጆች የሏቸውም። ግማሾቹ ምንም የገቢ ምንጭ ከሌላቸው እናቶቻቸው ጋር የሚኖሩ ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የት/ቤት፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የደንብ ልብስና ምሳ እናቀርብላቸዋለን፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ የግማሽ ቀን ጥናት እያስጠናን ምሳ በልተው እንዲሄዱ እናደርጋለን። ተማሪዎቹ ቢያንስ ምሳቸውን እያሰቡ እንዲማሩ አንፈልግም፡፡ የምሳ ጥያቄያቸውን ሙሉ ለሙሉ ለመመለስ እየጣርን ነው፡፡ የካ ክፍለ ከተማ ውስጥ ሾላ ገበያ አካባቢ "ተስፋ ብርሃን" በሚባል የመንግስት ት/ቤት ውስጥ ነው እየሰራን ያለነው። እንደ ድርጅት ፈቃድ ሳላወጣ በፊት፣ ኮተቤ አካባቢ ወንድይራድ ት/ቤት ውስጥ ለአንዳንድ ችግር ለባሰባቸው ተማሪዎች የደንብ ልብስ፣ ደብተር እና መሰል ቁሳቁሶችን እሰጥ ነበር፡፡ አሁንም ደጋፊ ባገኝና ቢሳካልኝ እዚያ በርካታ በተጐሳቆለ ህይወት ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች ስላሉ እነሱን መርዳት እፈልጋለሁ፡፡

*ስትጀምሩ ለአስሩ ተማሪዎች መርጃ የሚሆን ገንዘብ ነበራችሁ?*

ምንም ገንዘብና አቅም አልነበረንም፡፡ ፍላጐት ብቻ ነው የነበረን፤ ነገር ግን እነዚህን አስር ተማሪዎች በት/ቤቱ በጐ አድራጐት ክበብና ቤት ለቤት እየሄድን፣ (በእርግጥ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ካረጋገጥን በኋላ ነው) አምስት አስር ብር እየሰበሰብን፣ ማክሰኞ ማክሰኞ በምሳ ሰዓት ዳቦና ወተት ማቅረብ ጀመርን። ከዚያም ቅዳሜ ከመምህራን ጓደኞቼ ጋር በመሆን ማስጠናቱንና የዳቦና ወተት አቅርቦቱን ቀጠልን፡፡ ይህን ስራችንን ለወዳጅ ዘመድ መንገር ስንጀምር፣ ቦሌ መድኀኒያለም አካባቢ የሚገኝ አንድ መንፈሳዊ ማህበር፣ የኤሌክትሪክ ምጣድና ለስራው መጀመሪያ የሚሆን ጤፍ ለገሰን፡፡ እዚያው ት/ቤት ውስጥ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሆነች ኩሽና ሰርተን፣ እዚያው እያበሰልን ምሳ ማቅረብ ጀመርን፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን ነው የምንረዳቸው ተማሪዎች ወደ 60 የደረሱት፡፡ ምሳ በደንብ የምናቀርበው ቅዳሜ ቅዳሜ ነው፡፡ የወደፊት አላማችን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ሙሉ የምሳ አቅርቦት መስጠት ነው፡፡ ከተማሪዎቹ አዕምሮ ውስጥ የምሳ ጥያቄ ወጥቶ ትምህርታቸውን ብቻ እንዲያስቡ ለማድረግ መትጋታችንን ቀጥለናል፡፡

*አሁንስ የሚደግፏችሁ አገኛችሁ? የገንዘብ ምንጫችሁ ምንድን ነው?*

ቋሚ ለጋሽ አላገኘንም፤ ሆኖም አሁን አሁን ጓደኞቻችንም እያገዙን እኛም ፕሮፖዛል በአንዳንድ ድርጅቶች በማስገባት፣ ጥቂት ድጋፎችን በማግኘታችን የተማሪዎቹን ቁጥር ወደ 60 ማሳደግ ችለናል፡፡ ከዚህ የበለጠ መስራት እንፈልጋለን፡፡ በአዲስ አበባ የመንግስት ት/ቤቶች ውስጥ በርካታ ምሳ ሳይበሉ የሚውሉ፣ ነገር ግን በትምህርት ገበታ ላይ በየቀኑ የሚቀመጡ በርካታ ተማሪዎች እንዳሉ በጥናትም ተረጋግጧል፡፡ በተለያዩ ሚዲያዎችም ተዘግቧል፡፡ እኛም ድጋፍ ባገኘን ቁጥር አሁን ከምንሰራበት ት/ቤት በተጨማሪ በሌሎች ት/ቤቶች ያሉትን ለመድረስ እቅድ አለን፤ አሁን አቅም ገድቦን ነው፡፡

*ዕቅዳችሁን ለመተግበር ምን አሰባችሁ? በገንዘብ በኩል ማለቴ ነው ...*

በአሁኑ ሰዓት ከፅዳት ሰራተኛ እስከ ዶክተሮች እንዲሁም የአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ካንትሪ ዳይሬክተር ድረስ አባላት ማፍራት ችለናል። አምስት ሺህ አስር ሺህ ብር የሰጡን አንዳንድ ድርጅቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ ለጊዮርጊስ ቢራ ፕሮፖዛል አስገብተን 10ሺህ ብር ለግሶናል፡፡ በጣም እናመሰግነዋለን፡፡ እነዚህ አባላት ያልኩሽ በወር ከአምስት ብር ጀምሮ እስከ አምስት መቶ ብር ይሰጡናል፡፡ ከውጭም ጓደኞቻችን ብር እያሰባሰቡ መላክ ጀምረዋል፡፡ ይህን በማሰባሰብ ነው የልጆቹን የነገ ተስፋ ለማለምለም የምንሮጠው፡፡

*እነዚህ ተማሪዎች ክረምት ላይ ት/ቤት ሲዘጋ ምሳቸው ይቆማል ማለት ነው?*

በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ ይሄንንም በጣም አስበንበታል፡፡ እኛ ምግብና የትምህርት ቁሳቁስ ከማቅረብ ባሻገር በጣም ትኩረት የምንሰጠው ለስነ - ልቦናቸውና ነጋቸውን የመቅረፅ ጉዳይ ላይ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጨዋለሁ፡፡ አንድ እናት ያለምንም ቋሚ ገቢ ሶስትና አራት ልጆች ለማሳደግ ያገኘችውን ሁሉ ስትሰራ፣ ስለምትውል ልጆቹን ለመቆጣጠር አትችልም፤ ስለዚህ እነዚህ ልጆች ባህሪያቸውም ወጣ ያለ ነው፡፡ እኛም ያንን ባህርይ ለማራቅ እንሰራለን። እነዚህ 60 ልጆች አሁን ፍቅርና እንክብካቤ ስንሰጣቸው፣ ባህሪያቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ አይተናል፡፡ ስለሆነም ክረምት ላይ ሁለት ወርና ከዚያ በላይ ዝም ብለን ከለቀቅናቸው፣ ወደ ቀደመ ባህሪያቸው ይመለሳሉ የሚል ስጋት ስላለን ባለፈው ክረምት ከሰኔ እስከ ነሐሴ መጨረሻ በሳምንት ሶስት ቀን ሐሙስ፣ አርብና ቅዳሜ አስጠንተን፤ ምሳ እያበላን ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ በአሁኑም ክረምት ይሄው አሰራር ይቀጥላል፡፡

*አንተ ታስተምርበት የነበረው ቅ/ሚካኤል ትምህርት ቤት ደህና ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ልጆች የሚማሩበት ነው፡፡ አንተ በህይወትህ በዚህ አይነት ችግር ውስጥ አልፈህ ነበር? እንዴት ስራህን ትተህ እዚህ ውስጥ ገባህ?*

በእርግጥ እኔ የተማርኩት የመንግስት ት/ቤት ነው፡፡ ነገር ግን ምሳ ያለመብላት ችግር አልነበረብኝም። ወላጆቼ በጥሩ ሁኔታ ነው ያሳደጉኝ፡፡ ተወልጄ ያደግሁት ግን አራት ኪሎ ነው። አራት ኪሎ የድህነት ጥግ የሚታይበት አካባቢ እንደነበር ማንም አይክደውም፡፡ ስለዚህ አካባቢዬ ላይ የነበረውን የኑሮ ሁኔታ ጠንቅቄ አውቀዋለሁ። ብዙ ነገሩን ከአካባቢዬ አይቼዋለሁ፡፡ ለዚህ ነው ይሄንን ስራ ለመስራት በጥሩ ደሞዝ የምሰራበትን የዳይሬክተርነት ስራ ትቼ የወጣሁት፡፡

*በመጨረሻ ...*

ህፃናት የመመገብ፣ በጤናና በህይወት የመኖር፣ የመማርና ፍቅር እንዲሁም እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ምሳና ቁርስ ማግኘት የእነሱ የቤት ስራ መሆን የለበትም፤ ምክንያቱም ለአቅመ ስራ አልደረሱም፤ ፈልገውም ወደዚች ምድር አልመጡም፡፡ ስለዚህ ሁላችንም በምንችለው አቅም ከዚህ ጭንቀት እናውጣቸው ባይ ነኝ፡፡ አንዳንዶቻችን ተርፎን ከምንጥለው እናጉርሳቸው። እኛ የአቅማችንን ያህል ህፃናቱን ለመርዳት ስንነሳ፣ በኢትዮጵያዊያን የመደጋገፍ ባህል ተማምነን ነው። ስለዚህ በገንዘብም፣ በጉልበትም፣ በእውቀትም፣ በምክርም ድጋፍ እንሻለን፡፡ ግለሰቦችም ድርጅቶችም እንዲያግዙን ጥሪ እናቀርባለን፡፡ አሁን ስንተባበር ነው ኃላፊነት የሚሰማው መልካም ዜጋ የምንፈጥረው፡፡


# Vacancy Announcement

Century General Trading PLC (Century Promotion Service), is a leading company in organizing trade and investment promotional and related event in the country. With a view to enhancing its service, the company has advertised the following vacancies to young and highly motivated professionals.

| Nō. | Position | Education | Experience | Additional Skill | Required No. |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Marketing Expert | BA Degree in Marketing or Sales Management | 0 year & above | Good Command of English language, Computer literate (Microsoft office, Intenerate) interested to take challenging assignment & deal with wide ranges of clients including foreign companies. | 3 |
| 2 | Executive Secretary | BA Degree in Secretarial Science & Office Management | 5 Years & above | Must have good reading & writing and communication skill in English, Knowledge of office system, Software including the internet | 1 |
| 3 | Driver | *10th/12th Grade complete and 3rd grade driving license* | *5 years & above* | - | 1 |

**NB: For all Applicants;**

- **Salary:** Negotiable
- **Place of work**: Addis Ababa

Applicants who can fulfill the above requirements can send their application letter together with non returnable relevant copes of educational and other supporting documents in person with in **10(ten) working days** from the date of advertisement to the following address.

***Head office wollo sefer, Mina building 2nd floor***
***Tel- 0115-54-92-45/46***
***E-mail-*** *info@centurypromotion.com*

# በዓባይ ዱባ ሸለቆ ሌሊቱ ቀን፤ ቀኑም ቀን

ገ/ክርስቶስ ኃ/ሥላሴ

ለታላቁ የዓባይ ሕዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ብዙ መረጃዎችና ጉዳዮች እንደተነገሩ ይገባኛል፡፡ ይሁንና የሚባሉት ነገሮች ሁሉ ማለቂያ ያላቸው አይደሉም፡፡ መረጃዎቹ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ በአንክሮ፣ በፍቅር፣ በልግስናና በታላቅ ኩራት የሚያዳምጧቸው፣ የሚያነቧቸውና የሚከትቧቸው እንደሆኑ ከልብ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሰሞኑን የታላቁን ሕዳሴቸው እንደሆኑ ከልብ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሰሞኑን የታላቁን ሕዳሴ ኤሌክትሪክ ኃይል ግድብ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ በቅርበት ለመመልከትና ግድቡ የተጀመረበትን 4ኛ ዓመት ለማሰብ የሚያስችሉ የተለያዩ ኪነጥበባዊ ግብአቶችን ለማሰናዳት ከየኪነጥበባት ዘርፉ የተውጣጣ ቡድን ጉባ ሸለቆ ጉራ በማለት ዓባይንና የግድቡን ግንባታዎች በአካል ተገናኝቷል፡፡ ከድርሰት፣ ከሙዚቃ፣ ከስዕልና ቅርፃ ቅርጽ፣ ከፊልም ሥራ፣ ከፎቶግራፊንግ፣ ከዜማ ቅንብርና ከመሳሰሉት ማኅበራት የተውጣጡት የዚህ ጉዞ አባላት በየሙያቸው ጥልቅ ስሜት ያንን አስገራሚና ፋታ የሌለው የግድብ ሥራ ምልአተ እንቅስቃሴ እጅግ በመመሰጥና በመደመም ተመልክተውታል፡፡ እኔም የዚሁ ለታሪክ ያደለው ቡድን አባል ነበርኩ፡፡

የታላቁ ዓባይ ሕዳሴ ግድብ በሀገሬ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እየተገነባ ማየትና የዚህም ተግባር ባለድርሻ ሆኖ ለትውልድ የሚሸጋገር ታላቅ ሐብት ማፍራት የሚያጐናጽፈውን ክብርና ልዕልና ምናልባትም በቃላት መግለጽ አስቸጋሪ መሆኑን ብረዳም የአቅሜንና የተሰማኝን ለማጋራት ሃሳቡን በአጭሩ እነሆ ብያለሁ፡፡ ከጽሑፌ ርዕስ መረዳት እንደሚቻለው በዱባ ሸለቆ ሌሊት የለም፡፡

ድቅድቅ ጨለማውን ያስወገደው ደግሞ ከራሱ ከአባይ (ጣና በለስ) የመነጨውና በርካታ ኪሎ ሜትሮች ተስቦ ዱቦ የደረሰው የኤሌክትሪክ መብራት ነው፡፡

የበለስ መብራት ከራሱ የበለጠና ለበርካታ አካባቢዎች የሚዳረስ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ኃይል ሊገነባ ዱባ ታድሟል፡፡

ጀግኖቹን፣ የበረሃ ጀቢራዎቹንና ታሪክ ሠሪዎቹን የወንዙ ልጆች በዱባ ተገኝቶ የኤሌክትሪክ ፍላጐታቸውን በሙሉ እያሟላላቸው፣ ሌሊቱንም ከጉብታው፣ ከዳገቱ፣ ከየቤታቸውና ሠፈራቸው የብርሃን ፏፏቴውን እያንፏፏላቸው በጥብቅ አጋርነት ተሰልፏል፣ ከጣና በለስ የዘመተው መብራት፡፡ ዓባይን ዓባይ ሲያለማው የሚያሳይ አይነተኛ ትንግርት፡፡ በዚህ ኃያል ትንግርት ዋንኛው የግድቡ ግንባታ አርበኞች ማንም እንደሚያውቀው ከመሪው ዋና ኢንጂነር እስከ የካምፕ ጉድፍ አስወጋጆቹ ድረስ ያሉት የዱባ ሸለቆ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው፡፡ ታሪክ የጣለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊነት በመወጣት በረሃብተኛነት (በችጋር) ስሟ የሚነሳ ኢትዮጵያ ደግሞ ላለማየት ከሁሉም የአገራችን ማዕዘናት የዱባን ሸለቆ እንደንብ ወረውታል፡፡ ሌት ተቀንም እየታተሩ ማዬት የተለየ ምጡቅ ስሜት ውስጥ ያስገባል፡፡

እነዚህ ብርቱ ወገኖቻችን የግሪክና ሠራዊት አባላት ሀገራቸውን እጅግ ብዙ ከሆነው የጥርጊያ ሠራዊት ወረራ ለመታደግ በአንዲት ጠባብ ሠርጥ ውስጥ አንገት ለአንገት ተቀላልተው የተሰውትን 300ዎቹ ጀግኖቹ የተሰኙትን አንበሶች ታሪክ አስታወሱኝ፡፡ 9000ዎቹ ጀግኖቹ በዱባ ዓባይ ሸለቆ ፍልሚያ የዘጠና ሚሊዮን ሕዝብ (ወደፊትም ለሚፈጠረው) ምኞትና ተስፋ በማሳካት የዘመናት ጭንቀት፣ ቁጭትና ተዋራጅነቱን ሊታደጉት ላብ እያፈሰሱ፣ አቧራ እየላሱ፣ ያለዕረፍት ይማስናሉ፡፡ እነዚህ ሺህ ጀግኖች የሚሊዮኖች ውክልናቸውን በብቃት እየተወጡ ናቸው፡፡ የሚተማመኑትም በሚሊዮኖቻችን ደጀንነት መሆኑን ሁሉም ሊረዳው ይገባል፡፡ እነዚህ ጀግኖች ሠራተኞች በውቀቱና በአቧራው መካከል በፈገግታና በልዩ ልግስና ሲያስተናግዱን ማየት ምንኛ አስደናቂ ሁኔታ መሰላችሁ፡፡

የኪነጥበባት ቡድኑ ከግድቡ ቦታ ሲደርስ ሌሎች የዓለም አቀፍና የአገር ልጆች ጐብኝዎች በእንግድነት ታድመዋል፡፡ የጐረቤት ሱዳን የግንባታ ኢንጂነሮች ማኅበር አባላትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ፋኩልቲ በተለያዩ ሙያዎች ትምህርት እየተከታተሉ ያሉ ተማሪዎችና መምህራኑ ከእኛ ጋር በአንድ አነስተኛ አዳራሽ ታድመናል፡፡ ግጥጥሞሹ ግርምታን የሚፈጥር ነበር፡፡ ምክንያቱም ሦስቱም ቡድን የተገናኘው እዚያው እግድቡ እንብርት ላይ ነው፡፡

ሌሎች በርካታ ተማሪዎችም ግድቡን እየጐበኙ እንደነበር ተመልክቼአለሁ፡፡ እንደ ግድቡ ዋና ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ገለፃ ከሆነ የግድቡ ጐብኚዎች በየዕለቱ ይጐርፋሉ፡፡ ጐብኝዎቹ የግድቡን ሁለገብ ተግባራት ካዩ በኋላ፣ ከደስታቸው ብዛት የተነሳ ራሳቸውን መቆጣጠር ያቅታቸዋል፡፡ መመለስ ደስ የማይላቸው፣ እጅግ የሚያለቅሱ፣ የሚያቅራሩና የሚፎክሩ፣ በአሸዋው ላይ የሚንገዋለሉ ወዘተ በርካቶች እንደሆኑ ተነግሮናል፡፡ እኛም የዚሁ የፍቅርና የአንድነት ሕዳሴ ግድብ የአሸናፊነት ምትሀት ምርከኞች ነበርን ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ ሁላችንም የጉዟችንን ዓላማዎች እንዴት እንደምንፈጽም በምናውጠነጥንባት አዳራሽ የሕዳሴው ግድብ ዋና መሐንዲስ ስመኘው በቀለ በፊለፊታችን ቆመው "እንኳን ወደታላቁ የሕዳሰ ግድብ በደህና መጣችሁ" ሲሉ ሞቅ ባለ ፈገግታቸው አማተሩን፡፡ የሁሉም መንፈስና ሥጋ ጭምር በአንክሮ ተመለከታቸው፡፡ ገለፃቸውን ቀጠሉ፡፡ የግድቡን ይዘት፣ ከዓመታት በኋላ ስለሚፈጠረው ግዙፍ ሰው ሰራሽ ሐይቅ፣ ስለግንባታው ጥራትና ዘመናዊነት፣ ለሀገራችንና ለታችኛው ተፋሰስ አገሮች (ሱዳንና ግብፅ) ስለሰነቀው ጥቅሞች፣ ከጐረቤትም አልፎ በግብፅ በኩል ሜዲትራንያንን ባሕር አቋርጦ ወደቱርክና ስፔይን፣ በቀይባሕር በኩል ወየየመንና ሌሎች አገሮች ሊጓጓዝ የታሰበውን የኤሌክትሪክ ኃይል ወዘተ አስረዱ፡፡

የተረዳንበትን ቋንቋ በአጭር ቃል ለመግለጽ ኩርጥ ያለና ስሜትን የሚያገዝፍ ነበር፡፡ የግድቡ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴም ሲጐበኝ ይደረግ የነበረው ገለፃና ለጥያቄዎች ይሰጡ የነበሩ መልሶች የማይወላውሉና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥብቅ ውሳኔ በማስረገጥ መልዕክት የሚቸሩ ነበሩ። "እንደጀመርነውና እንዳጋመስነው በተባበረ አቅማችን እናጠናቅቀዋለን!" የሚል የልበሙሉነት መልዕክት፡፡

በተደረጉበት ገለፃዎችም ሆነ በጉብኝታችን የተማርኳቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች መፈንጠቅ

ሸለቆ ወደ ገፅ 22 ዞሯል

ኢሕባማ ELA

# Invitation for consultancy work

CSSP Civil Society Support Programme

**1. Background**

The Ethiopian Lawyers' Association (ELA) is a non-profit making and a non-partisan professional association of lawyers. It is established with the aim of promoting the interest of its members and the development of the legal profession. It also upholds rule of law, the independence of the judiciary, good governance and human rights. It endeavors to ensure the dignity and independence of the profession and to upgrade the legal skills of practicing lawyers along with the provision of free legal aid to those who are needy.

The Association is currently implementing the project entitled "strengthening Ethiopian lawyers' association thorough expanding its membership base". The project is aimed at increasing the number of` members throughout the country and capacity building of the association. Accordingly one of the activities planned for the implementation of this project is the development of a five year strategic plan.

**2. Objectives**

The objective of the strategic plan development is to help realize the association's aim through long term planning that has the capacity to yield sustainable impact, identify strategic issues, setout strategies to be employed as well as outline key programs to be implemented.

**3. Results expected to be achieved**

The consultant shall:

1. Conduct organizational capacity assessment
2. Develop of strategic plan of ELA
3. Asses and identify causes impeding membership expansion and prepare membership strategy

**4. Scope of the work**

- Propose long and short term strategy and program
- Map partners and government structure relevant for ELA's work
- Analyze pertinent legal and policy frameworks that benefit ELA and its 7 legal aid centers located at Addis Ababa, Jigjiga, Bahir dar, Hawassa, Mekele, Assosa and Adama.
- Conduct a simple SWOT analysis of ELA and the 7 legal aid centers
- Review the work and experience of relevant CSOs and government offices that give lessons to ELA

**6. Key Deliverables**

The consultant is expected to deliver the following:

A. Present an inception report, containing the methodology, brief literature review, a detailed work plan for the consultancy work, questionnaires, assessment tools as well as a list of key people and organizations

B. A zero draft consolidated report submitted to ELA covering the assessments, strategic plan, monitoring and evaluation formats. The reports should contain an executive summery not exceeding one page, and specific findings , identification of key activities for immediate action .The zero draft report should be presented to ELA in a half day review session

C. Facilitate a one day validation workshop to members to members to present, review and define the strategy document and collect additional input to

D. Submit a final three hard and soft copy report after the workshop

**7. Language**

The language of the consultancy work is Amharic.

**8. Time frame of consultancy**

The consultant/s or firm is expected to submit plan including time frame

**9. Profile of the consultant**

- The consultant shall have a team composed of a lawyer , sociologist or a related social science field graduate with a post graduate degree
- Experience in strategic planning process and organizational capacity assessment
- Strong skills in research
- Professional experience in participatory research approaches, strategy and plan development
- Relevant experience working in CSOs and government agencies
- Excellent writing skills
- Knowledge of the current legal framework governing civil society organizations

**10. How to apply**

Interested candidates who meet the criteria for this consultancy may send their technical and financial proposal copies of documents including cover letter, detailed curriculum vitae, and two current referees of similar assignments conducted copies of relevant degrees and certificates to ELA office located around ambassador next to the post office on Kidane Beyene building 1st floor, Tel 0115 53 01 22, Email eba@ethionet.et within fifteen 15 working days of advertisement or before February 24 2015

# “ወገቧ ቸቦ አይሞላም” - ጤና ያቃውሳል!

## ከልክ ያለፈ ቅጥነት መሀንነትን ሲያስከትል ይችላል

መታሰቢያ ካሳዬ

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ትኬት ቢሮ ውስጥ በትኬት ሽያጭ ባለሙያነት ተቀጥራ መስራት ከጀመረች አምስት አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ቀላ ያለ መልክና ረዥም ቁመትን ብትታደልም የሰውነቷ ቅጥነት እህል በልታ የማታውቅ ያስመስላታል፡፡ ሁሌም ቅጥነቷን በአለባበሷ ለመደበቅ ትጥራለች፡፡

ብሔራዊ ቴያትር አካባቢ ከሚገኘው መ/ቤቷ ተነስታ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ እስከምትድረስ ወጪ ወራጅ ወንዶች እንደ ዘበት ጣል በሚያደርጉባት የለከፋ ቃላት ሁሌም ትናደዳለች። በተለይ ከወፍራም ጓደኞቿ ጋር በምትሄድበት ጊዜ “ከእሷ ላይ ተልጠሽ ነው? ልጣጪ ነሽ?” እያሉ እንደሚያበሽቋት ትናገራለች፡፡ ለከፋው ጓደኛዋን ፈገግ የሚያሰኛት ቢሆን ለእሷ ግን ከእሬት የመረረ ነው፡፡

ወጣቷ ለከፋ የስነ ልቦና ችግር የዳረጋትን ቅጥነቷን ለማስተካከል ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም፡፡ ሰዎች ስታማክር፤ “ውፍረት ምን ያደርግልሻል? በሽታ እኮ ነው” ይሏታል፡፡ እሷ ግን ያልተነካ ግልግል ያውቃል ትላቸዋለች፡፡ የሚያወፍሩ ምግቦችን አብዝቶ ከመመገብ አንስቶ የተለያዩ የቫይታሚንና ሚኒራል ይዘት ያላቸው መድኀኒቶችን በመውሰድ ቅጥነቷን ለማስወገድ ጥራለች፡፡ ግን ለውጥ አላመጣችም፡፡

የ28 አመቷ ወጣት በሰውነቷ ቅጥነት ሳቢያ ከሚደርስባት የሥነ ልቦና ችግር የበለጠ የሚያሳስባት በየጊዜው በቀላል ህመሞች መጠቃቷና ራሷን ከበሽታ የመከላከል አቅሟ ደካማ መሆን ነው፡፡ እንደ ጉንፋን፣ ራስ ምታትና የምግብ አለመስማማት ያሉ ቀላል በሽታዎች ለሶስትና አራት ቀናት ሊያስተኝዋት ይችላሉ፡፡ በየጊዜው ለሚደቋቁሷት ህመሞቿ የምታነጋግራቸው የህክምና ባለሙያዎች፤ሰውነቷ ከጤናማውና ከሚፈለገው የክብደት መጠን በታች በመሆኑ በሽታን የመቋቋም አቅሟ እንደተዳከመና በዚህም ምክንያት ለተለያዩ በሽታዎች በቀላሉ እንደምትጋለጥ ገልጸውላታል፡፡ ከመጠን ያለፈው ቅጥነቷ መሀንነትን ሊያስከትል እንደሚችልም ነግረዋታል፡፡ ወደ ትክክለኛው የሰውነት ክብደት መጠን ለመግባትም በባለሙያ የታገዘ የአመጋገብ ሥርዓትን እንድትከተል ምክር ለግሰዋታል፡፡

ወጣቷ የህክምና ባለሙያዎቹ የሰጧትን ምክር ተግባራዊ በማድረግ ከችግሯ ለመላቀቅ ብትጥርም ምንም ውጤት ለማግኘት ባለመቻሏ ተስፋ መቁረጧን ትናገራለች፡፡ አሁን እሷን ይበልጥ



የሚያሳስባት ጉዳይ ግን የበዛው ቅጥነቷ ልጅ ወልዶ መሳምን እንዳይነሳት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት እንደዚህች ወጣት ሁሉ በቅጥነት ሳቢያ ለሚመጡ የጤና ችግሮች በቀላሉ የሚጋለጡ ወጣቶች እየበረከቱ እንደሆነ የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህክምና ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ፋሲል ተካልኝ ስለ ሁኔታው ሲያስረዱ፤ “ከሚፈለገው የሰውነት ክብደት መጠን በታች መሆን ለተለያዩ የጤና ችግሮች ሊዳርግ ይችላል፡፡ ትክክለኛ የሰውነት ክብደት መጠንን ለማወቅ የሚቻለው Body mass index በሚባለውና የሰውነት ቁመትን እርስ በርሱ በማባዛት፣ ክብደትን ለቁመት ብዜት በማካፈል ስሌት በሚሰራ ሳይንሳዊ መለኪያ መሰረት ነው። ሰዎች በዚህ ስሌት መሰረት የሚያስፈልጋቸው የክብደት መጠን ተሰርቶ ከዚያ ያነሱ ከሆነ፣ ከክብደት በታች ናቸው ይባላል፡፡ ይህም ቋሚና ዘላቂ ከሆኑ የጤና ችግሮች አንስቶ በቀላሉ ለበሽታዎች መጋለጥን ለሚያስከትለው የበሽታ መከላከል አቋም ማጣት ሊዳርግ ይችላል” ብለዋል፡፡

ጤናማ ሆነው ምግብ በአግባቡ የሚመገቡና የሰውነት ኢነርጂ ማግኛ ስርአታቸው የተሳካ ሆኖ በዘር አፈጣጠራቸው ምክንያት ከሲታ ሆነው የሚታዩ ሰዎች ግን ይህ አይነቱ ችግር ሊያጋጥማቸው እንደማይችል ሃኪሙ ተናግረዋል፡፡ የሰውነት ክብደት በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀንስ ይችላል ያሉት ባለሙያው፤ ከእነዚህ መካከል የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ ጭንቀትና ውጥረት፣ የአዕምሮ መደበትና የተለያዩ ህመሞች ጥቂቶቹ እንደሆኑ ጠቁመው በቀላሉ በበሽታ መጠቃት፣ መስራት የሚያስችል ኢነርጂ ማጣት፣ ቆዳ መሸብሸብና የጡንቻ መሟሸሽ የዝቅተኛ የሰውነት ክብደት ምልክቶች ናቸው ብለዋል፡፡

ከክብደት በታች የሆኑ ሰዎች ከሚያጋጥማቸው የጤና ችግሮች መካከል ዋንኛው በሽታን የመከላከል አቅም ማጣትና በተለያዩ በሽታዎች በቀላሉ መጠቃት ነው ይላሉ - ባለሙያው፡፡ በቂ ንጥረ ምግቦች በሰውነታችን ውስጥ ያለመኖር፤ ቆሻሻን ከሰውነታችን ውስጥ የማጣራት ሂደትን የሚያስተጓጉል በመሆኑ ሰውነታችን በመርዛማ ኬሚካሎች እንዲጎዳ ያደርጉታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዝቅተኛ ክብደት ኢንፌክሽኖችን የመቋቋም ብቃትን በማዳከም ለበሽታ ይዳርጋል። ከመጠን ያለፈ ድካም፣ የልብ መምታት ችግር፣ የስርዓተ ልመትና የምግብ መፍጨት ችግሮች በዝቅተኛ ክብደት ምክንያት የሚከሰቱ የጤና እክሎች እንደሆኑም ሃኪሙ ተናግረዋል፡፡



ዝቅተኛ የሰውነት ክብደት ያላቸው ሴቶች ለመሃንነት የተጋለጡ ናቸው የሚሉት ዶ/ር ፋሲል፤ ምክንያቱን ሲገልጹም በሰውነት ቅባት ውስጥ የሚገኘውንና ለመራቢያ ሆርሞኖች ወሳኝ ግብአት የሚሆነውን ነገር ስለሚያጡ ነው ብለዋል፡፡ “ቀጭን ሴቶች በሰውነታቸው ውስጥ የሚገኘው ቅባት (ፋት) እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ቅባት ደግሞ ለመራቢያ ሆርሞኖች መኖሪያ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህም ከሲታ ሴቶች እነዚህን ሆርሞኖች በበቂ መጠን ለማቅረብ ስለማይችሉ የመፀነስ እድላቸው እጅግ የመነመነ ነው፡፡”

እነዚህን ችግሮች አልፎ ፅንሱ ቢፈጠር እንኳን በተለይ በፅንሱ የመጀመሪያ ወራት አካባቢ ውርጃ መከተሉ አይቀሬ ጉዳይ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተዛባ የወር አበባ ዑደት፣ የደም ማነስ፣ ደም በበቂ ሁኔታ አክስጅንን በሰውነታችን ውስጥ እንዳያዘዋውር የማድረግ ችግር ሁሉ በዝቅተኛ የሰውነት ክብደት ሳቢያ የሚከሰት የጤና ችግር እንደሆነ ሃኪሙ ጠቁመዋል፡፡

ዝቅተኛ የሰውነት ክብደት ያላቸው ሴቶች፣በባለሙያዎች ምክር የታገዘ የአመጋገብ ሥርዓት በመከተል ክብደታቸው ወደ ትክክለኛው መጠን እንዲደርስ ማድረግ እንደሚገባቸውም ተናግረዋል፡፡ “ወገቧ ቸቦ አይሞላም” ሲበዛ ጤና ያቃውሳል ማለት ይኼው አይደለ?!

ፖለቲካ ከገፅ 3 የዞረ

ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል አለማለቱ ይገርመኝና ያስደነግጠኝ ነበር። አሉባልታ አገር እንደሚያፈርስ ሩዋንዳ ላይ አይተናል፡፡ አሉባልታ አሁንም በአገር ደረጃ የሚያሳስበኝ ነገር ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ወደ ፖለቲካ ሲገቡ የሚያስቡት ችግር የመታሰር፣ ከስራ የመባረር ወይ የሞት ጉዳይ ነው፤አሉባልታን እንደ ችግር ብዙም አይቆጥሩትም፡፡ እኔ 22 አመት በትግሉ አሳልፌያለሁ፤ እንደ አሉባልታ በትግሉ ውስጥ ከባድ ነገር የለም፡፡ ትግሉንም በከፍተኛ ሁኔታ የጎዳው አሉባልታ ነው፡፡

*ኢዴፓ የፓርቲዎች ህብረት፣ ውህደት---- የመሳሰሉ ስብስቦችን ለምንድን ነው ላለመቀላቀል የወሰነው?*

በማንኛውም ጉዳይ በተናጠል ከመሄድ መተባባር ይሻላል የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ ችግሩ ምንድን ነው-- ይሄ አስተሳሰብ በተለይ ወደ ፖለቲካ ስንመጣ፣ሊሰራ እንደማይችል፣ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን እንደሚችል ጥያቄ ማንሳት አይፈለግም። በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ ወይም ትችት ማቅረብም ከፍተኛ የፖለቲካ ስህተት ተደርጎ ነው የሚታየው። መተባበር ጥሩ ሀሳብ ነው፣ ግን በተጨባጭ ጉዳዩን እንለካው ከተባለ በተቃዋሚው ውስጥ የህብረት ጥያቄ፣ ትግሉን የጠቀመ ሳይሆን በጣም የጎዳ ነው ብዬ አስባለሁ፤ ባይኖር ይሻል ነበር፡፡ የህብረት ጥያቄ ባይኖር ኖሮ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁን ሁለት ወይ ሶስት ጠንካራ ፓርቲዎች ተፈጥረው እናይ ነበር። የህብረት ጥያቄ ትግሉን ለማጠናከር ከፈየደው በላይ በህብረት ስም አንዳንድ ግለሰቦች የራሳቸውን የፖለቲካ ተሰሚነት ወይም ተቀባይነት ለማግኘት የሚጠቀሙበት አጀንዳ ሆኖ ነው የኖረው፡፡ ህብረቱ ወይ የሚፈለግበትን አላሳካ ወይ በተናጠል የሚታገሉ ፓርቲዎች ራሳቸውን አጠናክረው እንዲያወጡ እድል አልሰጠም፡፡ እንዲያውም አንድ ጠንካራ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚችል ፓርቲ ሲፈጠር፣ ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ ያልቻሉት ነባር ፓርቲዎች፣ የዚያን ፓርቲ እንቅስቃሴ ማፈን የሚችሉበት ስልት ነው የታየው፡፡ ጉዳዩ መዘጋት የሌለበት ቢሆንም በደንብ መጤን ያለበት ነው፡፡ የእንተባበር ጥያቄ የድክመት መሸፈኛ ነው፡፡ ጠንካራ ህብረት ለመፍጠር መጀመሪያ ጠንካራ ፓርቲዎች መኖር አለባቸው፡፡ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል አንድ ላይ መቆም የሚለው አስተሳሰብም የተሳሳተ ነው፡፡ ለመተባበር የሚፈልጉ ቢያንስ መሰረታዊ ነገሮች ላይ መስማማት አለባቸው፡፡ ውህደት መፍጠር በራሱ ግብ አይደለም፡፡

*ተቃዋሚዎች እርስበርሳቸው፣ እንዲሁም ከገዢው ፓርቲ ጋር ያላቸውን ውዝግብ እንዴት ያዩታል?*

በኔ እምነት ትግሉን በጣም የሚያዳክመው በራሱ በተቃዋሚው ጎራ ያለው ችግር ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ስልጣኑን መልቀቅ አይፈልግም፣ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥሩ አመለካከት የለውም፤ስለዚህ የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲዳከሙ የቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ እንደዚህ አይነት ባህርይ ያለው ገዢ ፓርቲ እንዳለ እናውቃለን፡፡ የኛ ጥንካሬ የሚለካው ይህንን ተፅዕኖ ተቋቁመን በመውጣት ነው፡፡ ልንፈትነው እንዳንችል ያደረገን የውስጥ ችግራችን ነው፡፡ ክፋቱ ግን አብዛኛው ተቃዋሚ ይህንን አያምንም፤ ሁልጊዜ በውስጡ ያለውን ችግር ውጫዊ አድርጎ ነው የሚያቀርበው፡፡ ከምንሰራው ድርጅታዊ ስራ ይልቅ ትኩረት የምንሰጠው ለፕሮፓጋንዳ ነው፡፡ ራሳችንን የመገምገም ባህርይ የለንም፣ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አሰራር ነው የምንከተለው፡፡ ገዢው ፓርቲ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲን አላመጣም እንጂ ራሱን በደንብ የሚገመግምበት ዲሞክራሲያዊ አሰራር አለው፡፡ ኢህአዴግ እያዳከመን ነው ሲባል ዞሮ ዞሮ የራስን ድክመት መናገር ነው፡፡ ችግሩ ከውጫዊው ይልቅ ውስጣዊ ነው፡፡ ራሳችንን እንገምግም ስትይ፣ ለኢህአዴግ ጥቅም እየሰራሽ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

*በዘንድሮ ምርጫ ይወዳደራሉ?*

ፓርቲዬ ይወዳደራል፤እኔ አልወዳደርም፡፡

*ከግንቦቱ አገራዊ ምርጫ ምን ይጠብቃሉ?*

ተቃዋሚው ያለበትን ሁኔታና የኢህአዴግን አካሄድ ሳየው፣ ካለፈው ምርጫ የተለየ ውጤት ይመጣል ብዬ አላስብም፡፡ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ ምርጫውን በራሱ ቁጥጥር ስር አድሮጎ እንደቀጠለ ነው፣ ተቃዋሚው ጎራም ካለፉት ስህተቶቹና ችግሮቹ ተምሮ ራሱን አጠናክሮ የተሻለ ውጤት ለመያዝ የሚያደርገው ነገር ብዙም የለም፡፡ ድፍረት አይሁንብኝና ተቃዋሚው ጎራ ያለችውን አንድ መቀመጫ አስጠብቆ ይቀጥላል ወይ የሚለው ያሳስበኛል፡፡ ሂደቱ መቀጠል ስላለበት ተሳትፎ ማድረጉ አስፈላጊ ቢሆንም በዚህ ምርጫ የኢትዮጵያን ዲሞክራሲ አንድ የተሻለ ደረጃ ላይ የሚያደርስ ውጤት አልጠብቅም፡፡ ይህ የግል ግምቴ ነው፣ ውጤቱን እናያለን፡፡

*በመጀመሪያዎቹ የትግል አመታት በጎጃምና ወሎ አዋሳኝ ቦታ ላይ ተጀምሯል የተባለ የትጥቅ ትግል ለማየት ወደ ገጠር ሄደው እንደነበር በመጽሃፉ ገልጸዋል፡፡ የትጥቅ ትግል ለመጀመር አስበው ነበር?*

ብዙ ሰዎች ባለፈ ታሪካቸውና አስተሳሰባቸው ያፍሩ ይሆናል፤ እኔ በግልፅ ነው ያስቀመጥኩት። በወቅቱ ያን አይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዲኖረኝ የቀረፀኝ ሁኔታ ነበር፡፡

ትግሉን በተቀላቀልኩ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወይም አራት አመታት የነበረኝ አስተሳሰብ በጣም አውዳሚ ነበር፡፡ በስልት ደረጃ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በማንኛውም መንገድ መወገድ አለበት ብዬ ነበር የማምነው፡፡ ይህን መንግስት ከስልጣን ለማውረድ ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነበርኩ፡፡

የወጣቶች ካውንስል አባል በነበርኩበት ወቅት ራስን አቃጥሎ በስርአቱ ላይ ያለውን ብሶት በማሳየት፣ ህዝቡን ማነሳሳት ይቻላል የሚል እምነት ነበረኝ፡፡

ከነፍሰገዳይ ጋር የትጥቅ ትግል አለ በሚል የሄድኩትም በዚያ ምክንያት ነበር፡፡ አሁን ላይ ሳየው ስህተት ቢሆንም ተምሬበት ያለፍኩበት ነው፤ እኔ ይህን ያደረግሁት ከአስራ አምስት አመት በፊት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሰላሳ እና አርባ አመት አሳልፈው፣እኔ ከዛሬ 15 አመት በፊት የነበረኝ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ይህ በጣም የሚያስገርም ነው፡፡







## ውሃ ከገፅ 5 የዞረ

በአደገኛነት የሚታይ ሰው ስለነበር ነው፡፡ ይህን ሚሥጥር በውይይታችን ወቅት እሱ ራሱ ባይነግረኝ ኖሮ አላውቅም ነበር፡፡ ሁኔታውን ከተገነዘብኩ በኋላም ቁም ነገሬም ብዬም አልተጨነኩበትም፡፡ ጉዞውን በመግባባት ጀምረን በመግባባት ጨረስነው፡ ፡ በመጨረሻ ግን አንዱ በቅርብ የሚያውቀኝ ጋዜጠኛ “ከዚህ አደገኛ ሰው ጋር ምን አጣበቀህ?!” ብሎ ነገር ጣል እንዳደረገብኝ አስታውሳለሁ፡፡ ከዚያም ወደ ዩኒቨርሲቲው ተመልሶ መደበኛ ተማሪ ሆነ፡፡ በ1960 ዓ.ም በብሔራዊ አገልግሎት ተልዕኮ አሶሳ ያስተምር ነበር። እዚያም ቤተመጻሕፍት አሰርቶ በዓመቱ አጋማሽ ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ መፅሐፍትንና የመሳሰሉ ነገሮች ለመለመን አዲስ አበባ መጣ፡፡ በሬዲዮም በጋዜጣም ሀሳቡን ካሳወቀ በኋላ በግል ለሚያውቃቸው ሰዎች ስልክ እየደወለ እርዳታ ይጠይቅ ስለነበረ እኔን በዚህ እንድሳተፍ በጠየቀኝ መሰረት አንድ ቀን ወደ ሬዲዮ ጣቢያው ይዤው መጣሁ፡፡ በየቢሮው እየገባን መፅሐፍትና የመጽሐፍት መግዣም ገንዘብ ከየግለሰቦች ስንሰበስብ ቆየንና በመጨረሻ ከጣቢያው ኢትዮጵያዊ አማካሪ ቢሮ ገባን፡፡ አስተዋወኩት፡፡ አማካሪውም ስለእርሱ ተግባር በጋዜጣ ማንበባቸውንና ብዙ የወንጌል ማስተማሪያ ኃይማኖታዊ መፅሐፍት ሊሰጡት እንደሚችሉ ቃል ከገቡለት በኋላ ለዚያ አካባቢ ህዝብ እንዲህ ያለውን ተግባር ለማከናወን ከመጨነቅ ይልቅ ወደ አባቱ አገር ሄዶ ቢሰራ የተሻለ ይሆን እንደነበር ነገሩት፡፡ ራሱን ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ ተቆጥቶ ምክራቸውን እንደማይቀበል ሲገልጥላቸው፡ - “እኔኮ አሁን በስምም በመልክም አውቄሃለሁ፤ የአቶ ረዳ ልጅ አይደለህም? ብርሃነ መስቀል ረዳ፡፡ ለዚህ ብዬ ነው እንዲህ የመከርኩህ” አሉት፡፡ ቃል የገቡለትንም መፅሐፍ እንደማይቀበል ነግሮአቸው ተከታትለን ወጣን፡፡ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላም ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ አየር መንገድን አውሮፕላን በጠለፋ አስገድደው ከወጡት ሶስት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ሆነ፡፡ በኋላም ከኢ..ሕ.አፓ መሥራቾችና መሪዎች አንዱ ነበር ይባላል”፡፡

ይህን የማውቀውን ታሪክ በአዕምሮዬ ይዤ ነበር ወደ ጉብኝቱ ያመራነው፡፡ ጓጉቻለሁ፡፡ ብርሃነ የእኔ ትውልድ ሰው ስለሆነ ነው መሰለኝ ስስ (sensational) ሆኛለሁ፡፡ በዚያን ዘመን የብርሃነ መስቀል ተማሪ የነበሩ አቶ ስንታየሁ ቀልቤሳን በስልክ አግኝቻቸው ደግሞ እንዲህ ብለውኛል፡-

“ያኔ ተማሪው ነበርኩኝ፡፡ ሂሳብ ተማሪ ነበርኩ” አሉ፡፡

“አቶ ስንታየሁ ማን ልበል?” አልኳቸው፡፡

“ቀልቤሳ” አሉኝ፡፡

“የት ት/ቤት ነው?”

“አሶሳ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ነው የሚባለው፡ ፡ ብርሃነ መስቀል ረዳ እዛ አስተማሪ ነበር፡፡ ይወደኝ ነበር፡፡ መጽሐፍት ቤቱን ከማቋቋሙ በፊት ብዙ ዓይነት ውጣ ውረዶች ነበሩበት! ከሰራው በኋላ መጽሐፍ አጠረው፡፡ ወደ ክልል አካባቢ፤ ወደ ለቀምት ... አምቦ ሄዶ መጽሐፍ ይለምን ነበር፡፡ አጠራቅሞ ነው ተማሪዎቹ ዕውቀት እንዲቀስሙ ያደረገው፡፡ ...ዘወትር አፍሮ ፀጉር የነበረው ብርሃነ መስቀል ጎበዝ ነው፤ ታታሪ ነው ... ቤተ መጻሕፍቱ ዛሬ ደህና ብቅ ብሏል!”

“ማን ያስተዳድረዋል?” አልኳቸው

“ራሱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቱ ነዋ!”

በብሔር ብሔረሰብ በዓል ምክንያት ይመስለኛል እንደ ብዙ መ/ቤቶች ሁሉ የብርሃነ መስቀል መጽሐፍት ቤትም ተዘግቶ ደረስን፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሞ የለንም፡፡ አዘንኩኝ፡፡ ከብሔር ብሔረሰቦች በዓል ጋር በተያያዘ አንድ በአዕምሮዬ ያልጠፋ ነገር አለ፡፡ አንድ ዕለቱን በቅርብ የተከታተለ ወዳጄ ያጫወተኝ ትርዒት ነው፡፡ ከዘጠነኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ኅዳር 29 2007 ዓ.ም አከባበር አንዱ አካል የሆነው ዋንጫ የመረካከብ ሥርዓት ነው፡፡ ለሃያ ስድስት ቀናት በመኪና የተጓዘው ዋንጫ ወደ አሶሳ ሲመጣ፤ ምን የገጠማችሁ ነገር ነበር? ያልኩት ከሁለቱ ዋንጫ አምጪ አርቲስቶችና ማስታወቂያዎች አንደኛው “ህዝቡ በየወረዳው ዋንጫውን ካላሳደርነው ማለቱ ነበር ችግራችን!” ብሎኛል፡፡ ዋንጫው በመኪና ከመጣ በኋላ አሶሳ በዓሉ የሚከበርበት ግቢ ግን የገባው በተለየ መንገድ ነበር፡-

ዋንጫው የመጣው በሄሊኮፕተር ነበር፡፡ (ይሄ ፈጠራ ነው ያሉኝ አሉ) ዋንጫው የተንጠለጠለበት ገመድ አጠረ፡፡ ስለዚህ ዋንጫው መሬት አልደርስ አለ፡፡ ያለ ጥርጥር ሄሊኮፕተሩ ዝቅ ካላለ ዋንጫውን የሚቀበለው ሰው እጅ ውስጥ አይገባም፡፡ ስለሆኑም ሄሊኮፕተሩ ዝቅ ማለት ጀመረ፡፡ ጉዱ እዚህ ላይ ነው! (ገደደ! የሚሉት ነው የሰሜን ወንድሞቼ! ) ሄሊኮፕተሩ ዝቅ ሲል የተኛ አውሎ ንፋስ ቀሰቀሰ! ግቢው በንፋስ ታመሰ፡፡ ከየቦታው ለበዓሉ ድምቀት የመጡት ቆነጃጅት የት ይግቡ? በየወንበሩ ሥር!! የኦርኬስትራው ኖታ ከስቴጁ አየር ላይ በረረ! ታዳሚዎች አንዱ አንዱን መሸፈን፣ ፊትና ፊት መከናነብ ግድ ሆነ! ዋንጫውን ተረካቢው ገመዱን ከዋንጫው ለማላቀቅ ከአቧራው እሽክርክሪት መታገል ነበረበት! ኋላም ሲያወራ “ጉድ ሆነናል እረ!” ነው ያለው!!

ትልቅ ዝግጅት ተደርጎ በትንሽ አለማስተዋል “ዕዳ ከሜዳ!” ሲያጋጥመው ማየት አሳዛኝ፣ አንዳዴም አስደንጋጭ ነው! ዋንጫውን በሄሊኮፕተር ማምጣት በእርግጥ ፈጠራ ነውን? አንዳንዶች እንደቀለዱት “በየብስም በአየርም” የተጓዘው ዋንጫችን!” ለማለት ነውን? ከሆነስ በቂ ዝግጅት ነበረውን? ምን ያህል ዋጋ አስከፍሎ ይሆን? “ለነገ ያብቃን ለማተቱ

ፍሬ ነገሩ ተውኔቱ!”

በሚለው በሐምሌት መራር ቋንቋ ልደምድመው! የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በደማመቀ ባህላዊና ዘመናዊ ዝግጅት አበቃ፡፡ የመለያያ ግብዣ ተደረገ፡፡ ያቺን አሶሳ፤ ከነቀርከሃዋ፣ ከነ አሾተሬ የሚባል ባቄላዋ፣ ከሚያገለግለው ክማ፣ ከነቄንቄስዋ (Lady's finger)፣ ከነከድከዴዋ፤ ከነሞቀ አየርዋ ... ተሰናብተን ወደ አዲስ አበባ ልናመራ፤ በአካልም፣ በመንፈስም ተዘገጃጀንና ፊታችንን ወደ አዲስ አበባ አዙረን ተኛን!

የካይሮ ጉዞዬ

ከአሶሳ ተመልሼ ብዙም ሳልቆይ ዓርብ እለት ስብሰባ አለ የሚል የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥሪ ፖስታ አየሁ፡፡ ከአስተባባሪዎቹ አንዱ ደውሎ ጉዳዩ ወደ ካይሮ ጉዞ ሊደረግ መሆኑንና ፓስፖርትና ፎቶግራፍ ማዘጋጀት እንዳለብኝና፤ ከ60ዎቹ ልዑካን አንዱ እንደሆንኩ አበክሮ ነገረኝ፡፡ በዛው ቀን ስለጉዳዩ የምታውቅ አንዲት የሥራ ባልደረባዬ ደወለችና “ነቢይ ብትሄድ ጥሩ ነው!” ብላ አፅንኦት ሰጠችው። “ከውሃ ወደ ውሃ ጉዞ መጣብኝ/መጣልኝ!!” አልኩ፡፡ ፓስፖርቴ አልታደሰም፡፡ ደሞም የት እንዳረኩት እንጃ! ለመዘገጃጀት አሰብኩ፡፡ አንድ ወዳጄን ስለጥንታዊቷ ግብፅ መፅሐፍ ስጠኝ አልኩት፡፡ አንባቢ ሰው ጥሩ ነው Ancient Egypt ጥንታዊቷ ግብፅ የሚል ቆንጆ መፅሐፍ አመጣልኝ! የግብፅን ነገሥታት ታሪክ ከዱሮ ትምርታችን እስካሁን ለማገናኘት መንገድ ጀመርኩ - የንባብ!

እንግዲህ ዋና ዋናዎቹ ጥያቄዎች በአዕምሮዬ መጡ፡-

1. የኢትዮጵ የፐብሊክ ዲፕሊማሲ ልዑካን ዓላማ ምንድነው?
2. የኢትዮጵያ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ልዑካን እነማናቸው? እንዴት ተመረጡ? ዕውነት ኢትዮጵያን ይወክላሉ ወይ?
3. ዓርብ ታሕሳስ 3 2007 በ8 ሰዓት የተጠራው ስብሰባ ፍሬ - ነገረ ምንድነው?
4. የሰኞ ጠዋት ታህሳስ 6 2007 ስብሰባስ ምን ፍሬ አፈራ?
5. የአጠቃላይ የካይሮ ጉዞ ፕሮግራም ዝርዝር ምን ነበር?
6. እኔና ተጓዦቹ እንዴት አየነው?

(ይቀጥላል)


BLUE MEDIA PRESENTS
HEINEKEN ★ BEERFEST
MEET THE HEINEKEN FAMILY
FEB 14 & 15 FROM 2PM - 11PM AT FLORAL TROPICAL GARDENS
- BEER - MUSIC - FOOD - ENTRANCE 50 BIRR
18+
Brought to you by
BLUE MEDIA
ABC
Please Drink Responsibly: Not for sale to persons under the age of 18

# የግብርና የቀረጥ ሳምንት እየተከበረ ነው

መንግሥቱ አበበ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ባለሥልጣን “ሁላችንም ኃላፊነታችንን እንወጣ!” በሚል መሪ ቃል ለ7ኛ ጊዜ የግብርና ቀረጥ ሳምንት እያከበረ ነው፡፡

ገቢ የህልውናችን መሰረት ስለሆነ ህብረተሰቡ ስለግብር፣ ታክስና ቀረጥ ያለውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ ርእሰ ጉዳዩ አድርጐ እንዲወያይባቸው ከጥር 23 እስከ የካቲት 1 ቀን የሚቆይ የአንድ ሳምንት መርሐ ግብር ቀርፆ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን የባለሥልጣኑ የትምህርትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ገልፀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አቶ ኤፍሬም መኮንን ለአዲስ አድማስ እንደገለፁት፤ የግብርና ታክስ ግንዛቤ ለመፍጠር የአንድ ሳምንት ትምህርት ይበቃል ማለት ሳይሆን ይህች አገር ማደግ ካለባት፣ የታክስ አሰባሰቧ መሻሻል አለበት፤ ህብረተሰቡም በግብር አሰባሰብ ረገድ ባጋጠሙ ችግሮች ዙሪያ በመነጋገርና በመመካከር ሁሉም የጋራ ኃላፊቱን እንዲወጣና መነጋገሪያ ርእስ እንዲያደርገው ለማስገንዘብ ነው ብለዋል፡፡

ባለሥልጣኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች ቀርፆ እየተንቀሳቀሰ ነው ያሉት አቶ አፍሬም፤ ከሚዲያ ተቋማት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ከወጣቶችና ሴቶች አደረጃጀትና አባላት፣ ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ ከመካከለኛ ግብር ከፋዮችና ከአነስተኛ ግብር ከፋዮች፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ አንቀሳቃሾችና ከጉምሩክ አስተላላፊዎች ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በግብር አሰባሰብ ረገድ የሰሯቸውን ክንውኖች የሚያሳይ ኤግዚቢሽን ጥር 27 የተከፈተ ሲሆን እስከ የካቲት 1 ይቆያል ተብሏል፡፡ በዋና ዋና የመዲናይቱ ጐዳዎች በመኪና ቅስቀሳ ማድረጋቸውንና ስለግብረና ቀረጥ ሳምንት በሚዲያዎች እንዳስተላለፉ፤ ክንውኑ በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ክልሎችም ከደንበኞቻቸው ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

400 ከሚደርሱ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ጋር ባደረጉት ውይይት፤ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እያደረገ ያለው የለውጥ ሥራዎች ጥሩ ቢሆኑም ይበልጥ መሻሻል እንዳለባቸው ጠቅሰው፤ የግብር ጉዳይ የሁላችንም ስለሆነ ባለሥልጣኑ ለህብረተሰቡ እየሰጠ ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና ቅስቀሳ ይበልጥ መጠናከር እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የስፖርት አዘጋጆች የአየር ሰዓት ገዝተው ስፖርት የሚተነትኑበትና ዲጄዎች ሙዚቃ እያሰሙ የሚውሉባቸው ኤፍኤም ራዲዮች ሞልተው ሳለ፣ ገቢዎች ባለስልጣንን የሚያህል ትልቅ መ/ቤት በሳምንት በቲቪ የ20 ደቂቃ፣ በራዲዮ የ30 ደቂቃ ፕሮግራም ብቻ ማቅረቡ በቂ አይደለም፤ ሰፊ የአየር ሰዓት ሊኖረው ይገባል በማለትም አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ከፍተኛ የሠራተኛ ጥሎ መውጣት (Turn over) ከሚታይባቸው መ/ቤቶች አንዱ የገቢዎች ባለሥልጣን መሆኑን የጠቆሙት ከፍተኛ ግብር ከፋዮች፤ ልምድ ያላቸው ሙያተኞች ሲለቁ አዲስ ማሰልጠን ጉዳት ስላለው መ/ቤቱ የሠራተኞቹን አያያዝ (ክፍያ፣ ጥቅማ ጥቅም...) እንዲፈትሽ፤ የሠራተኞች አገልግሎት አሰጣጥ ተመሳሳይ ስላልሆነ መ/ቤቱ ራሱን እንዲፈትሽ፤ የተመላሽ ገንዘብ ክፍያ መዘግየትም እንዲስተካከል ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

“ወደ ታክስ መረቡ የገባን አለን፤ ብዙ ነጋዴዎች ግን አልገቡም ስለዚህ የንግዱ ሜዳ ፍትሐዊ አይደለም፤ አዲት አራት ዓመት ያህል ስለሚዘገይ ወደኋላ ሄዳችሁ ወለድ ትጠይቁናላችሁ፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ተመሳሳይ ስላልሆነ ውስጣችሁን ብታዩ ጥሩ ነው፤ ...” በማለት በመ/ቤቱ ያዩትን ድክመቶች መጠቆማቸውን ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡

አወያዮቹ ለተነሱት አስተያየቶች ከመድረክ በሰጡት ምላሽ፣ በአገልግሎት አሰጣጡ ብዙ መሻሻሎች ቢኖሩም ድክመቶች እንዳሉባቸው አምነዋል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጡን የተሻለ ለማድረግ የእናንተና የሁሉም ደጋፍ ያስፈልገናል ያሉት አወያዮቹ፤ ማንኛውም ሰው አገልግሎት ፍለጋ ወደ ተቋሙ ሲመጣ ማሟላት የሚገባውን ግዴታዎች አሟልቶ መቅረብ አለበት፤ ያላሟላው ነገር ኖሮ አሟልቶ እንዲመጣ ሲነገረው “አገልግሎት አሰጣጡ ፈጣን አይደለም” ማለት አይችልም፡፡

በመ/ቤቱና በአገልግሎት ፈላጊዎች መካከል ግልፅነት ሊኖር ይገባል ያሉት ኃላፊዎቹ፤ ደንበኛን ያጉላላ፣ የሚለግም... ሠራተኛ ካለ መጠቆምና ማሳወቅ እንዳለባቸው ገልፀዋል። የኦዲት መዘግየትንና ወለድን በተመለከተ በሰጡት ምላሽ፣ በግብር ሕጉ መሰረት መጀመሪያ የሚደረገው አምንሃለሁ፣ የሠራኸውን ሳትደብቅ ክፈል የሚል ስለሆነ፣ ነጋዴው “እኔ ሰርቼ ያገኘሁት ይሄ ነው” ብሎ የሰጠውን እንደሚቀበሉ ተናግረዋል፡፡ ነጋዴው ያለበትን ግብር በትክክል ካሳወቀ፣ ኦዲት የሚደረገው በፍጥነትም ሆነ ቆይቶ ቢሆን ለውጥ እንደሌለው ጠቅሰው፣ ግብሩን አሳንሶ የከፈለ ሰው በኦዲት ሲደረስበት ግብራቸውን ለሚያሳንሱ ሌሎች ሰዎችም ማስተማሪያ እንዲሆን መቀጫው ከፍ ያለ ነው ብለዋል፡፡

ድርጅቱ ኦዲት ለማድረግ የሚያስጠረጥረው ደግሞ የተጋነነ ትርፍ ወይም የተጋነነ ኪሳራ ነው። የእኛም ሠራተኛ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ግብር ሲያሳንስ ወይም ከፍ ሲያደርግ ሕገ-ወጥነትን መከላከል የምንችለው በጋራ ስለሆነ ለመ/ቤቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል በማለት ኃላፊዎች ምላሽ እንደሰጡ ታውቋል፡፡

አንዳንድ ዓመታዊ ገቢያቸው ከ100ሺ በታች የሆኑ የ“ሐ” ነጋዴዎች፤ አገር ውስጥ ገቢ ግብር እየጫነብን መሥራት አቅቶናል፤ ከዚህ ኑሮ በሰው አገር ተሰድዶ መኖር ይሻላል በማለት የሚኮበልሉ አሉ ወይም አየር በአየር ሕገ ወጥ ንግድ ውስጥ የሚገቡ እየበረከቱ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላሉ ተብለው የተጠየቁት አቶ ኤፍሬም፤ እነዚህ ነጋዴዎች የሂሳብ ባለሙያ መቅጠር ስለማይችሉ የሽያጭ መዝገብ እንዲይዙ አይገደዱም፡፡ ግብራቸው የሚተመነው በግምት ነው፡፡ ግምት ደግሞ ከፍም ዝቅም ሊል ሰለሚችል ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡

ሰለዚህ “ግብር በዛብኝ” እያሉ ከማማረር የየእለት ሽያጫቸውን በደብተር መዝግበው ቢይዙ መ/ቤቱን ከማማረር ይድናሉ፡፡ ያለ አግባብ ግብር ተጣለብኝ የሚል ሰው በ10 ቀናት ወይም በ30 ቀናት ውስጥ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ ቢያቀርብ ይታይለታል፡፡ ብዙ ሰዎች ቅሬታ አቅርበው እውነታው ታይቶ ወደ ሥራቸው ተመልሰዋል በማለት አብራርተዋል፡፡

## ዛሬ አዲስ ቴሌቪዥን የ18 ሰዓት ቀጥታ ስርጭት ይጀምራል

### ከ100ሚ ብር በሳይ ወጪ ተደርጐበታል

መንግሥቱ አበበ

የአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ በአሁኑ ወቅት ዓለምና ትላልቅ (ሜትሮ ፖሊታንት) ከተሞች የሚጠቀሙበትን ኤክስ ፒ (XP) የተባለ የመጨረሻ ቴክኖሎጂ የተገጠመለት ትራንስሚተር ዛሬ በ11 ሰዓት በማዘጋጃ ቤት ግቢ በይፋ በማስመረቅ የ18 ሰዓት ቀጥታ ስርጭት እንደሚጀምር አስታወቀ፡፡

ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት የአዲስ ቴሌቪዥን ስርጭት፣ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባና አካባቢዋ ፋይዳቸው የጎላ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የ18 ሰዓት ስርጭት እንደሚጀምር የኤጀንሲው የትምህርታዊና ዶክመንተሪ ዘርፍ ዳይሬክተርና የምረቃው ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አበበ ያረጋል ገልጸዋል፡፡

አቶ አበበ፣ በሂደት ወደ መካከለኛ ምስራቅ አገሮችና ለዚች አገር ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች ስርጭቱ እንዲዳረስ ይደረጋል ብለዋል፡፡

መረጃ የሚገኘው ከህዝብ ነው፡፡ እኛ ደግሞ የምንሰራው ከህዝቡ ጋር ስለሆነ ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ ነን ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከሕዝቡ የሚያገኙትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እየተነተኑ ደረጃውን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል፡፡

ኤጀንሲው፣ የ18 ሰዓቱን ስርጭት ለመሸፈን በርካታ ዝግጅት በመደረጉ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች፣ ህብረተሰቡን እያዝናኑ የሚያስተምሩ ጉዳዮች እንደሚቀርቡ ጠቅሰው፣ በርካታ የአየር ሰዓት ለመዝናኛው ክፍል መሰጠቱን፣ በትምህርት ክፍል ዶክመንተሪና የምርመራ (ኢንቨስቲጌቲቭ) ጋዜጠኝነት ሥራ፣ እንዲሁም የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች እንደሚቀርቡ፣ በማህበራዊ ዘርፍ (በትምህርት፣ በጤና፣ በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በሕፃናት ..) ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ዘገባዎች ስራዎች እንደሚሰሩ አስታውቀዋል፡፡

በኢኮኖሚው ዘርፍ ልማትን ማስተዋወቅና የከተማዋን ገጽታ መገንባት፣ ... እንዲሁም የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በምርመራ ጋዜጠኝነት ካሜራቸውን ደግነውና ብዕራቸውን አሹለው እየተጠባበቁ መሆናቸውን ገልጸው፣ ህዝቡ በየትኛውም ክፍል የሚፈፀሙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን (ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ጉቦ፣ ሙሰኝነት፣ ...) እንዲሁም ከህዝብ አፍና ከመንግስት ነጥቀው ለግል ጥቅምና ብልጽግና የሚያውሉ ሰዎችን እንዲያጋልጡ ተማፅነዋል፡፡

ፖለቲካ፣ በህዝብና በመንግስት መካከል በምርጫ የሚደረግ ስምምነት በመሆኑና የህዝብና የመንግስት ሚዲያ በመሆናቸው፣ ህዝብ የመረጠውን መንግስት እንደሚያገለግሉ ጠቅሰው የዚያን መንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ... በማስተዋወቅ ህዝቡ እንዲፈጽማቸው ማድረግ ግዴታቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይህም ሲባል እኛ የምንሰራው ከገዢው ፓርቲ ጋር ብቻ ነው ማለት አይደለም ያሉት አቶ አበበ፤ አሁን የምንገኝበት ወቅት የምርጫ ቅስቀሳ የሚከናወንበት ጊዜ ስለሆነ፣ ማንኛውም ፓርቲ፣ ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ፖሊሲውን፣ ስትራቴጂውን፣ ሐሳቡን፣ ... ማቅረብ ስለሚችል የማናስተናግድበት ምክንያት አይኖርም ብለዋል፡፡

አዲስ ቲቪ፣ ቀጥታ ስርጭት መጀመሩን ምክንያት በማድረግ፣ ከትናንት በስቲያ በአዲሱ የአፍሪካ ህብረት አዳራሽ፣ “የህዝብ ግንኙነትና የሚዲያ ተቋማት በብሔራዊ መግባባት ስራ ላይ ያላቸው ፋይዳ” በሚል ርዕስ ሲምፖዚየም መካሄዱንና ከልዩ ልዩ የህዝብ አደረጃጀቶች የተውጣጡ ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎች መሳተፋቸውን አቶ አበበ ያረጋል አስረድተዋል፡፡

# “ጋላክሲ ኤስ6” በ2 ወር ውስጥ ገበያ ላይ ይውላል



የሳምሰንግ ኩባንያ ምርት የሆነውና የበለጠ ዘመናዊና አገልግሎቱን የተለየ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ተሻሽሎ የተመረተው ዘመናዊው ስማርት ፎን ጋላክሲ ኤስ6፤ በመጪው ሚያዝያ ወር መጀመሪያ ገበያ ላይ እንደሚውል ሲኤንኤን ዘገበ፡፡

ኩባንያው ላለፉት ስድስት አመታት ለገበያ ሲያቀርባቸው የቆዩት የጋላክሲ ኤስ ሞባይሎች ቀጣይ ምርት የሆነው ኤስ ሲክስ፣ በአጠቃላይ ሁኔታው ከቀደሙት የተለየ እንደሆነ ታውቋል፡፡

ሞባይሉ የተሰራበት ቁስ የተለየ ከመሆኑ በተጨማሪ የተሻሻለ ዲዛይን እንዳለው፣ የተመረጡ ሶፍትዌሮች እንዳሉትና በተለያዩ የቀለም አማራጮች ለገበያ እንደሚቀርብ ተነግሯል፡፡ ቅርጹ ከዚህ በፊት ከነበሩት የጋላክሲ ኤስ ምርቶች የተለየ እንደሆነ፣ ለአጠቃቀምም ምቹ በሆነ መልኩ እንደተመረተ የጠቆመው ዘገባው፣ ሞባይሉ በመጪው ወር በይፋ ተመርቆ ለእይታ እንደሚበቃና በሚያዝያ ደግሞ በገበያ ላይ እንደሚውል አክሎ ተጠቁሟል፡፡


ፊደል ከገፅ 8 የዞረ

ማወቅ ግድ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ቢቻልም ላለማንዛዛት ስም ተቆጥቤአለሁ፡፡ ሆኖም ይትባረክ ገሠሠ የሚባሉ ጸሐፊ፤ “ኪነጥበብ ሥነጥበብ ዘጠነኛ” በሚል ካዘጋጁት መጽሐፍ (ገጽ ሠ) ላይ ያሠፈሩትን በአጭሩ እጠቅሳለሁ፡፡ “በግዕዝ እግዚአብሔርን ለማመስገን የተለያዩ የክብር ቃላት አሉ፡፡ ባረከ፣ ቀደሰ፣ አእኰተ፣ ወደሰ፣ ሰብሐ...የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሁሉም አመሰገነ ማለት ነው፡ ፡...በዘፈቀደ የፈለግነውና የቀናንን ቃል ጐትተን አንጽፍም፡ ፡ ቦታ ቦታ አላቸው፡፡ የሚለዩትም በትምሕርት ብቻ ሳይሆን በልብ ስብራት ጭምር ነው፡፡” ሲሉ ገልፀዋል፡፡ እነዚህን ቃላት አማርኛም ይጠቀምባቸዋል፡፡ ስለሆነም ከፊደላቱ ውስጥ “ሰ፣ አ፣ ሐ” ቢቀነሱ ቀሪው ቃል “ባረከ” የሚለው ብቻ ይሆናል፡ ፡ ይህ ብቻ ደግሞ መንፈሳዊ ግንኙነታችንን በሙሉ ይወጣል ማለት አይቻልም፡፡ በተለዋጩ ፊደላት ደግሞ “ቀደሠ፣ ዐዕኰተ፣ ወደሠ፣ ሠብሀ ወይመ ሠብኃ” ብለን ብንጽፍ፣ ቃላቱ የሆሄ ጥርቅም እንጂ የሚታወቁ አይደሉም። በዚህና በቅንነት ታሪካችንን ጠብቆ ለመሄድ የሚያስችሉ ምክንያቶችን በመቀበል ፊደሉ ሳይሸራረፍ በእንክብካቤና በጥበቃ እንዲቀጥል ማድረግ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት እንደሆነ ማመን ይቻላል፡፡ መልካም ጊዜ፡፡

# እንኳን ደስ አላችሁ




በጥር 17 ሠርጋችሁን ላከበራችሁ
ኃይለየሱስ እና ዘላለም
እንኳን ደስ አላችሁ
እመቤትና ሳምሶን ብሩ



## ከአብደላ ዕዝራ

# ሒሣዊ ዳሰሳ ያልገቡኝ ነገሮች

ደረጀ በላይነህ

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ስለ ሀገራችን ስነ-ጽሑፍ፣ ይበልጡንም ስለ ሀገራችን ግጥም መውደቅና መዋረድ ሙሾ አሚሽተን፣ ነጠላ ዘቅዝቀን፣ ድንኳን ጥለን ተላቅሰናል፡፡ አንዳንዶቻችን ደግሞ ታምሚል እንጂ አልሞተም፡፡ ለግጥም የተወለዱ ችግኞቻችንን አረሞች ከነቀልንና ከኮተኮትን፣ ነገ ፍሬ እናያለን በማለት ለልቅሶ በተጣለው ድንኳን ውስጥ አበባ ነስንሰን፣ ዘንባባ ቀንጥሰን፣ የተስፋ ሽቶ ለማርከፍከፍ ሞክረናል፡፡

በተለይ ጋዜጦች፣ ይልቁንም አዲስ አድማስ ጋዜጣ በግጥም ዘውግ ላይ፣ ባልተልፈሰፈሰና የነገን አድማስ በናፈቀ ሁኔታ በጐ አስተዋጽኦ አድርጓል ቢባል ውሸት አይሆንም፡፡ "ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም"ና የኋላ እትሞችን ብንገላልጥ እውነቱን እናገኘዋለን፡፡ ምናልባትም አንዳንድ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሀን ለግብስብስ ጉዞ ምንጣፍ ሲያነጥፉ የተከላከልንበት ይኸው ጋዜጣ ነበር፡፡

አሁን አሁን ግን የዘመናችን ግጥሞች፣ በተለይ በቁጥር ጥቂት የማይባሉ ገጣሚያን ከብዙ አሰስ - ገሰስ ውስጥ እንደ ሰጐን አንገታቸውን አሠግገው፣ አንገት ከመድፋት ገላግለውናል፡፡ እንደ እኔ እንደ እኔ፣ አይኖቻችንን ጠራርገን ካየን፣ ከዚህ በፊት እያደነቅን ሰማይ ካደረስናቸው ገጣሚያን ጋር ሚዛን ላይ ብናስቀምጣቸው የላቀ አቅም ያላቸውን እናገኛለን፡፡ ለነገሩ የቱም ሥራ የሚለካው በየዘመኑ ዓውድ፣ ፍልስፍና፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን መሠረት አድርጐ እንደሆነ የምንስተው አይመስለኝም፡፡ ጥበበኛ ሁሉ የሚለካው በየዘመኑ ነው፡፡ ይህንን ጠበቅ የሚያደርገው ደግሞ እንግሊዛዊው ገጣሚ ጆን ድራይደን ነው፡፡ በድራይደን እምነት፣ እያንዳንዱ ዘመን የየራሱ የላቀ አእምሮ ባለቤት (ጂኒዬስ) አለው፡፡ ቻርልስ ዲከንስ በዚህ ዘመን ሚዛን ቢለካ፣ ቀሽም የሚያሰኙት ብዙ ነገሮች እንዳሉት ፀሐፊው አስቀምጠዋል፡፡ እርግጥ አንዳንድ ገጣሚያንና ደራሲያን፣ የክፍለ ዘመናትን ድንበር ጥሰው፣ በሌሎች ዘመን ላይ ኮከብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደ ኤሚሊ ዲከንሰን፣ በአፀደ ሥጋ በነበሩበት ዘመን ላይ ስማቸውና ሥራቸው ተዳፍኖ ከሞቱ በኋላ እንኳ ክፍለ ዘመን ይሻገራሉ፡፡

ወደ እኛ ጓዳ መለስ ስንል በኢትዮጵያ ሥነ - ጽሑፍ መድረክ ላይ ሥነ ጽሑፉን ለማገዝ ብቅ ካሉት ሰዎች ውስጥ አብደላ ዕዝራ አንዱ ነው። አብደላ የሚጣፍጥ ግጥማዊ ዜማ ያለው ብዕረኛ ነው፡፡ ምናልባትም ሳይዘረጥጥና ሳይቆነጥጥ በማባበል፣ችግኞችን ለማቅናት የመሞከር ዝንባሌ ያለው ፀሐፊ ነው ብል የሀቅን አጥር የዘለልኩ አይመስለኝም፡፡ በተለይ እንደ እኛ ሀገር ባለው የጋራ ባህል ትስስር ውስጥ ነገሮችን ከሥራ ጋር ከማያያዝ ይልቅ ተራና ሠፈራዊ ትርጉም በሚሰጥበት ሁኔታ ውስጥ አጐንብሶ ቅዝምዝሞችን በማሳለፍ ለውጥ ለማምጣት መሞከር ቀላል አይደለምና ጥረቱ ትልቅ ነው፡፡

ለአብደላ ይህንን ያህል ቄጠማ ከጐዘጐዝኩ በኋላ የዘነጋቸው የመሠለኝንና ምናልባት ውለው አድረው በሀገሪቱ ሥነ ጽሑፍ ላይ አደጋ ሊሆኑ ይችላሉ የምላቸውን ሥጋቶች ባነሳ ደስ ይለኛል። ይህንን ሥጋቴን አብደላን አግኝቼ ፊት ለፊት ብናወራው እመርጥ ነበር፡፡ ግን ደግሞ ሁላችንም ጊዜዎቻችን በእንጀራ ታሥረዋል፤ ሃሳቦቻችን በነገ ሩጫ ተወጥረዋልና በአንባቢያን ፊት ብናወራውስ? የሁለታችንም አደባባይ እንግዲህ ይኸው ጋዜጣ ነውና እነሆ፡-

ከሦስት ሳምንት በፊት ጥር 9 ቀን 2007 ዓ.ም የታተመውን ጋዜጣ ሳነብ፣ አንጋፋዎቹ፣ ወጣቶቹን ስለ መግፋታቸው የተነሣው ሃሳብ ምቾት አልሰጠኝም፡፡ እጅጉን ከነከነኝ፡፡ አብደላ ወጣቶቹን ይገፋሉ ብሎ የጠረጠራቸው እነማን ይሆኑ? ለመሆኑ እኛ ሀገር በግጥሙ ዘርፍ አንጋፋ የሚባሉት በሕይወት አሉ ወይ ብዬ ጠየቅሁኝ፡፡ ማን አለ? ገብሬ የለም፣ ደበበ ፀጋዬ፣ መንግስቱ ለማ፣ ዮሐንስ አድማሱ... የሉም፡፡ አንዳንዴ ኖረው በተወቃቀስን ሁሉ እላለሁ፡፡ መድረክ ላይ ሲያነቡ ባያቸው፣ ድምፃቸውን ብሠማ እናፍቃለሁ፡፡ ታዲያ አብደላ የሚገፉንን ሰዎች ከየት አመጣቸው ብዬ አሰብኩ። አሁን አንድ የቀረው ሰለሞን ዴሬሳ ይመስለኛል። እሱም በሰው ሀገር ስደተኛ ሆኖ ተለይቶናል፡፡ እንዲያውም አሁን አንጋፋ ሊባል የሚችለው ገጣሚ ነቢይ መኮንን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከዚያ ጐን ወንድዬ ዓሊ፡፡ አብደላ፤ "ወጣት ደራሲያን በዳበሳ እያደቡ የብርሃን ፈለግ አገኘን ብለው ምሁራን መከተል ይሻሉ፤ መገፍተራቸው ከአንጋፋው ራስ ወዳድነት ባሻገር አርቆ ያለማጤንም ህፀፅ ነው፡፡" ይላል፡፡

የቱ አንጋፋ የቱን ወጣት እንደገፈተረው አልገባኝም፡፡ ምናልባት የሌሉ ሰዎችን ሳናውቀው ወንጀለኛ እንዳናደርግ እፈራለሁ፡፡ የቀደሙትም እኮ የየአቅማቸውን ፅፈውልን አልፈዋል፡፡ ብዙዎቻችንም ልንበቅል የምንችለው በነርሱ ዘር ነው፡፡ እንደ እነ ኤስ.ቲ ኢሊየት፤ "በዳንቴ ግጥሞች ውስጥ በቅያለሁ"፣ እንደ ሩሲያዎቹ "ከጐግል ካፖርት ስር ተቀጥፌያለሁ" ማለት ባንችልም ቅሉ፣አንጋፋዎቹ ባለውለታዎቻችን መሆናቸውን አንድክድም፡፡

ባለፈው ሳምንት ቀድሞ ቅዳሜ በወጣው የአዲስ አድማስ እትም ላይ ደግሞ፣ አብደላ ምርጥ ብሎ የጠቀሳቸው ገጣሚያን ግራ አጋብተውኛል፡፡ መቸም ስለ ግጥምና ገጣሚያን ስናነሳ፣ አንዱ ከአንዱ የሚለይበትና የሚመጥቅበት የራሱ ሞገስና ግርማ እንዳለው ለአብደላ መንገር አያስፈልግም፡፡ የኤስኤች በርተንን "The Criticism of Poetry" ብቻ ያነበበ ሰው መልሱን በቀላሉ ያገኘዋል፡፡ ታዲያ አብደላ ለምን ዘነጋው? ይህ ዝንጋኤ የጐንዮሽ ጉዳት የለውም ወይ? ምናልባት አንዱ በሃሣብ ልቀት ቢበልጥ፤ ሌላው ከእርሱ የበለጠ የቋንቋ ልቀትና የምት፣ የተስማምና የመሳሰሉት መመዘኛዎች ሃይል ከፍታ ሲዘመን የበለጠ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ይህ አይነቱ ዳኝነት በርተን፤ "The hasty and uncritical reader then plunges into his judgment I like this!" እንዳለው ይሆናል፡፡ አሊያም ዶ/ር አይ.ኤ. ሪቻርድስ "First impressions differ widely and notoriously unreliable" እንዳሉት የስሜታዊ አንባቢዎች ዳኝነት ሊሆንብን ነው፡፡ በርግጥ የግጥም መለኪያዎች እጅግ ብዙና ውስብስብ መሆናቸውን ብዙዎቻችን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ሎውረንስ ፔረኔ እንደሚሉት፤ "...yet over a period of time the judgments of qualified readers tend to coalesce there comes to be more agreement than disagreement" ይላሉ፡፡ አንዳንዴ ግን ጥቂት የሚያከራክሩ አሉ፡፡ ለምሳሌ በውጭው ዓለም ለሼክስፒር ሶኔቶች ታላላቅ ምሁራን ሁሉ ሲያጨበጭቡ /ሳሙኤል ጆንሰንን ጨምሮ/ በጆንኪትስና በዶን፣ በቻውሰርና በወርድስወርዝ፣ በሼሊና በኤሌክሳንደር ፖፕ መካከል ግን ልዩነት ነበር፡፡ ግን ደግሞ እነዚህ የተጠቀሱት ገጣሚያን ከኪፕሊንግና ከሎንግፌሎው ከፍ ይላሉ የሚል ስምምነት አለ፡፡

ታዲያ እኛ ገጣሚያንን የምንፈርጅበት መለኪያ ምንድነው? አንዱን ከአንዱ ከፍና ዝቅ ስናደርግ የትኛው በምን ይበልጣል? በምን ያንሳል? የሚል ማሣያ ከሌለን የሚሻሻለው በምን ይሻሻል? አደረጃጀት፣ ቅጥንብር፣ ድምፀት፣ ዘይቤ፣ ተስማሞ - ሌላም ብዙ ነገሮች አሉ አይደል?

ይህንን ስል አብደላ ግድ የለውም ከሚል ዝንባሌ አይደለም፡፡ እንዳይዘነጋ ማሳሰብ ስላለብኝ እንጂ፡፡ አብደላ ለሀገራችን ስነጽሑፍ ከየትኛችንም ይልቅ ግድ እንደሚለው ከዚህ ቀደም የፃፋቸውን ሂሣዊ ዳሰሳዎች ማንበብ ብቻ በቂ ነው፡፡ ምናልባት አሁን ያለውን ሁኔታና የሰዎች ስነ ልቡናዊ አረዳድ አጢኖ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ግን ልብ ማለት የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ እውነት ለመናገር፣ አሁን ያለው ወጣት ለመነቃቃትና ለመበረታታት ከቀድሞው የተሻለና የመተጋገዝ አዝማሚያ ያለው ነው፡፡

አቶ አብደላ ላይ ሌላም የመዘንጋት ዝንባሌ ያየሁ ይመስለኛል፡፡ የዛሬ ሁለት ሣምንት የብሩክታዊት ጐሣዬ "ጾመኛ ፍቅር" ላይ በሠራው ሂሣዊ ዳሰሳ ላይ ምናባችንን የሚያስጐዘጉዙ ወንድ ገጣሚያንን ስም ዝርዝር ከጠቀሰ በኋላ ከሴት ገጣሚያን አንድ ሁለቱ ስማቸው እንደተጠቀሰው ገጣሚያን እንዲያስደንቁን መናፈቁን ነግሮናል፡፡ አብደላ፤ እዚህ ቦታ፣ አሁንንና ወደፊትን ብቻ ያየ ይመስላል፡፡ ለመሆኑ ገጣሚ መቅደስ ጀንበሩና ሰዓሊና ገጣሚ ከበደች ተክለአብ በቀላሉ ይረሳሉ እንዴ? በምናብ ምጥቀት፣ በረጋ አደረጃጀት፣ በምትና ተስማሞ፣ በሸጋ ቃላት፣ ከሃሣብ ጋር ወጥተው በሚወርዱ ድምፀቶች ነፍሳችንን አስደንሰው፣ እምባችንን ጨምቀው አልረጩም እንዴ? የመቅደስ ጀንበሩን "ታቲሆያን" አንድ ሁለት ዐረፍተ ስንኞች እናስታውሳ፡-

*ስህተት ናት - በእርግጥም ስህተት ናት*
*መዘመሯ ላጥቢያ ለንጋት ማዜሟ*
*ከደንቡ እንዳትወጣ ወግ እንዳይቀርባት*
*ድምጽዋን ማስደመኗ ቃሏን ማስለምለሟ*
*ስታውቀው ላይነጋ ብርሃን ላይታያት*
*በጩኸት ላይነጋ ጨለማው ዓለሟ፡፡*

* * *

*ወፎቹ ሲያዜሙ ሰምታ ሲዘምሩ*
*ማለዳ ተነስተው ደፋ ቀና ሲሉ*
*የንጋትን መምጣት በደስታ ሲያበስሩ*
*ምስጋና መግለጫ አንሶባቸው ቃሉ*
*ሲወድቁ ሲነሱ ሲከንፉ ሲበርሩ*
*ሲፖሯሩጡ እያየች ከዛፍ ዛፍ ሲዘሉ፡፡*

በነገራችን ላይ የሥነፅሁፍ ምሁሩ ብርሃኑ ገበየሁ በአማርኛ ስነግጥም መጽሐፉ፤ ገጣሚ መቅደስ ጀንበሩን እንዲህ ይላታል፤ "በዘመናዊው ሥነግጥም በህለ - ህለ የቤት ዓመታት ስልት እጅጉን ከተዋጣላቸው ወጣትና ዘመናዊ ገጣሚያን አንዷ ናት፡" ይሄ ብቻ አይደለም፣ የቤት አመታቱ፣ ስልትና ሙዚቃዊ ቃና ሸጋ እንደሆነ ይመሠክርላታል፡፡ ተምሳሌታዊ ፋይዳውንም በአድናቆት ከፍ አድርጐ ያሞካሻቸዋል፡፡ ""ታቲሆዬ" በደቡብ ምዕራብ አፍሪካ የምትገኝ ዘማሪ ወፍ ነች፡፡ ግን ደግሞ በነፃነት ተምሳሌትነት በአፍሪካ የነፃነት ትግል ታላቅ ሚና የተጫወቱ ታላላቅ ሰዎችን ወክላ ተስላለች" በማለት ብርሃኑ የመቅደስ ጀንበሩን ሌላኛ ጥግ ያሰላዋል፡፡

እንግዲህ ይህ የተወሰነ ውበትና መልክ ነው፡፡ ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከብሉይ መጻሕፍት ሲሶ ያህሉ በግጥም የተፃፈ መሆኑን የነገረ መለኮት አዋቂዎች ይነግሩናል፡፡ ይሁንና ከዚህ ሲሶ ውስጥ ግን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያህል የሚደነቅ የለም። ይህ መደነቅ ከየት መጣ ካልን፣ ዋነኛው ሚዛኑ ከመልዕክቱ ሌላ የዘይቤያዊ ቃላት አጠቃቀሙ ነው። በለዋጭ አነፃፃሪና ሰውኛ ዘይቤዎች ልብን እያዘለለ የሚያስደንስ ሃይልም አለው፡፡ ምናልባትም ብዕሩን ኮከብ ተጋጭቶ እሳት ይወልዳል ብንለው ይመጥን ይመስለኛል፡፡ እውነት ለመናገር አንዳንድ ቦታ ቃላቱ ጡት ሲጠባቡ እናያለን!

በሌላ በኩል ግጥሞችን በየዝርያቸው ማየትም ያስፈልገናል፡፡ ከተራኪ ግጥሞች እንደሌሪክ ዓይነት ባህሪ ጠብቀን፣ ሃሣቡ ጥልቅ ነው፤ ብንል ተሣሥተናል፡፡ ምክንያቱም በባህሪ ሁለቱም የተለያዩ ናቸውና፡፡ ጋሽ ፀጋዬ ገብረመድህን ስለ ከተሞች የፃፋቸውንስ ምን ልንል ነው? (ሃሣቡ ሲደንቅ ልንል?!)

ሃሣብ ብቻውን ግጥም አይደለም፡፡ ጥሩ መጣጥፍም ሊሆን ይችላል፡፡ ሃሣብ ከቡና ቤትና ከሌሎች ቦታዎችም መልቀም ይቻላል፡፡ ግን ግጥም ያ ብቻ አይደለም፡፡ በሰንደል እግር ቃላት ብናቆማቸው ወዲያው ይወድቃሉ፡፡

ፐረኔ፤ "በሃሳብ ብቻ ግጥም አይሆንም፤ መጣጥፍ ነው" እንዳሉት ሁሉ፤ ዴጋስ የተባሉ ፀሐፊ ደግሞ "You can't make a poem with ideas you make it with words!" ብለዋል፡፡ የስነግጥም ምርምር መጽሐፍ የፃፉት ኤክስ ጄ. ኬኔዲም ይህንን ሃሳብ ይደግፉታል፡፡ "በዓለም ላይ እጅግ አስደማሚ

ዳሰሳ ወደ ገፅ 21 ዞሯል

# ወደ ነገ

**የፍቅር ወግ**

አሸናፊ መለሠ
(ashusheger@gmail.com)

ነገ፡-

ያራራቁንን መቶ ኪሎ ሜትሮች በፈጣኖቹ የመኪናው ጎማዎች ሽክርክሪት ስር እየጠቀለልኩ ወዳንቺ እከንፋለሁ፡፡ ናፍቆት ያሳበጠው ገላዬን ተሸክሜ እነዚያን የፎቅ ደረጃዎች መንታ መንታ እየተሻገርኩ በየእርምጃዬ ልክ ወዳንቺ እቀርባለሁ.......

የግንባሬን ላብ በክንዴ እየከላሁ፣ ያቀፍኩትን ስጦታ ለማበርከት እያመቻቸሁ፣ በኔና ባንቺ መካከል ያለውን ኮሪደር ጣጥሼ አልፋለሁ፡፡ የልቤን ፈጣን ምት ከቁብም ሳልቆጥር፣ ስለዛለ ገላዬ ላፍታም ሳላስብ፣ የውብ ገላሽን ማማርና የብቻ የጠረን ጣዕምሽን እያሰብኩ ድካሜን በናፍቆቴ አጣፋዋለሁ .......

እጣዬን የሚመስለኝን ቀዩን በርሽን በጉጉትና በጉጉት ደጋግሜ አንኳኳለሁ ........

በሩን ቶሎ አትከፍቺም ......

በዚህም፣ ልቤ በጉጉት ልትፈርጥ፣ ቀልቤ በርሃብሽ ጠኔ ሊደባይ ምንም አይቀረውም፡ ፡ በናፍቆትሽና በሰቀቀንሽ ሲኦል ውስጥ ለድፍን ሁለት ደርዘን ሰከንዶች ተነክሬ ከተሰቃየሁ በኋላ በሩን ትከፍቻለሽ ......... !

ከዚያስ?

ከዚያ ......

"ውይ በናቲ ሞት! አንተው ነህ እንዴ?!" ትይኛለሽ - በልጅሽ እየማልሽ፣ ክንፉን ተሰብሮ እንዳልተሰበረ ለማሳየት ባየር ላይ እንደሚንደፋደፍ አሞራ ሆነሽ ......

ያኔ ........ አይሻለሁ! .......

ታላቁ ቅላትሽ ከፍም እያምታታ፣ ከፀሃይ እያጥበረበረ ይንቦገቦጋል ..... ታላላቅ ጡቶችሽ በለበስሺው ፒጃማ ውስጥ ሆነው ፋፍተው ይታያሉ ..... ጠብደሎቹ ጭኖችሽ በተራመድሽ ቁጥር ዳሌሽን እያውረገረጉ ውስጤን በሙቀት ያጥለቀልቁታል ...... የሽንጥሽ ቅጥነትና ክበ'ት ምራቄን አድርቆ ጥምሽን ያረካልኝ ይመስል መቀነትሽን መሆን ያስመኘኛል ..... በዚህ መሃል አሎሎ አይኖችሽ የምስኪኖቹን አይኖቼን አከርካሪ በፍጥነት ሰባብረው የዕይታ አፅናፌን ከሽፋሽፍትሽ ዳርቻ በማንሳት በበርሽ ስር ምንጣፍ ላይ ይፈጠፍጡታል .....

ዕይታዬን እዚያው አርመጥምጬ ስረጋጋ፣ የአይኖቼን ብርሃን የእግሮችሽ ጣቶች ላይ አሳርፋለሁ ..... አቀላላቸው ..... አረዛዘማቸው ..... አደራደራቸው ...... አወቃቀራቸው ...... ሁሉ ነገራቸው ውብ፣ ውቦች ......

"እ......... አዎ ..... ደህና ዋልሽ ፀደይ! እ.... አብርሃም ነው እንዳደርስልሽ የላከኝ" እየተርበተበትኩ የያዝኩትን ያደራ ዕቃ አስረክባለሁ ......

"ውይ አብርሽዬ ... የኔ ጌታ! እሱ ግን ደህና ነው? ወይኔ ሲያም...ር! ውይ የኔ ቆንጆ፣ ባለፈው ስላወራሁለት እኮ ነው ዛሬ የላከልኝ! ምስኪን አብርሽ! ቆይ አሁኑኑ እደውልለታለሁ ....... አንተ አትገባም ታድያ?" ትይኛለሽ ....

"አይ ..... እቸኩላለሁ፤ ደህና ዋይ" ብዬሽ ለስንብት አይኖቼን ወዳይኖችሽ እልካለሁ ....

አይኖችሽ እኔን አያዩም፤ ይልቅ ከአለቃዬና ከባልሽ የተላከልሽን ስጦታ በፍቅርና በናፍቆት ሰክረው ያደንቃሉ ...... የቀኝ እጅሽ ውብ ጣቶች የስጦታውን ጆርባ ይደባብሳሉ ....... ውብ ጡቶችሽ የስጦታውን ደረት ከደረቶቻቸው ጋር ለጥፈው ለስጦታውና በስጦታው ይጨመቃሉ ...... የግራ እጅሽ ጣቶችም እንደቀኞቹ ሁሉ የስጦታውን ቀሪ ጆርባ ለማቀፍ ሲሉ የያዙትን የበር መዝጊያ ይለቁታል ...... ያ ደም መሳይ በራችሁም "ጥዝዝዝዝዝ ....." እያለ ሄዶ በበሩ መቃን ላይ በሚጠብቀው ሽንቁር ስር ምላሱን ይወትፋል ......

በሩ ይጋርድሻል፡፡

ያኔ ......

እኔ ......

በቀስታ የፎቁን ደረጃዎች መውረድ እጀምራለሁ።

# የመምህሬ ወልደ ዩሃንስ ቀልዶችና አሽሙሮች - ክፍል 2

ከጉማራ ዙምራ
zmtm1229@yahoo.com

*አራት ገበሬዎች አክሱም ጽዮን ሊሳለሙ ሲመጡ ቀዬአቸው ላይ አንዷት ጠብታ ዝናብ እንኳን ሳይጥል አክሱም ግን ከባድ ዝናብ ጥሎ ይቆያቸዋል፡፡*

*ጠላ ቤት ገብተው ሲያወጉ አንደኛው "እንደው ይሄ መድኃኔዓለምስ !! እንዳ ማሪያም አክሱም ወተት የሆነ ዝናብ ጥሎ ሲያበቃ እኛ መሬት ላይ ጠብ የምትል ዝናብ ይከልክለን?" ብለው ሲያማርሩ ምህረይ ጆሮ ውስጥ ጨዋታው ይገባል፡ ፡ ምህረይ መለስ አድርገው "እና እንደ እናቱ እንዲያያችሁ ትፈልጋላችሁ እንዴ?" አሉ ይባላል፡፡*

ባለፈው ሳምንት ጽሁፌ ማገባደጃ ላይ በቸር እንሰንብት ብለን እንደተለያየነው ይኸው በሰላም ቆይተን ለቀጣይ ክፍል ደርሰናልና ተመስገን ነው መቼስ ሌላ ምን ይባላል፡፡ የክፍል አንድ ጽሁፌ ላይ እንደገለጽኩላችሁ፣ የምህረይ ወልደ ዩሀንስ የህይወት ጉዞ እጅግ ፈታኝና መከራ የተቀላቀለበት፤ አሳዛኙ የህይወት እጣ ፈንታቸውን በጸጋ ተቀበለው ነገር ግን ከዚያ ክስተት በኋላ አብዛኛው ማህበረሰብ "እብደት" ብሎ የሚጠራው፣ የፍልስፍና ባለሙያዎች ደግሞ "ህሊናዊ ምጥቀትን ማረጋገጥ" የሚሉትን ዓለም መስርተው ለሶስት ዐስርት ዓመታት ዘልቀዋል፡፡

ህሊናዊ ምጥቀትን ማረጋገጥ ምን ማለት ነው? ቀላል የሚመስል ነገር ግን ጥልቅ የሆነ ሃሳብ ውስጥ ስዋኝ በአጋጣሚ ስለ ምህረይ ወልደዩሃንስ በተጻፈው መጽሀፍ ላይ የግል ምልከታውን በአጭሩ ያኖረ ሰው በግሌ አፈላልጌ አገኘሁት፡፡ አቶ ጎይቶም ገብሩ ይባላል፡፡ አክሱም ከተማ ተወልዶ ያደገ ሲሆን ምህረይ ወልደዩሃንስን ከልጅነት ጀምሮ ያውቃቸዋል። በፍልስፍና የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ አግኝቷል፡፡ "ፍልስፍና ዘ ካህሊል ጅብራን" የሚል መጽሀፍ በትግርኛ ተርጉሞ ለአንባቢያን እንዳደረሰ ነግሮኛል፡፡ ህሊናዊ ምጥቀትን ማረጋገጥ ምን ማለት ነው ? እንዴት ይረጋገጣል? ከፍልስፍና አንጻር እንዴት ይታያል? ከምህረይ ወልደዩሃንስ ህይወት ጋር የሚያገናኘው ነገር ይኖር ይሆን? የሚሉ እና ሌሎች ጥያቄዎችንም በቃለ መጠይቅ መልክ አቅርቤለት ነበር፡፡ የሰጠኝን ምላሽ ለጽሁፍ በሚመች መልክ አቅርቤዋለሁ፡፡

እብደት የተለያዩ መገለጫዎች ሊኖሩት ይችላሉ ይላሉ አቶ ጎይቶም፡፡ ከፍልስፍና አንጻር እብደት ማለት ምን ማለት ነው? ከምህረይ ወልደዩሀንስ የህይወት ታሪክ ጋር አያይዘው ቢያስረዱኝ? ብዬ ያቀረብኩላቸውን ጥያቄ ሲመልሱ፤ በመሰረቱ እብደትን በሁለት መንገድ ከፍለን ልናየው እንችላለን። አንደኛው የህሊናዊ ወይም የመስተሀለይ ምጥቀት የምንለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከህሊናዊ ዝቅጠት ጋር ልናያይዘው እንችላለን፡፡ የተለያዩ ፈላስፎች ስለ እብደት የተለያዩ ነገሮችን ብለዋል፡፡ ለምሳሌ ጀርመናዊው ፈላስፋ ፍሬድሪክ ኒቼ እንዲህ ይላል፡- "በመጀመሪያ እብደት ነበር። እብደትም ከዘላለማዊነት ጋር ነበር፡፡ እብደትም ዘላለማዊነት ነው፡፡" ስለዚህም እብደት ሁሌም ያለና ከእኛ ጋር የሚኖር እንደሆነ ነው የሚነግረን፡፡ በተጨማሪም ኒቼ "በቡድን ማበድ ወይም በቡድን ተደራጅተህ ማበድ በጣም የተለመደ ነገር ቢሆንም ግለሰባዊ እብደት ግን ብዙም የተለመደ አይደለም" ይላል፡፡ በመሆኑም ይሄ ወደ ግለሰባዊ አስተሳሳብ ወይም Individual way of being ወደ ሚለው ሃሳብ ይወስደናል፡፡ ይሄን ጉዳይ ከምህረይ ጋር ስናያይዘው ሁለት ነገሮችን መውሰድ እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው እርሳቸው በህይወታቸው ላይ በደረሰው ከባድ ሀዘንና መከራ ምክንያት ህሊናዊ ምጥቀት ያረጋገጡ ሰው ስለሆኑ ወይም ከተለመደው አስተሳሰብና አካሄድ ወጣ ስላሉ፣ ህብረተሰቡ እብድ ብሎ ይጥራቸው እንጂ ህሊናዊ ምጥቀታቸውን ያረጋገጡ ሰው ነበሩ ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ነገር ግላዊ ህይወት ስለመምራት ፈላስፋዎች የተለያዩ ነገሮች የሚነግሩን በመሆኑ ከፍልስፍናዊ እይታ ጋር እያሰናሰልን ብንሄድ ጥሩ ነው፡፡ ፈላስፋዎች ይሄ ግላዊ ህይወትን ከሰዎች መንጋ ዓለም ጋር በማነጻጸር ይነግሩናል፡፡ ለምሳሌ ብዙ ሰዎች ራሳቸውን ከመንጋ ውስጥ ማጣት የሚመርጡበት የራሳቸው ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ኪርኪጋድ የተባለው ዴንማርካዊ ፈላስፋ ምን ይላል፤ "ሰዎች በቡድን ውስጥ ራሳቸውን ያጣሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ለምሳሌ አንዳንድ እንስሳት ራሳቸውን ለመከላከል ሲያስቡ አፈር ይቆፍሩና ራሳቸውን አፈሩ ውስጥ ለመደበቅ ይጥራሉ፡፡ ልክ እንደ እንስሳቱ የሰው ልጅም ከመንጋው ለመራቅ በሚፈልግ ጊዜ ራሱን አፈር ውስጥ ይደብቃል እንደማለት ነው" ይለናል ኪርኪጋድ፡፡ ይህም ማለት ሰዎች አንድን አመለካከት በቡድን ሲይዙት ምንም ችግር ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን አንድን አመለካከት በግለሰብ ደረጃ ማራመድ ስትጀምር ችግር ይሆናል። ምክንያቱም በጋራ የሚታሰብ አመለካከት ካለ ለግላዊ ህይወት አስጊ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ግላዊ ህይወት ከዚህ ወጣ ያለ አስተሳሰብ ስለሆነ ነው፡፡

ማርቲን ሀይድጋርድ የተባለው ጀርመናዊ ፈላስፋ እንደሚነግረን ከሆነ ደግሞ "የሰው ልጆች ግላዊ አስተሳሰብን መቀዳጀት ካልቻሉ፣ ሳያስቡት ወደ የሰዎች መንጋ ዓለም ይፈጠፈጣሉ ይላል፡፡ አንድን ነገር ሌሎች እንዳዩት ማየት ስንጀምር ነው ፍጥፈጣው የሚከሰተው፡፡ እናም በነዚህ የሰዎች መንጋ ዓለም ራሳቸውን በማጣት፣ እንደ አንድ ተግባራዊ ስራ እንደሚሰራ ቁስ አካል ይታያሉ" ይላል፡፡ በሰዎች መንጋ አለም ውስጥ ራሳቸውን ያጡና አንድን የጥበብ ስራ ወይም አካሄድ ሌሎች እንዳዩትና ሌሎች ሂስ እንደሰጡበት እይታ ያዩታል። ስለዚህ የመንጋው ደስታ የእነርሱ ደስታ ይሆናል፡፡ የመንጋውን ሀዘን የእነርሱም ሀዘን አድርገው ያዩታል ማለት ነው፡፡

ነገር ግን ግላዊ ህይወት ስንል ብዙ Existential Philosophers እንደ እነ ኒቼ፤ ኪርኪጋድ እና ከቅርቦቹም እንደ እነ ሀይድጋርድ እንደሚመርጡት "አንድ ሰው ግላዊ ህይወትን መምራት ካልቻለ በነጻነት ማሰብ ይሳነዋል" ብለው ስለሚያምኑ ነው። ሁለተኛው "የሰው ልጅ አንድ ነገር ከሌሎች ለየት ባለ መንገድ ለማየት ከፈለገ፣ ግላዊ ህይወቱን ነው መምረጥ ያለበት" ብለው ያምናሉ፡፡" ይህንን የፍልስፍና እይታ ወደ ምህረይ ስናመጣው ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ነው ጥያቄው፡፡ የምህረይ የእብደት ደረጃዎች አሉ፡ ፡ እርሳቸውን የሚያውቁ ብዙ ሰዎች እንደሚናገሩት ከሆነ፣ መጀመሪያ ዝምተኛነት ያጠቃቸው ነበር -Silence የምንለው ማለት ነው። ከዚያም ብቸኝነት ያጠቃቸው ነበር - Solitude የምንለው ነው፡ ፡ ሶስተኛው ደግሞ መጮህ፤ በነገሮች መሳቅና ማፏጨት የመሳሰሉትን ያደርጉ ነበር። እነዚህን ነገሮች ስናያቸው ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ለየት ብለው እንዲታዩ ያደረጓቸው መገለጫዎች ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ እነዚህ ድርጊቶች የህይወት ስቃይን ተጋፍጦ በማለፍ፣ ህይወትን እንደ ተራ ጨዋታ ነገር ቆጥሮ ኑሮን መቀጠል መቻል ሊባል ይችላል፡፡

ሌላው ምህረይ ስለ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ነጻና ግላዊ በሆነ መልኩ በሽሙጥና በአሽሙር መልክ ሂስ ይሰጡ ነበር። ክላውድ ሳምነር የተባሉ በኢትዮጵያ ፍልስፍና ላይ ሰፊ ምርምር ያካሄዱ ሰው "የቅኔ ትምህርት ለኢትዮጵያ ፍልስፍና መሰረት ነው" ብለው ያምናሉ። (ምህረይ የቤተክህነት ትምህርት ጎጃም ድረስ ሄደው እንደተማሩ-የባለፈው ጽሁፍ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ) ለምን ቢባል "የቅኔ ትምህርት ተማሪዎች ነጻ በሆነና ግላዊ በሆነ መንገድ የማሰብና የመመራመር እድል ስለሚፈጥርላቸው፤ ቅኔ የፍልስፍና መነሻ ምንጭ ነው" ብለው ያምናሉ፡፡ እናም ምህረይ ከቅኔ ትምህርት ባገኙት እውቀት መነሻነት ግላዊ የሆነ አስተሳሰብ፤ እይታ እና ሂስ እንዲሰጡ አግዟቸዋል ሊባል ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ብዙ ፈላስፋዎች እንደሚስማሙበት፤ የሰው ልጅ ግላዊ የሆነ አስተሳሰብ ማበጀት ካልቻለ በስተቀር (የቡድንን አመለካከትና አስተሳሰብ የሚደግም ከሆነ) አስተሳሰቡ ፍልስፍናዊ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ምህረይ ቀን እንደ እብድ ሲጮሁ ውለው ሌሊት ደግሞ ቤ/ክ ሲጸልዩ ያድሩ ነበር፤ ይሄን እንዴት ትመለከተዋለህ ወይም ከምን የመነጨ ነው? ብዬም ጠይቄው ነበር፡፡

እንግዲህ ምህረይ ሁለት የተለያዩ ሰብእናዎች/ dual personalities/ እንደነበራቸው ከልጅነቴ ጀምሮ ሳስተውለው የነበረ ነገር ነው፡፡ እናም ምህረይ በሶስት መንግስታት ስርአት ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው ቀን ላይ በተለመደው አነጋገር እንደ እብድ ሆነው ህብረተሰቡን፤ ያለውን መንግስትን ሲወርፉ ውለው፣ ሌሊት ደግሞ ልክ እንደ ሌላው ካህን ሙሉ ሌሊት ቆመው የክህነት አገልግሎት ሲሰጡ ማደራቸው ሁለት የተለያዩ ሰብእናዎች ባለቤት እንደነበሩ አመላካች ነው፡፡

ምህረይ ሽሙጣቸው፤ ሂሳቸው ከባዶ የመነጨ አይደለም፡፡ በአስከፊው የአንበጣ ወረርሽኝ ምክንያት ቤተሰባቸው ለረሀብ በመጋለጡ፣ ቤተሰቤን አተርፋለሁ ብለው ስደትን መርጠው ወጥተው ነበር፡፡ ነገር ግን ሶስት ልጆቻቸውንና ባለቤታቸውን በአስከፊው የተስፋ ምድር ፍለጋ ጉዞ ምክንያት አጥተዋል፤ መሬታቸው ተዘርፏል፤ ተወስዷል፤ ፍርድ ቤት ሄደው መሬታቸውን ለማስመለስ ቢጠይቁም ምላሽ አላገኙም፡፡ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተደራርበው በፈጠሩባቸው ጫና ምክንያት ዝምተኛነት፤ ብቸኝነትና ማፏጨትን ያዘወትሩ እንደነበረ ይነገራል፡፡ በዚህም ምክንያት ራሳቸውን ለማጥፋት "ማይ ሹም" በሚባል ሃይቅ ውስጥ እስከ መግባት የደረሱበት ሁኔታ እንደነበር መጽሀፉ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተቃራኒም ህይወትን እየወረፉ፤ እየተቹ፤ እያሄሱና እየቀለዱ መኖር እንደሚቻል ባለሙሉ ተስፋ እንደነበሩ መረዳት እንችላለን፡፡ እዚህ ላይ ፍሬድሪክ ኒቼ ያለውን መጠቀስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ "ህይወትን ተስፋ ከመቁረጥና ካለመቁረጥ ባሻገር ማየት መቻል አለብን" ባይ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ከቻልን ብቁ ሰው ለመሆን አያዳግተንም ይላል፡፡ እናም ምህረይ ይህን ያረጋገጡ ሰው ነበሩ ለማለት እንደፍራለን፡፡ ነጻ ህሊናዊ አስተሳሰብ ለማረጋገጥ የቻሉ ነበሩ፡፡ ይህን ሁሉ መከራና ስቃይ ተቋቁመው ራሳቸውን ወይም ህይወታቸውን ማስቀጠል የቻሉ በጣም ቆራጥ ሰው እንደነበሩ ከህይወት ታሪካቸው ማረጋገጥ እንችላለን።

ሌላው መታለፍ የሌለበት ነገር ምህረይ ራሳቸውን እንደ አንድ ተራ ሰው ሳይሆን ልክ እንደ አንድ ታላቅ ንጉስ የሚመለከቱ ሰው ነበሩ፡፡ ራሳቸውን ሲጠሩ እንኳን "ወልደዩሀንስ ንጉስ" እያሉ ነበር፡፡ ለዚህም ይመስለኛል የአስተሳሰብ፤ የመናገርና የአመለካከት ነጻነት ብቻ ሳይሆን የቦታ ነጻነት (Freedom of Space) ይፈልጉ የነበረው፡፡

እኚህ ሰው የሰዎችን የነፍስ ፍላጎት በቀላሉ የማንበብ እና የመረዳት ችሎታ ነበራቸው፡፡ ለምሳሌ በፍጹም እንዲቀርቧቸው የማይፈልጓቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ ምናልባትም የሰው ልጅ ደመነፍሳዊ ፍላጎትን በቀላሉ ማንበብ የሚችሉ ሰው ስለነበሩ ይመስለኛል። ፈላስፎቹ "Beastly Man ብለው የሚጠሩትን ግማሽ ሰው ግማሽ አውሬ ሰብእናን እንደማለት ነው። እናም የሰው አውሬ ባህሪውን በቀላሉ መረዳት የሚችሉ ዓይነት ሰው ነበሩ፡፡

እርሳቸው ህሊናዊ ምጥቀትን ያረጋገጡ እንደመሆናቸው ሌሎች እብዶችን (ወደ ህሊናዊ ዝቅጠት የተፈጠፈጡትን) ይጠየፉና ይሸሹ ነበር። በተለይ ሴት እብዶችን ሲፈሩ አይጣል ነበር፡፡ በመጽሀፉ ላይ ሴት እብዶችን ለምን እንደሚፈሩ አንድ ሰው ሲጠይቃቸው፤ "ኧረ ተወኝ ወንድሜ፤ ሴቶች ሲያብዱ ደግሞ የምራቸውን ነው፡፡ እንደኛ ለስለስ ያለ አይደለም፡፡ ያከሩታል፡፡" ብለውታል፡፡ በአሽሙሮቻቸው እንሰነባበት፡፡

**ካለነበባችሁን**

ምህረይ ከአንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ጋር በምርጫ ሰሞን ያወጋሉ፡፡

ምህረይ፡ "እኛን ምረጡ እያላችሁ ለምንድነው የምታደርቁን? ለመሆኑ ከሌሎቹ እናንተ በምንድን ነው የምትሻሉት?"

የተቃዋሚው ፓርቲ አባል፡ "እኛ ምሁሮች ነን፡፡ ብዙ መጽሀፍቶችን አንብበናል፡፡"

ምህረይ፡ "ምን ዋጋ አለው ብዙ መጽሀፍ

ቀልዶች ወደ ገፅ 21 ዞሯል

## የግጥም ጥግ

### ተጠየቅ

ታደሠ ለገሰ (ሀዋሳ)

ባንድነት ተዛምዶ....ያንድነት ተቃርኖ
አንድም በዝማሬ .........አንድም በ'ንጉርጉሮ
አንድም በዝማዌ..አንድም በአንባጓሮ
አንደዜም በብርዱ ......አንደዜም በግለት
አንደዜም በዘፈን.......አንደዜም በማህሌት
እንዲህ እኛ ና ኔ.....አንድም ሆነን ሁለት
ቀናና ጠምዛዛ .........ትጉና ነባዙ
ሐዘንም ይባቤ.......ጥፍጥፍ ጉምዛዛ
እራስና ግርጌ
ግርጌና እራስጌ
አዲስ እና አሮጌ..
በምኞት ትካዜ ከገባን ምናኔ
እኮ እኛ ማነን
ማነኝ እኛ ና'ኔ?!

## የአፋልጉኝ ማስታወቂያ

ወ/ሮ ሰላም ኃይለ ሰመረ፤ ልጆቻቸው ናሆም የማነ የ12 ዓመት፣ ሳሮን የማነ የ9 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ሲሆን ከአክስታቸው ከአክበረት ተስፋ ፂዮን ጋር የዛሬ 5 ዓመት ከቤታቸው እንደወጡ እስካሁን አልተመለሱም፡፡

እነዚህን ልጆች ያያችሁ ወይም ያሉበትን የምታውቁ፡-

በስልክ ቁጥር

0946-69-90-56 /0912-48-16-01

ብታሳውቁን ወሮታውን እንከፍላለን፡፡ ፈላጊ እናታቸው

ወ/ሮ ሰላም ኃይለ ሰመረ፡፡



## የምስራች!!!

### ለትዳር ፈላጊዎች በሙሉ

የትዳር አጋርዎን በምርጫዎ ማግኘት እንደሚችሉ ያውቃሉ

- ትዳር ሳይመሰርቱ እድሜዎ ቆይቷል
- ሲያልሙት የቆዩት የትዳር አጋር ማግኘት ይሻሉ

እንግዲያውስ በቅሎ ቤት ግሎባል ሆቴል ፊት ለፊት ወዳለው ቢሯችን ብቅ ብለው 3 ደቂቃ ባልሞላ ግዜ ውስጥ ፎርም ሞልተው የዘላለም የህይወት አጋርዎን፣ ይመኙት የነበረውን ተጓዳኝዎን በቀላሉ ያግኙ፡

**ወደ ቢሯችን ብቅ ሲሉ ሁለት ጉርድ ፎቶ መያዝዎን እንዳይዘነጉ፡፡**

እድሜዎ የቱን ያህል ድረስ ቢያልፍ፣ ድርጅታችን ለርሶ የሚሆን ውሃ አጣጭ በእግር በፈረስ ፈልጎ ያስገኝሎታል፡፡

ቀለም፣ ጾታ፣ ብሔር፣ እምነት ሳይለይ ሁሉንም በየዓይነቱ የትዳር አጋር ያስገኛል፡፡

**አድራሻችን፡-** ወደ ሳሪስ በሚያስኬደው መንገድ በቅሎ ቤት አካባቢ፣ ከግሎባል ሆቴል ፊት ለፊት አልፋ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 18 ነው፡፡

ስልክ፡- 0926-726297/0913-173971/0912-648858

# ልቻል ወይስ ልድፈር?

አጭር ልብወለድ

ደረጀ ይመር

ጉሮሮዬን በቀዝቃዛ ቢራ ለማርጠብ ወደ አንድ ምሽት ክበብ ደጃፍ ስደርስ አፍታም አልፈጀብኝም፡፡ ደጃፉን አልፌ ወደ ውስጥ እንደዘለቅሁ አንዲት እንስት አቀንቃኝ በታዳሚው የጋለ ጭብጨባ ታጅባ ወደ መድረኩ እየተውረገረገች ስትወጣ ተመለከትኩ፡፡ የቤቱ ኮከብ ዘፋኝ ትመስላለች፡፡ በእርግጥም ኮከብ ነች፡፡ ማይኩን ጨብጣ ተስረቅራቂ ድምጿን ስትለቀው አጃኢብ ነው፡፡ ድምጿን ስታወጣ ግብግብ የለም፡፡ ዝም ብሎ መስረቅረቅ ብቻ ...

ተሰጥዖን ሲያገኙ እንዲህ ነው፡፡ ተሰጥኦ ባለበት የትግል ዱካ ይሸሸጋል፡፡ ዶልፊን ውሃ ላይ ለመሰልጠን ክንፎቹን እና ጭራውን ዝግጁ ማድረግ ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡ ዝግጁ ሲሆን ይከናወንለታል፡፡ ልክ እንደ መተንፈስ፡፡ ጥረት እና ትግል ለተሰጥኦ ምኑም አይደሉም፡፡ እንስቷ ማቀንቀንን ስለወደደች ብቻ ሁሉም ነገር በቀና እየሄደላት ነው፡፡

አቀንቃኟን ትክ ብዬ ሳስተውላት ግን ግራ ሆነችብኝ፡፡ ድምጿ ወዲህ፣ ስሜቷ ወዲያ ሆኖ አጥበረበረኝ፡፡ ከፊቷ የሚነበበው ስሜት ድንዛዜ ነው፡፡ በስጋዋ ልግምና ላይ ተሰጥኦዋ ቢታከልበት ኖሮ መስረቅረቁን ውሃ በበላው ነበር፡፡ ግን አልሆነም፡፡ ከተራበ ጆሮ አንጀት የሚጠጋ ውብ ዜማ ከለገመው ገላዋ ላይ ማስወንጨፏን ቀጥላለች፡፡

ከየማዕዘናቱ የሚያስተጋባ፣ ባዶነትን ያረገዘ ቅላጼ አሁንም አሁንም እየወተወኝ ነው፤ ውትወታውን በጄ ማለት እንዳለብኝ ወሰንኩ፤ ስለ ውብ ቅላጼ ... ስለ ለገመ ገላ ... ስለ ዜመኛዋ ውስጠ ወይራነት ... ላወጣ ላወርድ ... ተነሳሳሁ፡

በእርግጥም ይህቺን ውብ ዜመኛ ከተጣባት ልግምና በስተጀርባ አንድ ጥላ አጥልቷል፡፡ ጥላው ለመኖር መታዘዝ ነው፡፡ የታዘዘችውን ካልከወነች እህል ውሃ ያከትማል፡፡ ተሰጥኦዋ ብልፅግና እንደተጠየፈ ይኸው እንዳለች አለች፡፡ ከተሰጥኦዋ የተረፋት ጥሪት ቢኖር ማገልገል ብቻ ነው፡፡ ታዛዥነቷ በተሰጥኦዋ ጉያ ውስጥ ተሸሽጎ ጎለመሰ እና ቀናት ቀናትን ሲወልድ ለአይን የሚያጠግብ ወደል ሆኖ ታያት፡፡ ለምሽት ክበቡ ማቀንቀን አህዱ ስትል፣ ከህሴት ጋር ጫጉላ ላይ ነበረች፡፡ ያኔ ታዛዥነቷን፣ አገልጋይነቷን ዞር ብላ የምታማትርበት አንገትን አልተቸረችም፡፡ ብታማትረውም ገና ከእቅፍ ያልወረደ ጨቅላ ስለነበረ ቁብ አትሰጠውም፡፡ ጥቂት አገልጋይነት ብዙ ደስታ ነበራት፡፡ በስኳር የተቀባ መራራ መድሃኒት፣ ስኳሩ እስከሚያልቅ መጣፈጡን ይቀጥላል፡፡ የስኳር መጠኑ ሲያልቅ፣ ለመራራው ጣዕም ቦታውን ያስረክባል፡፡ ስኳር አልቆባት ከመራራው ጋር እየተጋፈጠች ነው፡፡ ከንፈሬን መጠጥኩላት፡፡ አሁን ይህች አቀንቃኝ ለድፍረት ነው ለችሎታ እጅ ያጠራት?

"ምን ልታዘዝ?" የሚል የአስተናጋጅ ድምጽ፣ ለጥያቄው መልስ እንዳላፈላልግ ለጊዜውም ቢሆን ገታ አደረገኝ፤

የምጠጣው ቢራ ከጉሮሮዬ አልወርድ እያለ ቢታገለኝም፣ ለሞቅታ ብዙም ጊዜ አልፈጀሁም፡፡ ሞቅታዬ ግን ቅድም ብልጭ ያለብኝን ጥያቄ ማሸነፍ አልተቻለውም፡፡ ከድፍረት እና ከተሰጥኦ ማን ያስከነዳል? በእርግጥም ይህቺ ውብ አቀንቃኝ ከድፍረት ጋር ዓይን እና ናጫ ባትሆን ኖሮ እንዲህ በቢራ ለሚነፍዘው ታዳሚ ከመባከን አልፋ ለሀገር ምድሩ በበቃች ነበር፡፡ የአቀንቃኟ ሁኔታ ከበቀቀኗ ታሪክ ጋር ተገጣጠመብኝ፡፡ በቀቀኗ በታጠረላት ሸቦ (ኬጅ) ውስጥ ሆና ወዲህ ወዲያ ትበራለች፡፡ መብረር ተሰጥኦ ቢሆንም ከሸቦ ወሰን በላይ ፈቀቅ ማለት አልቻለችም፡፡ ሰማይ እየገመሰች መብረር ተክና፣ ክንድ በማትሞላ አጥር ውስጥ መንከላወሷ ምቾት ስላልሰጣት፣ የአድኑኝ ጩኸት ማሰማቷን ቀጥላለች፡፡ በጩኸቱ ልቡ የተነካ ደግ ሰው ወደ ሸቦው ተጠግቶ በሩን ከፈተና ወደ ሰማይ ለቀቃት፡፡ የተወሰነ ርቀት እንደተጓዘ ግን በድጋሚ ጆሮው የበቀቀኗን የአድኑኝ ጩኸት ይሰማው ጀመረ፡፡ መለስ ብሎ ወደ ኬጁ ሲጠጋ በቀቀኗ ልክ እንደ በፊቱ ከኬጁ ውስጥ ሆና እየጮኸች ነው፡፡ አሁን ግን የኬጁ መዝጊያ ወለል ብሎ ተከፍቷል፡፡ በቀቀኗን መርዳት ባለመቻሉ እያዘነ ተለያት፡፡ በቀቀኗ ከኬጁ ውጪ ያለው ህይወት ከማያውቁት መልአክ ሆኖባታል፡፡ ተሰጥኦዋን በሸቦ አጥሩ ልክ ገድባ መኖርን መርጣለች፡፡ በሌላ ጐን ደግሞ ደፋር መሰሎቿ በየዳሩ እንዳሻቸው እየከነፉ ከምንጩ ውሀ እየተጐነጩ፣ ከመስክ ላይ ጥሬ እየለቀሙ የሚኖሩት ኑሮ አስቀንቷታል፡፡ መብረር የሚችሉት ይቅርና ገና የተጐነደሸ ክንፍ ያላቸው ጫጩት በቀቀኖች ሳይቀሩ ከእርሷ በተሻለ ደፍረው ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ ይዘላሉ፡፡ የመብረር ተሰጥኦዋ ከጫጩቶቹ እጅግ ቢልቅም ድፍረት ስላነሳት ከእነርሱ በተሻለ በአደባባይ ልትታይ አልቻለችም፡፡

የእንስቷን አቀንቃኝ ተሰጥኦ ለማየት የታደሉት በምሽት ክበቡ ቅጥር ግቢ ውስጥ የታደሙት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ከቅጥር ግቢ ባሻገር ላለው ህዝብ ተሰጥኦዋ ባይተዋር ነው፡፡ ታዲያ እንዲህ አላላውስ ብሎ ቀፍድዶ የያዛት አባዜ ምንድን ነው? መፅሐፍ ቅዱስ የትጉህ እጅ አለምን ይገዛል ይላል፡፡ ይህ አባባል ለደፋሮች ቦታ የለውም፡፡ ደፋሮችም ለአባባሉ ቁብ አይሰጡም፡፡ ከትጋት ይልቅ ለብልጠት ይባትታሉ፡፡ ባትተውም አይቀሩም፤ በመጨረሻ ሲያሸንፉ ይታያሉ፡፡ የቀዬው አድባር ልቡ የሚሸፍተው ለሚደፍሩ እንጂ ለሚችሉ አይደለም፡፡ ጥያቄው ደፋር እንድሆን ማን ያስተምረኝ ነው? መልስ የለም፤ ከራስ ጋር ሙግቱ ቀጥሏል፤ የጠየቅሁት ጥያቄ እንደ ገደል ማሚቱ ተመልሶ ይሰማኛል፡፡

እንስቷ አቀንቃኝ መድረኩን ለሌላ አቀንቃኝ ለቃ ወርዳለች፡፡ ቅድም ክፍት ቦታ በብዛት ይታየኝ ነበር፡፡ አሁን ግን መፈናፈኛ እስኪታጣ ሁሉም መቀመጫዎች በታዳሚዎች ተይዘዋል፡፡ ከእኔ ቅርብ ርቀት ያሉት ቦታዎች በታዋቂ ሰዎች ምርኮ ስር ወድቀዋል፡፡ ታዳሚው ውስጡን በቢራ፣ አይኑን በታዋቂ ሰዎቹ ፊት እያጠበ መዝናናቱን ተያይዞታል፡፡ ታዋቂዎቹም ከታዳሚው ያገኙት ከልክ ያለፈ እንክብካቤ ሙቀት ጨምሮላቸው ልባቸውን እንደ ተራራ ቆልለዋል፡፡

"የደፋሮች ሀገር" ብዬ ከብርጭቆ ውስጥ የቀረችውን እንጥፍጣፊ ቢራ ወደ ጉሮሮዬ ላኳት፡፡

እነዚህ ባለ ጉንድሽ ክንፍ ደፋሮች ከእንስቷ አቀንቃኝ ሲነፃፀሩ መብረር ቢሳናቸውም እየዘለሉ መራቅ ችለዋል፡፡ ለተሰጥኦ እጅ ቢያጥራቸውም ለድፍረቱ ግን አልተቸገሩም፡፡ ለድፍረታቸው ምስጋና ይግባው እና ሁሉንም ዘርፍ እንዳሰኛቸው አክሮባት ይሰሩበታል፡፡ ለነገሩ የሚጠብቅባቸውን ግብር ነው ለአውደ ርዕይ ያቀረቡት፡፡ ባለተሰጥኦዎች ተሟልተው ወደአደባባይ እስኪወጡ ድረስ እጃቸውን አጣጥፈው ይቀመጡ ማለት ኢ-ምክናያታዊ ነው፡፡ "If you wait until you become perfect, you will wait forever" የሚለውን የፈረንጆቹን አባባል ከባለ ተሰጥኦዎቹ በተሻለ ደፋሮቹ ተረድተውታል፡፡ ባላቸው ጉንድሽድሽ ክንፍ ለመብረር ይሞክራሉ፡፡ ለሚያያቸው ሰው የሚበሩ ይመስላሉ፡፡ በመብረር ህግ ግን መሬት ለቀቁ እንጂ በረሩ አይባልም፡፡ ከእይታ ገሸሽ አሉ እንጂ አልጠፉም፡፡ የሀሳብ ትርምሱ ከቤቱ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ወርውሮ አውጥቶኝ ነበር፡፡ አሁን ወደ ቤቱ ተመልሻለሁ፡፡

ቤቱ ውስጥ የማየው ትእይንት ምንም ሰላም ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ ሁሉም የሚጠጣው የሚዝናናው አንዱ አንዱን እየጠበቀ ነው፡፡ ክብር እና ሞገስ ለሞቅታ እንኳን እጅ መስጠት አልቻሉም፡፡

ኪሴን ስዳብሰው ሚሸሿል፡፡ ብዙ ሳልሚሚቋ የያዝኳቸው የብር ኖቶች ጭዳ መሆናቸው ሰላም አልሰጠኝም፡፡ የቀበሌ መዝናኛ ውል አለኝ፡፡ እንደ እናት ጓዳ ያለስስት የሚቃመሱበት፤ በጥቂት የብር ኖቶች በርከት ያሉ ባለ አረንጓዴ እና ቢጫ ቦኖዎችን እጅ በእጅ የሚቀባበሉበት፤ ቦኖዎችን ተገን አድርጐ የከርስን ውትወታ በነፃነት አደብ የሚያስገዙበት፡፡ ሰዓቱ ባይገፉ ቀሪ የስራዬን ምስ እኔም እንደ ወዳጆቼ እዚያው ለማግኘት እንደረደር ነበር፡፡ ይህ ግን እንዳይሆን ምሽቱ ነጉዷል፡፡ ክበቦቹ ደርግ ላወጀው ሰዓት እላፊ ቃል አባይ ላለመባል በታማኝነት የፀኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ገራገር የብዙሃን ማጀቶች፣ "ሶሻሊዝም" ትቶ ያለፋቸው የህዝባዊነት ዳናዎች፤ ለአይን ያዝ እንዳደረገ ፍጥምጥ ማለትን ያውቁበታል፡፡ በእርግጥም ተፈጣጥመዋል፡፡ በእዚህ ሰዓት ወዴትም መላወስ የሚበጅ አይደለም፡፡ አንዱን ይገፏ አንዱን መጣሌን ቀጥያለሁ፤ ድንገት ከወለል ጋር የተሳሳመ የቢራ ጠርሙስ ከሰጠምኩበት የምናብ ንትርክ ጐትቶ አወጣኝ፡፡

ድፍረቱም ተሰጥኦውም ድብልቅልቅ ብለውብኝ ስምታታ ኖሬያለሁ፡፡ ልድፈር ወይስ ልቻል? አሁንም ጥያቄው አልተመለሰም፡፡

የፅድቁ መንገድ የትኛው ነው? የእንስቷ ወይስ የታዋቂ ሰዎቹ? የታዋቂ ሰዎቹን መንገድ ይሻለኛል ብል "የጭቦ ክህነት ይቅርብህ" የሚል ተግሳፅ አዘል ሀይለኛ ድምፅ በውስጤ ያስተጋባል ብዬ ፈራሁ፡፡

አይ የእንስቷን መንገድ ልከተል ብዬ ብደመድም "ባክህ ተሰጥኦ ለበቀቀኗም አልጠቀመ" እያለ የሚሳለቅብኝ መሰለኝ፤ ታዲያ ብችል ነው ብደፍር የሚሻለው፡፡

ላም እሳት ወልዳ አይነት ምርጫ ሆነብኝ፤ እንደምንም ጥሪት ቋጥሬ፣ የቢራ አምሮቴን ልቆርጥ ፈልጌ ካልጠበቅሁት የሃሳብ ጋጋታ ጋር ስፋለም አመሸሁ፡፡

የእንስቷ አቀንቃኝ ድምፅ ተመልሶ ተሰማኝ፡፡ ከቅድሙ በተዛነፈ ሁኔታ ለዘፈኑ የምትደረድራቸው ስንኞች ቤት የማይመቱ ስድ ንባቦች ሆነው ወደ ጆሮዬ ይንቆረቆራሉ፡፡ ተስረቅራቂ ድምጿን ከሞቅታ ጋር ስሰማው የጣር ድምፅ ሆኖ ውስጤን ሸነቆጠኝ፡፡ የበቀቀኗ የአድኑኝ ተማፅኖ በእንጉርጉሮ መልኩ የመጣ መሰለኝ፡፡ እባክሽ እህቴ ደፈር በይ፤ መቻል ለበቀቀኗም አልጠቀመ... ብዬ የሚከተለውን ስንኝ በመቋጠር ከቤቱ ውልቅ ብዬ ወጣሁ፡፡

ሀገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ
የቻለብሽ ቀርቶ የደፈረሽ በላ

## አዶት ሲኒማ ዛሬ ይመረቃል

በዓይነቱና በአደረጃጀቱ እጅግ ዘመናዊ እንደሆነ የተነገረለት 600 ተመልካቾችን የሚይዘው አዶት ሲኒማና ቴያትር አዳራሽ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና የኪነጥበብ ባለሙያዎች በተገኙበት ዛሬ ይመረቃል፡፡ ብስራተ ገብርኤል አካባቢ በሚገኘው አዶት ሕንፃ ላይ የተሰራው የሲኒማና ቴያትር አዳራሽ በዘመናዊ መሣሪያዎች የጥበብ ሥራዎችን ለተመልካች ለማቅረብ ዝግጅቱን ማጠናቀቁ ተገልጿል፡፡

## "ተስፋ ከጥበብና ሙዚቃ ጋር" ኤግዚብሽን ነገ ይከፈታል

ወላጆቻቸውን በኤችአይቪ ኤድስ ባጡ ህፃናት የተዘጋጁ የጥበብ ውጤቶች የሚታዩበት "ተስፋ ኪነጥበብና ሙዚቃ ጋር" የተሰኘ የኪነ ጥበብ ኤግዚቢሽን ነገ በ ‹አለ› ዲዛይንና የስነ ጥበብ ት/ቤት ግቢ ውስጥ ይከፈታል፡፡

የእስራኤል ኤምባሲ ከእስራኤሉ ሃዳስ ዩኒቨርሲቲ ኤንግልሃርድ፣ ከነፃ የጥበብ መንደር የአርቲስቶች ቡድንና ከአርቲስት ፎር ቻሪቲ ጋር በመተባበር ያሰለጠናቸው ወላጆቻቸውን በኤች አይቪ ኤድስ ያጡ ህፃናት ከመቶዎች በላይ ልዩ ልዩ የጥበብ ስራዎቻቸውን በኤግዚሽኑ ላይ እንደሚያቀርቡ ተገልጿል፡፡

"ተስፋ ከጥበብና ሙዚቃ ጋር የሚል ስያሜ በተሰጠው በዚህ ዝግጅት ላይ ህፃናቱ በተለያየ አይነት አቀራረብና አሳሳል የሳሏቸውን ስዕሎች እንደሚያቀርቡና ኤግዚቢሽኑም ለአንድ ሳምንት ለህዝብ ክፍት እንደሚሆን ኤምባሲው የላከልን መረጃ ያመለክታል፡፡

## ኪነጥበባዊ ዜና

ናፍቆት ዮሴፍ

### ልዑል ሲኒማ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

በሌላ በኩል ቦሌ መሰናዶ ት/ቤት አካባቢ በሚገኘው አናት ህንፃ 4ኛ ፎቅ ላይ የተከፈተው ልዑል ሲኒማ ሰሞኑን ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን የሲኒማ ቤቱ ባለቤትና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ልዑል አበበ ገለፁ፡፡ 400 መቀመጫዎችና 60 የቪአይፒ ወንበሮች ያሉት ሲኒማ ቤቱ፤ ዘመናዊ ሳውንድ ሲስተም እንደተገጠመለትና ወንበር መርጠው ትኬት የሚቆርጡበት አሰራር እንዳለው ባለቤቱ ተናግረዋል፡፡ ሲኒማ ቤቱ ሳምንቱን ሙሉ በቀን አራት ጊዜ ጥራታቸውን የጠበቁ የአማርኛ ፊልሞችን እንደሚያሳይና የራሱ ካፌና ሬስቶራንት እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

### "ፍንጃል ወግ" የግጥም መድበል ገበያ ላይ ዋለ

#### "ሥነ-አዕምሮ" መፅሀፍ ለንባብ በቃ




በገጣሚ በቀለ ፍቃዱ (ነሁቸር) የተፃፉ የግጥም ስብስቦችን የያዘ "ፍንጃል ወግ" የተሰኘ የግጥም መድበል ሰሞኑን ገበያ ላይ ውሏል፡፡ መድበሉ ከመቶ በላይ ግጥሞችን ያካተተ ሲሆን ግጥሞቹ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም በፍቅር ዙሪያ ያጠነጥናሉ ተብሏል፡፡ በ130 ገፆች የተቀነበበው መፅሀፉ፤በ19 ብር ከ50 ሳንቲም ለገበያ የቀረበ ሲሆን በቅርቡም "እንዶድ፣ ዘመቻና ዘመን" የተሰኘ ረጅም ልብ ወለድ ለንባብ እንደሚያበቃ ገጣሚው ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል በከተማ አድማሱ የተፃፈውና በሥነ - አዕምሮ ጤና ላይ የሚያተኩረው "ስነ-አዕምሮ" የተሰኘ መፅሐፍ ባለፈው ሳምንት ለንባብ በቅቷል፡፡ ለበጎ ስሜትና ለጤናማ አዕምሮ ባለቤትነት እንደ መመሪያ ያገለግላል የተባለው መፅሀፉ፤ የጭንቀትና የድብርትን እንቆቅልሽ የሚፈታና የአዕምሮ ጤና እውቀትን የሚያጎናጽፍ በመሆኑ ሁሉም ሊያነበው እንደሚገባ ተጠቁሟል፡፡ በአምስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ በ340 ገፆች የተቀነበበው መፅሀፉ፤ በ70 ብር ለገበያ መቅረቡም ታውቋል፡፡

### ሁለተኛው "የዘመራ ምሽት" ዛሬ በባህር ዳር ይካሄዳል

ግጥም በማሲንቆን ጨምሮ የተለያዩ የኪነጥበብ ዝግጅቶች የሚቀርቡበት ሁለተኛው "የዘመራ ምሽት" ዛሬ ማታ በባህር ዳር ካስትል ኩሪፍቱ ዋይን ሃውስ ውስጥ እንደሚካሄድ የፕሮግራሙ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ደምስ አያሌው ለአዲስ አድማስ ገለፁ፡፡ በምሽቱ 13 ግጥሞች በማሲንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንትና ከበሮ ታጅበው እንዲሁም ከጀርባ በተዋንያን ደምቀው እንደሚቀርቡ የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ በየግጥሞቹ መሃልም የጐጃም ባህላዊ ሰርግ ከሆማ ቆረጣ እስከ ብር አምባር በግጥምና በተውኔት እንደሚተወኑ ተናግረዋል፡፡ የኔልሰን ማንዴላ የጀግንነት ህይወት ላይ የሚያጠነጥን ግጥም እንደሚቀርብ ታውቋል፡፡

### የ"ሰው ለሰው" ድራማ አሸናፊዎች ነገ በሸራተን ይሸለማሉ

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቢሲ) ከሶስት ዓመታት በላይ ሲተላለፍ የነበረው የ "ሰው ለሰው" ድራማ አሸናፊ ተዋንያን በነገው ዕለት ከቀኑ 9 ሰዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ ይሸለማሉ፡፡ አሸናፊዎቹ ላለፉት ጥቂት ወራት በሞባይል አጭር መልዕክት ተመልካቾች በሰጡት ድምጽ መሠረት እንደተለዩ ተጠቁሟል፡፡ የሽልማት ሥነ ስርዓቱ በአራት ግብዣ ፕሮግራም እንደሚጠናቀቅ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በላከው መግለጫ አስታውቋል፡፡

# ከስድስተኛው ጣት የመነጨ ሃሳብ

## ተፈጥሮ ለጉልበት እንጂ ለፍቅር አታደላም

ሌሊሣ ግርማ

ቻርለስ ቡካውስኪ ከተፈጥሮ ጋር ታላቅ ቅራኔ ያለው ገጣሚ መስሎ ይሰማኛል፡፡ በአንድ ወቅት በገጣሚው ህይወት ላይ ያጠነጠነ ዶክመንተሪ መመልከቴ ትዝ ይለኛል፡፡ ዶክመንተሪው ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ቡካውስኪ የሚያነባት ግጥሙ አለች። ቃል በቃል ትዝ ባትለኝም በጥቅሉ ግን አንድ ድመት አንዲት እርግብን የሚበላበትን አሰቃቂ እውነታ የሚገልፅ ነው፡፡

በድመቱ ክራንቻ ተይዛ ጥቂት ህይወት ብዙ ሞት በሚነበብባት ቅጽበት ውስጥ የተመለከተው ገጣሚ ወፏን እንደ ፍቅር፣ ድመቱን ደግሞ እንደ ተፈጥሮ አድርጌ መመሰሉን ይገልፃል፡፡

“ተፈጥሮ ጤናማ (Normal) አይደለም፤ እግዜር ጤናማ አይደለም” ይላል፡፡ ድመት ወፍን መመገቡ ለማንም የሚገርም ነገር ባይሆንም፣ ለገጣሚው ግን መግረም ሳይሆን ሰቅቆታል፡፡ ምክንያቱንም ሲናገር “ሌላው ሰው የማይገርመው ራሱን በተከሰተው ትዕይንት ውስጥ ተክቶ ስለማይመለከት ነው” ይላል።

እውነትም ደግሞ፤ ሰው ራሱን የተለየ አድርጎ ስለሚያስብ የአውሬ ተፈጥሮ፣ የመብላት እና መበላት ትያትር...የሰውን ልጅ እንደሚመለከተው አያስብም። ግን ሰውን የሚበላው ደግሞ ሌላ ሰው ነው፡፡

ቡካውስኪ ብቻ ሳይሆን እኔም ተፈጥሮን እንደ ጤናማ የማልመለከትበት ጊዜዎች ብዙ ናቸው። በተለይ የተፈጥሮ ህግ በጉልበት እንደሚሰራ በማገናዝብበት ጊዜያት ሁሉ፡፡

ተፈጥሮ ጤናማ እንዲሆን በጉልበት የሚሰራ ህጉ በፍትህ መስተካከል ነበረበት፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ድመቷም እንደ እርግቡ ጥሬ ትልቀም ማለቴ ይመስላል፡፡ ትርጉም የማይሰጥ ነገር ነው፡፡ ለድመቱ ክራንቻን የሰጠው ተፈጥሮ ለእርግቧ ደግሞ ክንፍን ሰጥቷታል፡፡

ተፈጥሮ፤ “ጉልበት ያለው ርትዕ አለው” በሚለው ህግ የሚሰራ ከሆነ “ህገ ልቦና” ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ነገር ነው ማለት ይመስላል፡፡ በአምስቱ የተፈጥሮ ጣቶቻችን ላይ እንደተጨመረ ስድስተኛ ጣት፡፡

ገጣሚው ቡካውስኪ የእርግቧ መበላት ሲሰቀጥጠው፣ ራሱን እንደ ድመቱ ሳይሆን እንደ እርግቧ አድርጎ በመመሰሉ ምክንያት ነው፡፡ ጥፍር ሳይሆን ክንፍ የተሰጣቸው ሁሉ ወደ ተፈጥሮ ሳይሆን ወደ ፈጣሪ መቅረብ ነበረባቸው ብሎ ስለሚያምንም ሊሆን ይችላል፡፡ ተፈጥሮ የመጣው ከፈጣሪ ከሆነ፣ ድመትነት ከእርግብነት የበለጠ ወደ ፈጣሪ ይቀርባል፡፡ በይው በተፈጥሮ ህያው ሆኖ እንዲቆይ የሚፈለገው መሆኑ ነው፡፡ ተበይው የበይውን ህይወት ማስቀጠያ ነው፡፡

የተፈጥሮ ህግ በጉልበት ሲሰራ እንደዚህ ነው። ጉልበት ያለው ያሻውን ማድረግ መብቱ ነው፡፡ ድመቱ የርግቧን ክንፍ ነጭቶ ሊጫወትባት ይችላል፤ ወይንም ቸኩሎ ሊመገባት፡፡

የሰው ልጆችን በተመለከተ ቡካውስኪ የታየው እውነት፣ ከእርግብ እና ድመቱ ትራጀዲ የተለየ አይደለም፡፡ ሰውን ሌላ እንስሳ አይበላውም፡፡ ሰውን የሚበላው ሌላ ጉልበተኛ ሰው ነው፡፡ ህገ ልቦና (ስድስተኛዋ ጣት) የሰውን የእንስሳ ተፈጥሮ ልትለውጠው አትችልም፡፡ “ከእንስሳ የተለየህ ነህ” ብላ ማንነቱን ግን ልታድበሰብስለት ትሞክራለች። ሙከራዋንም ያምናል፡፡ ቢያምንም፤ እምነቱ ከእውነቱ አያስጥለውም፡፡

የሰው ተፈጥሮ ከእንስሳት የሚለየው መቀጠል መቻሉ ላይ ነው፡፡ ድመቱ ጥፍሮቹ ላይ ምንም መቀጠል አይችልም፡፡ ሰው ግን ጠመንጃ መቀጠል ይችላል፡፡ እርግቧ ክንፏ ላይ በተፈጥሮ ከተሰጣት ውጭ የምትጨምረው ነገር የላትም፡፡ ሰው ግን ሃይማኖትን ወይንም ጥበብን ይቀጥልበታል፡፡ መቀጠሉ ቱባ ተፈጥሮውን አይለውጠውም፡፡ ቱባ ተፈጥሮው ከአውሬ ጉልበተኝነት ብዙ አይለይም፡፡

ሰው መቀጠል ይችላል፡፡ በተፈጥሮው ላይ እምነት ይቀጥላል፡፡ በአምስቱ ጣቶቹ ላይ ስድሰተኛ ጣት፡፡ ተፈጥሮ “በፍቅር” ስለ መስራቱ የሚያሳምን ሃሳብ ሊያመነጭ ይችላል፡፡ ሃሳቡ ግን መልሶ ጉልበትን ለማደላደል ነው ጥቅሙ፡፡ በሃይማኖት ስም (ለፍቅር ሲባል) ጉልበትን በምእመናን ብዛት ያጠራቅማል። የእርግቧን ክንፍ ለብሶ የድመቱን ጥፍር ሲያወጣ ይስተዋላል፡፡ ፍቅርን በሀይል ለማስፈን ይጥራል፡፡ ጠመንጃም ያነግባል፡፡ በጠመንጃ ስም ፍትሀዊነትን ለማምጣት ይታገላል፡፡ ለማዳን ሲል ይገድላል። “ማንም የሰው ልጅ እንዳይሞት ጥቂቶች መሞት ይኖርባቸዋል” ብሎ ሰላምን በጉልበት ለማስከበር ይንቀሳቀሳል፡፡

ዋናው ነገር ግን አይለወጥም፡፡ ስድስተኛዋ ጣት አምስቶቹን የተፈጥሮ ጣቶች ተግባር ልትለውጥ አትችልም፡፡

በጦርነት አሸንፎ የገባ በንግግር አሸንፎ ለገባ ስልጣኑን ሊያስረክብ አይችልም፡፡ አምስቱ ጣቶች፣ ከበቀለ ጥቂት መቶ አመታት ላስቆጠረው ስድስተኛ ጣት ተፈጥሮአቸውን ሊያስገዙ አይችሉም። ስድስተኛዋ ጣት...ፍትህ ናት፡፡ ስድስተኛዋ ጣት ፍቅር ናት፡፡ ስድስተኛዋ ጣት ዴሞክራሲ ናት። ስድስተኛዋ ጣት ህገ - ልቦና ናት፡፡ መሆን የምንመኘውን ሁሉ ናት፡፡ መሆን የምንመኘው ከተፈጥሯችን ውጭ ነው።

ዲሞክራሲ የመናገር የመፃፍ መብት፣ በእናንተ ላይ እንዲደረግባችሁ የማትፈልጉትን በሌሎች አታድርጉ (እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ)፣ በህግ ፊት ሁሉም እኩል ነው...ስድስተኛዋ ጣት ድመቱ እርግቧን እንዳይበላ በእርግቦች የፀደቀች ህልም ትመስላለች፡፡ ወይንስ ድመቱ ላይ የሰው ጭንቅላት ሲጨመርበት እና እርግቧን ለመብላት የተሻለ የማስመሰያ ዘዴ ሲያክልበት የበቀለች ቅዠት ናት?

ተፈጥሮ ህገ - ልቦና የለውም፡፡ ደመነፍስ ብቻ ይመስላል፡፡ ሁሉም እንስሳ ሰውንም ጨምሮ የራሱን ህልውና ለማቆየት የመፍጨርጨሪያ አቅም ተሰጥቶታል፡፡ ግን በስተመጨረሻ እንዲያሸንፍ የሚሆነው ጉልበቱን በአቅሙ ላይ ማከል የቻለ ነው፡፡ በተፈጥሮ ቋንቋ መልካም እና እኩይ የለም፡፡ በህልውና መቆየት እና ዘሩን ማስቀጠል የቻለ አሸናፊ ነው፡፡ አሸናፊ ሁሉ ለተፈጥሮ የጨዋታ ህግ ፍትሀዊ ነው፡፡

ቡካውስኪ “ተፈጥሮ ጤነኛ አይደለም” የሚለው ከስድስተኛዋ የህልም ጣቱ ባመነጨው እምነቱ ተመርቶ ነው፡፡ የክርስቶስ ትምህርት ስድስተኛዋን ጣት ትመስላለች፡፡ ከትምህርቱ የመነጨው ሃይማኖት ግን በህልውና መቆየት የቻለው (በስድስተኛው ሽፋን) ጉልበትን በተፈጥሮ አምስት ጣቶቹ ጨብጦ ነው፡፡

ተፈጥሮ ለጉልበት እንጂ ለእውነት አታደላም። ጉልበት ያለው እውነትም አለው፡፡ የጉልበተኝነት እውነት ለጉልበት አልባዎቹ ውሸት መሆኑ ተፈጥሮን አያገባትም፡፡ ጉልበት አልባውም ውሸትን ተጠቅሞ ጉልበት ማብቀል ከቻለ፣ አብቅሎም ሃያል ከሆነ ተፈጥሮ ትቀበለዋለች፡፡

የክርስቶስ ትምህርት ለድሆች እና አቅመ ቢሶች እንጂ ለሮማዊያኑ እውነት አልነበረም፡፡ ለሮማዎቹ፤ ደካማነት ማለት ሽንፈት፣ ደካማ ስለሆኑ ደግሞ ባርያ መሆናቸው የሚጠበቅ ነበር፡፡ ሮማ በተፈጥሮ ዲክሽነሪ የምትተረጐም መንግስት ነበረች፡፡ ክርስቲያኖች ጉልበት እያገኙ ሲመጡ ነገር ተገላበጠ፤ የሮማዊያኖቹ የቀድሞ እውነት አቅሙ ደከመ፡፡ ስለዚህ ከክርስቲያኖቹ ጋር መደባለቅ ነበረባቸው። የክርስቲያን እውነት በደጋፊ መብዛት ምክንያት ጉልበት ማግኘቱ አያጠራጥርም፡፡ ብዛት ራሱን የቻለ የጉልበት ምንጭ ነው፡፡ ጉልበት የሌለውን ተፈጥሮም ህልውናውን ታንኳስስበታለች፡፡

ተፈጥሮ ለጉልበት እንጂ ለፍቅር አታደላም። ተፈጥሮ ለጉልበት እንጂ ለውበት/ጥበብም አታደላም፡ ፡ እርግጥ ነው፤ ጥበብ ጉልበት አለው። ጉልበቱ ግን የጠመንጃን አፈሙዝ መቆልመም ስለማስቻሉ እጠራጠራለሁ፡፡ ጥበብም የስድስተኛዋ ጣት ውጤት ናት፡፡ ወይንም የስድስተኛዋ ጣት ናፍቆት፡ ፡ ጥበብም ስለ ፍቅር ይሰብካል፡፡ ስለ ፍትህ ጉድለት ይጮሃል፡፡ ተፈጥሮን በጥበብ ፈጠራ እንደገና ለማረቅ ይሞክራል፡፡ ግን ይህ ሙከራው ስድስተኛ ጣት ላበቀሉት ሁሉ ቢያማልላቸውም፣ ተፈጥሮን ግን ጥበብ በፈጠራው ማሸነፍ አይችልም። ዘማሪዋ ወፍ በዜማዋ ውበት ምክንያት በጭልፊት ከመጠለፍ መዳን አትችልም፡፡

ነብሩ እረኛው ዋሽንቱን ሲጫወት አርምሞ ውስጥ ገብቶ፣ ፈዞ ሲያዳምጥ እንደሚቆይ በተረት ተረት ሲነገር ሳትሰሙ አትቀሩም፡፡ ጉዳዩ አፈ ታሪክም ይሁን ተጨባጭ እውነት እኔ እንደ ምሳሌነቱ ተቀብዬዋለሁ፡፡

ባለዋሽንቱ ጥበበኛ ነው እንበል፡፡ ውበተኛ፡፡ ውበተኛም ሆነ ጥበበኛ፣ ነብሩ እያደነ ባለበት ሰአት ዋሽንቱን ቢጫወትለት እንደማይሰማው እርግጥ ነው፡፡ በእረፍቱ ሰአት ግን (አውሬው) ዋሽንት መስማት እና ውበት ውስጥ መሆን ሊወድ ይችላል። የመብል ሰአቱ ሲደርስ ግን ጥበበኛውን ከሌላው

ሃሳብ ወደ ገፅ 21 ዞሯል

# ጥድፊያ እና ሆሆታ - የሀገራችን ኪነጥበብ ተግዳሮቶች!

ባዩልኝ አያሌው

“የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው ያለው” እየተባለ በብዙዎች የሚነገርለት (በዚህ ባልስማማም) የሀገራችን ኪነጥበብ በተለያዩ (በአብዛኛው ራስ ወለድ) በሆኑ ተግዳሮቶች እንደተያዘ “እንዲህ ነው” የማይሉት ጉዞውን እንደቀጠለ ነው፡፡ ብዙዎች “ኪነጥበባችን ካለው የአጭር ጊዜ ታሪክ አንጻር አሁን ያለበት ደረጃ ከፍተኛ የሚባል ነው” በማለት አድናቆታቸውን ሲገልጹ፣ ጥቂቶች ደግሞ “የደረሰበት ደረጃ የሚወደስ አይደለም፤ ይልቁንም እጅጉን ግልብ ነው” በማለት የቀዳሚዎቹን አስተያየት ይቃወማሉ፡፡

ወደ ጉዳዩ ከመግባቴ በፊት በሁለቱ አስተያየቶች ላይ ሊነሱ የሚገቡ አንዳንድ ጥያቄዎችን ልሰንዝር። “ኪነጥበባችን የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው ያለው” የሚል መከራከሪያ ላይ የተመሰረተውን አስተያየት ላስቀድም፡፡ አያይዤም አልስማማበትም ያልኩትን ሀሳብ አስረዳለሁ፡፡

ኪነጥበብ ብዙ ዘሮችን/ዘውጎችን በስሩ የሚያቅፍ ጓዘ ብዙ መስክ ነው፡፡ በመሆኑም ኪነጥበብ ስንል ቢያንስ ሥዕልን፣ ቅርጻቅርጽን፣ ስነጽሑፍን (ግጥም፣ ልቦለድ፣ ተውኔት፣ ወግ...)፣ ሙዚቃን፣ ቴአትርን እና የፊልም ጥበብን እየጠራን ነው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጥበባት በሀገራችን ምን ያህል ረጅም ዘመናትን እንዳስቆጠሩ (ከፊልም ጥበብ በቀር) ለማወቅ ብዙ መድከም አያስፈልግም። ጥቂት ቀደምት ድርሳናትን ማገላበጡ ይበቃል፡፡

ሙዚቃው ብንል ሥዕሉ፣ ቅርጻቅርጹ ብንል ስነጽሑፉ... ምናልባትም ከብዙዎች ቀድሞ በሀገራችን ተጀምረዋል፡፡ ቀደምት አባቶች (እርፈቱንና ጽድቁን ይስጣቸው!) ጥበባቱን ከመጀመርም አልፈው ተራቀው አርቅቀዋቸዋል፡፡ ሊያውም ከማንም በፊት- ቀደም! ታዲያ “ካለው የአጭር ጊዜ ታሪክ አንጻር...” ማለት ምን ማለት ነው? እንደኔ ይህን ማለት በአጉል ቃል አባብቶ የማይገባ ይቅርታን ከመለመን ውጪ ሌላ አንድምታ አይኖረውም፡፡

ይህን ስል ግን “ኪነጥበባችን የትም አልደረሰም፤ አንዳችም መልካም ነገር የለውም፡፡” የሚሉትን እየወገንኩ አይደለም፡፡ ጉዞውንና ያለበትን ደረጃ የምር ፈትሾ፣ ገለባውንና ምርቱን፣ ትርፉንና ኪሳራውን በመለየት “እንደዚህ ነው፤ ወይም እዚህ ጋ ነው ያለው” ማለት እንደሚገባ ይሰማኛል፡፡ በደፈናው “እንዲህ ነው” ማለት ብቻውን በቂ ነው ብዬ አላምንምና፡፡ እርግጥ ነው ከምርቱ ይልቅ ገለባው እየበዛ አደከመን እንጂ (ቢያንስ በተወሰኑ ዘውጎች) መልካም ነገሮችን ማየታችን አልቀረም፡፡ መልካሙን ማውራት፣ መልካም ያሰራልና እሱንም መመስከር ይገባል፡፡

ያም ሆኖ ወደጎላው ነገር ስንመጣ የምናዝንበት ብዙ ነው፤ እጅግ ብዙ፡፡ በስነጽሑፉ ቢሉ በፊልሙ፣ በሙዚቃው ቢሉ በሌላውም እጅጉን የሚያሳዝኑና “ጥበባዊ ስራዎች ናቸው” ለማለት በፍጹም የምንቸገርባቸውን ስራዎች መድረኩና ገበያው እያስተናገደ ነው፡፡ እነዚህ ስራዎች ላይ በአብዛኛው የሚታየው አንድ የጋራ የሆነ ባህሪይም አንዳች ፍሬና ጥልቀት ማጣት ነው፡፡ ሀሳብን/ጭብጥን ቢሉ ስንክናዊ ውበትን (Aesthetic Value) ያጋቱ አይደሉም፤ ግልብ ናቸው፡፡

በየእለቱ ፊልሞች ይመረቃሉ፡፡ መጻሕፍት ይታተማሉ፡፡ ሙዚቃዎች ይለቀቃሉ፡፡ ሆኖም ግን ከጥቂት ስራዎች ውጪ አብዛኞቹ አንዳችም ፍሬ የማይገኝባቸው ገለባ ናቸው፡፡ ለዚህም (ምንም እንኳን ይሄ አንዳንዴ በቲፎዞ እና በእድል የሚወሰን ቢሆንም) ለወራት ሳይታይ የሚወርደው ፊልምና ቴአትር፣ ሳይሰማ የሚረሳው የዘመኑ ሙዚቃ፣ ገበያውን የሞላው የስነጽሑፍ ስራ ወዘተ... ዋቢ ነው፡፡ ይህንን ማለት ምናልባትም ጥቂቶችን ያስከፋ ይሆናል፡፡ ደግሞም ሁሉንም አንድ ላይ በጅምላ አጅሎ መተቸትም ሊመስል ይችላል፡፡ ፍሬዎቹን ለማግኘት ገለባውን ማንፈሱ የሚያድክመን ቢሆንም በየዘውጉ ሊመሰከርላቸው የሚገቡ ስራዎች አልፎ አልፎም ብቅ ማለታቸውን መካድ ቢያንስ ሞራላዊ አይደለም፡፡ እነሱን ባናገኝማ ምን ቀምሰን እናድር ነበር? በክረምትስ ቢሆን ፀሐይ እያሰለሰች ብልጭ ትል የለ!

ጉዳዩ የሀገራችን ኪነጥበብ ተግዳሮት ናቸው ከምላቸው ጉዳዮች መካከል ጥድፊያን እና ሆሆታን መዝዞ ጥቂት ማለት ነው፡፡ ሲመስለኝ ኪነጥበባችንን ገለባ ብዙ ካደረጉት ተግዳሮቶች መካከል ጥድፊያ እና ሆሆታ ሁለቱ ናቸው፡፡ ልብ ብላችሁ ከሆነ በሀገራችን በተለይ አሁን አሁን እየተበጁ ያሉ ጥበባዊ ስራዎች እጅጉን በጥድፊያ የተሞሉ ናቸው፡፡ ቅኝታቸው ሩጫ ነው፤ “ረጋ ሰራሽ!”... የያዙትን ይዞ ወደ መድረክና ገበያ ለመውጣት ያለው ጥድፊያና ግፊያ ያህላል የለውም፡፡

የሰራሁት ምንድን ነው? ምን ይጎለዋል? ብሎ ለመፈተሽ፣ ለባለሙያ ለማሳየትና ክፍተቱን ለመሙላት የሚሆን ትዕግስቱም ሆነ ፍላጎቱ የለም። መሮጥ ብቻ፡፡ ገንዘቡ ካለ ደግሞ አለቀ። በአንድ ሳምንት ውስጥ ገበያ ላይ ይውላል፡፡ ሊያውም በሚያሳፍር ውሸት ተሽሞንሙኖ፡፡ “ይህንን ያህል በጀት ፈጅቶአል! ይህንን ያህል ዓመታት ተደክሞበታል!” ወዘተ ተብሎለት፡፡ እውነቱን ግን የምናውቅ እናውቀዋለን፡፡

የአንድ ጥበባዊ ስራ የመጀመሪያ ታዳሚም እንበለው ሐያሲ መሆን ያለበት ራሱ ባለቤቱ ነው፤ ከያኒው፡፡ እሱን ማርካት ያልቻለ ስራ ማንንም ሊያረካ አይችልም፡፡ ከያኒው በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ስራው ውስጥ ይህንን መፈለግና ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለማንም ከማቅረቡ በፊት ራሱ የሰራውን ራሱ ቀምሶ ሊያጣጥመው ይገባል፡፡ ማንም ሴት ድግሷን ቀምሳ መጣፈጡን ሳታረጋግጥ ለእንግዶቿ አታቀርብም፡፡ ሳይቀምሱ ማቅረብ/መጋበዝ መሰደቢያን እንደማቀበል ነው፡፡

ከዚህም አልፎ በዘውጉ ላይ የተሻለ እውቀትና ምልከታው ላላቸው ባለሙያዎች ማሳየቱ የበለጠ ያተርፋል እንጂ አይጎዳም፡፡ ማንም በምንም ጉዳይ ምሉዕ አይደለም፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ስራ ውስጥ (በራሱ ካልሆነ በቀር) ምልዑነት የለም፡፡ ምልዑነቱ አንጻራዊ በሆነ መልኩም

ሆሆታ ወደ ገፅ 22 ዞሯል

# ግብጽ 230 አብዮተኞችን በእድሜ ልክ እስራት ቀጣች

## በ189 ዜጎች ላይም የሞት ቅጣት ጥላለች




የቀድሞውን የግብጽ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ በአመጽ ከስልጣን ለማውረድ ከአራት አመታት በፊት በተቀሰቀሰው አመጽ ተሳትፈዋል የተባሉ 230 የአገሪቱ አብዮተኞች ባለፈው ረዕቡ በካይሮ የእድሜ ልክ እስራት እንደተፈረደባቸው ቢቢሲ ዘገበ፡፡

እ.ኤ.አ በ2011 ታህሳስ ወር ላይ በካይሮው ታህሪር አደባባይ በተካሄደው አመጽ ከአገሪቱ የጸጥታ ሃይሎች ጋር ተጋጭተዋል፣ የተለያዩ የመንግስት ህንጻዎችንና ተቋማትን በእሳት አቃጥለዋል የተባሉት እነዚሁ ተከሳሾች፣ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው የቅጣት ውሳኔው እንደተላለፈባቸው ዘገባው ጠቁሟል፡፡ ተከሳሾቹ ከእስራቱ በተጨማሪ በድምሩ 2ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር በቅጣት መልክ እንዲከፍሉ በፍርድ ቤቱ ተውስኖባቸዋል፡፡

ቅጣቱ ከተላለፈባቸው ግለሰቦች መካከል በችሎቱ ተገኝቶ የፍርድ ውሳኔውን ያደመጠው ብቸኛ ተከሳሽ፣ አመጹን በማቀጣጠልና በመምራት ጉልህ ሚና እንደተጫወተ የሚነገርለት የ26 ዓመቱ አህመድ ዱማ፤ ዳኛው ክሱን በሚያነቡበት ወቅት በማጨብጨብና ጮክ ብሎ በመናገር፣ ተቃውሞውን ለማሰማት ሞክሯል ተብሏል፡፡

የተከሳሾቹ ጠበቆች በበኩላቸው፤ ፍርድ ቤቱ ያስተላለፈውን ውሳኔ የተቃወሙ ሲሆን ዳኛው በተከሳሾቹና በጠበቆቻቸው ላይ ተጽዕኖ ሲፈጥሩ ነበር፣ የፍርድ ሂደቱ በአግባቡ አልተከናወነም፣ ውሳኔውም በአገሪቱ ታሪክ አስደንጋጭና የማይጠበቅ ነው ብለዋል፡፡

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፍርድ ቤቱን ውሳኔ የተቃወመ ሲሆን፣ የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይም በአገሪቱ የሚታየው የጅምላ እስራትና ቅጣት ከዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ጋር የሚጋጭ ነው ብለዋል፡፡ የአውሮፓ ህብረት በበኩሉ፤ ግብጽ አለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ግዴታዎችን ስትጥስ ቆይታለች፤ የግብጽ ባለስልጣናት ይህንን ግዴታ ማክበርና ፍትሃዊ የፍርድ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ ይገባቸዋል ብሏል፡፡

ውሳኔውን ያስተላለፉት ዳኛ ባለፈው ሰኞም የእስላማዊ ቡድን አባላት ናቸው ተብለው በተጠረጠሩ 183 ግለሰቦች ላይ ባለፈው ሰኞ የሞት ፍርድ መበየናቸውን ያስታወሰው ዘገባው፣ አለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማት ፍርዱን መቃወማቸውን እንደገለጹ አመልክቷል፡፡

# አሜሪካ በጨረቃ ላይ ቁጥጥር ማድረግ ልትጀምር ነው

## *ውሳኔው ጨረቃ የማን ናት በሚለው ጥያቄ ላይ ተጽዕኖ አለው ተብሏል



የአሜሪካ መንግስት፤ አገራት፣ የግል የህዋ ምርምር ተቋማትና ኩባንያዎች በጨረቃ ላይ የሚያከናውኗቸውን የንግድ ስራዎች በተመለከተ ቁጥጥር ማድረግ ሊጀምር እንደሆነ ዘ ኢንዲፔንደንት ዘገበ፡፡

አሜሪካ ቁጥጥር ማድረግ እንደምትጀምር ማስታወቋ፣ ጨረቃ የማን ናት፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ወደ ጨረቃ መላክ የሚችሉትስ እነማን ናቸው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተጀመሩ ጥረቶችን አንድ እርምጃ ያራመደ ነው ተብሏል፡፡

የአገሪቱን ኩባንያዎች ጨምሮ በመስኩ የተሰማሩ የመላው አለም ኩባንያዎች መንኮራኩሮችን ወደ ጨረቃ መላክና የተለያዩ ስራዎችን ማከናወን የሚችሉት ከአሜሪካ ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ ነው ያለው ዘገባው፤ ፍቃዱን የሚሰጠውም የአገሪቱ የፌዴራል አቪየሽን ባለስልጣን እንደሚሆን ጠቁሟል፡፡

ባለስልጣኑ ያወጣው የቁጥጥር መመሪያ ኩባንያዎችና ተቋማት ወደ ጨረቃ ለሚያደርጉት ጉዞ ፈቃድ ከመስጠት በተጨማሪ፣ በጨረቃ ላይ የሚኖራቸውን ክልል የሚወስን ነው፡፡

አሜሪካ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸደቀውንና ጨረቃ እና ሌሎች የህዋው አለም ቦታዎች በማንኛውም መንግስት ባለቤትነት ስር አይሆኑም የሚለውን ህግ እንደተቀበለች ያስታወሰው ዘገባው፣ ህጉ የግል ኩባንያዎች በጨረቃ ላይ እንዳያስቀምጡ ባይከለክልም፣ አሜሪካ ግን ይሄን አካሄድ ለመቆጣጠር መነሳቷን አስረድቷል፡፡

# ሳዳም ሁሴን የተሰቀሉበትን ገመድ ለመግዛት ፉክክሩ ተጧጡፏል

## አንድ ተጫራች 7 ሚሊዮን ዶላር አቅርቧል



የኢራን፣ የእስራኤልና የኩዌት ዜግነት ያላቸው ባለጸጎች፣ ቤተሰቦችና ተቋማት የቀድሞው የኢራቅ ፕሬዚዳንት ሳዳም ሁሴን በስቅላት የተገደሉበትን ገመድ በከፍተኛ ገንዘብ በመግዛት የራሳቸው ለማድረግ የጦፈ ፉክክር ውስጥ ገብተዋል ሲል ቢቢሲ ዘገበ፡፡

ተቀማጭነቱ በለንደን የሆነውን አል አራቢ አል ጃዲድ ድረገጽ ጠቅሶ ዘገባው እንዳለው፣ ግለሰቦቹ በቀድሞው የኢራቅ ብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ሞዋፋቅ አል ሩባይ እጅ ውስጥ የሚገኘውን ይህን ገመድ የራሳቸው ለማድረግ እየተፎካከሩ ነው፡፡

ግለሰቡ በመኖሪያ ቤታቸው ከነሃስ በተሰራ የሳዳም ሃውልት አንገት ላይ ገመዱን አጥልቀው የሚያሳየውን ፎቶግራፍ ከሁለት አመታት በፊት ይፋ ማድረጋቸውን ተከትሎ ገመዱን በእጃቸው ለማስገባት ፍላጎት የሚያሳዩ ግለሰቦች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን አንድ የወቅቱ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ተናግረዋል፡፡

ገመዱን ለማግኘት በሚደረገው ፉክክር ከተሳተፉት መካከል፣ ሁለት የኩዌት ባለጸጎች፣ አንድ የኢራን የሃይማኖት ተቋም እና አንድ የእስራኤላውያን ሃብታሞች ቤተሰብ እንደሚገኙበት የጠቆመው ዘገባው፣ አንድ ተጫራች 7 ሚሊዮን ዶላር ማቅረቡን አክሎ ገልጧል፡፡

የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ገመዱን ለማግኘት የተጀመረውን ጨረታ የተቃወሙ ሲሆን፣ ጨረታው የሚቀጥል ከሆነ ግን የሚገኘው ገንዘብ የአገሪቱን ህዝቦች ተጠቃሚ ለሚያደርግ ተግባር መዋል ይገባዋል ብለዋል፡፡

# የእንግሊዙ ፓርቲ ለፌስቡክ በአመት ከ1 ሚ ፓውንድ በላይ ያወጣል

## ብዙ ወጣቶች በምርጫ ድምጽ እንዲሰጡት ለማድረግ ነው



የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሩን አባል የሆኑበት ወግ አጥባቂው ትሮይ ፓርቲ በቅርቡ በሚከናወነው ምርጫ ብዙ ድምጽ ለማግኘት በፌስቡክ ለሚያደርገው ቅስቀሳ በአመት ከ1 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ገንዘብ ወጪ እንደሚያደርግ ዘ ኢንዲፔንደንት ዘገበ፡፡

ፓርቲው ባለፈው አመት መስከረም ላይ ብቻ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች እንዲወዱት ለማድረግ የከፈለውን 25 ሺህ ፓውንድ ጨምሮ፣ በወሩ በድምሩ 123ሺህ የእንግሊዝ ፓውንድ ለፌስቡክ ኩባንያ ገቢ ማድረጉን የጠቆመው ዘገባው፤ ባለፈው ህዳር ወር ፖለቲካዊ ይዘት ላለው ሌላ ድረገጽ 115 ሺህ ፓውንድ መክፈሉን አስታውቋል፡፡

ለፌስቡክ ይህንን ያህል ወጪ ማውጣቱን እንደ ትልቅ ኢንቨስትመንት እንደሚቆጥረው የገለጸው ትሮይ ፓርቲ፤ ገንዘቡን የሚያወጣው ቁጥራቸው የበዛ ወጣቶች በምርጫ ድምጻቸውን እንዲሰጡት በማሰብ እንደሆነ ቢገልጽም፣ የሚሳካለት አይመስልም ብሏል ዘገባው፡፡

በፌስቡክ ተጠቃሚዎች ዘንድ ተወዳጅነትን በማትረፍ ረገድ፣ ብሪቴን ፈርስት የተባለው ፓርቲ ትሮይን በእጥፍ ያህል እንደሚበልጠው የጠቀሰው ዘገባው፣ ብሪቴን ፈርስት 650 ሺህ፣ ትሮይ ደግሞ 340 ሺህ ያህል የፌስቡክ ወዳጆች እንዳሏቸው ጨምሮ ገልጧል፡፡

ዳሽን ባንክ ግሎባል ፋይናንሻል ማርኬት ሪቪው ከተሰኘ አለም አቀፍ ተቋም እ.ኤ.አ. የ2014 በኢትዮጲያ እጅግ በጣም በዕድገት ግስጋሴ ላይ ያለ ባንክ ተብሎ ሽልማትና ዕውቅና ተቀዳጀ




በዚህ አጋጣሚ ባንካችን ለዚህ ክብር የበቃው በእናንተ ውድ ደንበኞቻችን ነውና እናመሰግናለን!!

ስልክ (+251) 011 466 1380 ፋክስ (+251) 011 465 3037
dashen.bank@ethionet.et www.dashenbanksc.com

ዳሽን ባንክ Dashen Bank

2014 Most Progressive Bank Ethiopia
GLOBAL FINANCIAL MARKET REVIEW

ለእድገት ትክክለኛ ምርጫ !

# የአቶ መኮንን ሸዋረጋ
# የ40 ቀን መታሰቢያ

**እግዚአብሔር የወደደውን አደረገ**
**መዝ. 135 ቁ.6**



የአቶ መኮንን ሸዋረጋ የ40 ቀን መታሰቢያ ቅዳሜ የካቲት 7 ቀን 2007 ዓ.ም ከጠዋቱ አንድ ሰዓት በማህበረ ስብሃት ቅድስት ልደታ ለማርያምና ደብረ መድሐኒያለም ቤተክርስቲያን በፀሎተ ፍትሐትና ነዳያንን በመዘከር ታስቦ ይውላል፡፡

ምስጋና፡-በደረሰብን መሪር ሐዘን ምክንያተ ከጎናችን ሆናችሁ ከውጭም ሀገር ሆነ ከአገር ውስጥ ላጽናናችሁን ሁሉ በልዑል እግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡

ከቤተሰቦቻቸው


# የወ/ሮ አሠገደች ታፈሥ
# 1ኛ ሙት ዓመት መታሠቢያ



## ዋ'አካሌ እናቴ!

የእግዜር ቅዱስ ዐፈር
የፍጥረት ሠሌዳው
የዕፍታው ማደሪያ
የቃል መገለጫው
ጽንስ ያህል ሸክም፣
ምጥን ያህል ህመም፣
ይህ ሁሉ በርሷ አቅም፡፡
ወዲህ የጀግና ሚስት
አንድም የመንታ እናት
ተረት ገደል ገባ
ወድቃ ተነስታ እንጂ መች
ተንጋላ ትሙት
ከሰባት ምድጃ ለሚሞቀው
ፍቅሯ
ከጥቢ ጨረቃ ለሚደምቀው
ሳቋ
ሰባ ክብር ቢሰፈር
ሰባ ጊዜ ሰባ ቢደረደር ቅኔ
ቢደረደር
ከሠባት ሠማያት ሠባ መላዕክት
ወርደው
ማኅሌት ቢቆሙላት
"ባሕር እንደ ቀለም ዛፎች እንደ
ብዕር
ምድር እንደብራና" ገድሏን
ለመዘከር
ከቶ አይቻላቸው
ከቶ አይቻላቸው
ከ ቶ አ ይ ቻ ላ ቸ ው
ይኸው ቃል መከነ ልሣን አቅም
አጣ
ናፍቆት ሰቀቀኗን፤ ድካም እንግልቷን፣
ሕልምና ተስፋዋን፤
ገልጦ እንዳያወጣ
ዝም ነው ዝም ነው
እንዲያው ዝም እንዲያው ዝም
የርሷን ነገር ይዞ
ለብቻ ለብቻ ለብቻ ተክዞ
ዘለ'ለት ንግግር ተራ ተርታ እንዳይሆን
መሸሸግ ነው ለራስ
ከውስጥ አንጀት ቀብሮ
ለብቻ ለብቻ ለብቻ፤
"ዋ አካሌ እናቴ" ዋ እምዬ እናቴ
ላንቺም እንደ ልማድ እንዲያው ወየው
ወየው
እንዲያው ወይኔ ብቻ፡፡
(አያልቅበት አደም)

# ማረሚ ያ



ባለፈው ሳምንት የክቡር አቶ ነጋ ድዋቶ የ7ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም የተባለው ጥ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ይውላል በሚል እንዲነበብ እየጠየቅን ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ዳሰሳ ከገፅ 15 የዞረ

የሆነው ሀሳብ እንኳ ግጥምን አይፈጥርም! ወይም ግጥም አይሆንም፡፡" ይሁን እንጂ እኛ ሀገር በተለይ ከቅርብ ዓመታት በኋላ የመጣው ግጥም መመዘኛ ይህ እየሆነ ነው። ወደ ስህተት እየመራንም ያለው እርሱ ነው፡፡ ግጥም የብዙ አላባዊያን ቅንብር ነው፡፡ ጥሩ ሃሣብን እንደ አውሮፕላን ሞተር እንኳ ብንወስደው፣ ለመብረር ክንፍ ያስፈልገዋል፡፡ ቃላት ወሳኝ ናቸው፡፡ ዜማ፣ ስዕል፣ ምት፣ ማዕከላዊ ሃሣብን የማብሰልና የማጠንከር ጉዳይ ሁሉ ሊታይ ይገባል፡፡ አቶ አብደላ እዝራ ላይ ቅር ያሰኘኝም ይህ ነው፡፡ የሥነጽሁፍ ባለሙያዎችን ሲክብም ሆነ ሲንድ ምክንያት ቢሰጠን ደስ ይለኛል፡፡ የትኛው በየትኛው የውበት ሠፈር እንዳለ ለመለየት ያስችለናል፡፡ በተረፈ ግን ለሥነፅሁፋችን እድገት እየታተረ ነውና አድናቆቴን መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ መልካም ጊዜ፡፡

ሃሳብ ከገፅ 18 የዞረ

ታዳኝ ሳይመርጥ ውበቱን ገድሎ ይበላዋል፡፡ ጥበብ ጉልበት አለው፡፡ ሰውን ከተፈጥሮ የአውሬ ባህሪው ማጽዳት የሚችል ጉልበት ግን አይደለም፡፡

እኔም አሁን እያፃፍኩ ያለሁት በአምስቱ ጣቶቼ እስክሪብቶውን ጨብጬ፣ እውነቴን ግን ከስድስተኛው ጣት እያፈለቅሁ ነው፡፡ እንደ ቡካውስኪ እኔም ጉልበት (ተፈጥሮ) ጤነኛ ስላለመሆኑ አምናለሁ፡፡ ግን እምነቴ ተጨባጩን የተፈጥሮ ባህርይ ሲለውጥ ተመልክቼ አላውቅም፡፡ እምነቴ በተፈጥሮ ቀዳዳ ላይ እንደተጣፈ ባዕድ ቀለም ያለው ጨርቅ መስሎ ይሰማኛል፡፡ እምነቴ ውህን ሽቅብ እንዲፈስ ማድረግ ሲችል አላየሁም፡፡

Nature VS Nurture – Nature ways wins የሚሉት ወደው አይመስለኝም፡፡ ሳይንቲስቶች በሰው ልጅ ህይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥን ሲያመጡ ማየት የቻልነው ተፈጥሮ ላይ ስለሚያተኩሩ ብቻ ነው፡፡ ሳይንስ ህገ ልቦናን አያጠናም፡፡ ሳይንስ መልካም እና እኩይን ሳይሆን ተጨባጩን እውነታ ነው የሚመረምረው፡፡ መርምሮ የሚያቀርበው ፈጠራ ደግሞ ከተፈጥሮ ባህርይ የተቀዳ በመሆኑ እውነተኛውን ተፈጥሮ ማገልገሉ አይካድም፡፡ እውነተኛው ተፈጥሮ:- ጉልበት...ፍትህ ነው፣ ጉልበት ህይወት ነው፣ ፍቅርን ጉልበት ይገዛዋል (ጉልበት ያለው ነው የሚፈቀረው)...የሚል ይመስለኛል፡፡ ከመሰለኝ ደግሞ ነው!

ዲሞክራት ከገፅ 6 የዞረ

መዋቅር ነው፡፡ አሠራሮቹ በሙሉ ከሙስና የፀዳ መሆኑን ግን እንከታተላለን፣ ከፖለቲካ ገለልተኛ መሆኑን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፡፡ መንግስት እንደመንግስት ብቻ የሚሠራቸው መሆኑን ማረጋገጥ እንሻለን፡፡ ገዥው ፓርቲ የኔ ሃብቶች ናቸው፣ የኔ ውጤቶች ናቸው... እያለ የሚሰብከውን ግን እንቃወማለን፤ የህዝብ ተቋሞች መሆናቸውን እንዲያረጋግጥ እንፈልጋለን፡፡

*ኢዴፓ ለግንቦቱ ምርጫ ምን ዝግጅት እያደረገ ነው? ከምርጫው የሚጠብቀው ውጤትስ ምንድን ነው?*

የምርጫ ቦርድን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት አድርገን እቅድ አውጥተን እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ እጩዎችን በመመልመል በርካታ ስራ ሠርተናል፡፡ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች፤ በትግራይ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል፣ ኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ፣ አፋር፣ ሱማሌ፣ በጋምቤላ... እጩዎችን አስመዝግበናል፡፡ በምርጫው አብላጫ ድምጽ በማግኘት ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር ወይም በገዥው ፓርቲ ላይ ተፅዕኖ እንፈጥራለን ብለን ነው የምናስበው፡፡

እስከመጨረሻው ያለው የምርጫ ሂደት ሠላማዊ እንዲሆን ለፓርቲዎች ጥሪ አስተላልፋለሁ፡፡ ህዝቡም ለሠላማዊ ትግሉ የማይመጥኑና ወደ ጥርጣሬ የሚወስዱትን ሂደቶች በጥንቃቄ እንዲገመግም ጥሪ አቀርባለሁ፡፡ ገዥው ፓርቲ መንግስት እንደመሆኑ መጠን የዲሞክራሲ ተቋማት ነፃና ገለልተኛ ሆነው ምርጫውን የሚታዘቡበትን ሁኔታ መዘርጋትና መከታተል ይጠበቅበታል፡፡ አሁን ገለልተኛ አይደሉም የሚባሉትን ተቋማት፣ ገለልተኛነት ማስመስከር አለበት፤ ካልሆነ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ እየበደለና እያሳዘነ የሚሄድበት እድል ሠፊ ነው፡፡ ሌላ የትግል አማራጭ የመፈለግ አዝማሚያም እየታየ ስለሆነ፣ ያንን የሚዘጋበትን እድል ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

ቀልዶች ከገፅ 16 የዞረ

ማንበብ፡፡ በአግባቡ ካላነበባችሁን፡፡"

**<u>ሌላ እብድ</u>**

በአንድ ወቅት አክሱም ከተማ ውስጥ ድንጋይ የሚወራወር አዲስ እብድ መጣና ህዝበ አዳምን በድንጋይ ሲያራኩተው፣ ምህረይም እንደ ሌላው ሲሸሹ አንድ ሰው ያያቸውና፤ "ምህረይ እርስዎ እብድ ሆነው እንዴት እብድ ፈርተው ይሮጣሉ?" ብሎ ይጠይቃቸዋል።

ምህረይም ፈጠን ብለው" ሁላችንም አብደን እንዳየነው እኛ ጨዋታ እንጂ ድንጋይስ አልወረወርንም ነበር፡፡ የዚህ ግን ለብቻው ነው ወንድሜ" ብለው ሩጫቸውን ቀጠሉ፡፡

# ላንቺና ላንተ

# “...እድሜ ትልቁና ዋነኛው ምክንያት ነው...”

ዮዲት ባይሳ ከኢሶግ

ልጅ ወልዶ የመሳም ፍላጎት አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ሊያገኛቸው ከሚጓጓላቸው ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው:: ታዲያ ይህ ልጅ የማግኘት ጉጉት በተለያዩ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሊስተጓጎል አልፎም መሀንነትን ሊያስከትል ይችላል::

የአለም የጤና ድርጅት በፈረንጆቹ 2010ዓ/ም ባወጣው ጥናት መሰረት በአለማችን ላይ ቁጥራቸው 48.5 ሚሊዮን የሚገመት ጥንዶች የዚህ የማሀንነት ችግር ተጠቂዎች ናቸው:: ጥናቱ የተደረገው በፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ1990-2010/ አመተ ምህረት በ190/ የተለያዩ ሀገሮች ነው:: በጥናቱም በ1990/ ዓ/ም 42.2/ ሚሊዮን የነበረው የመሀንነት ችግር ያለባቸው ጥንዶች ቁጥር በ2010/ ዓ/ም 48.5/ ሚሊዮን መድረሱን ጠቁሟል::

በዛሬው ፅሁፋችን በተፈጥሮ ከሚከሰተው መሀንነት ውጪ ከአኗኗር እንዲሁም ከመድሀኒት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ መሀንነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች በሚመለከት የባለሙያ ማብራሪያ አካተን ያጠናቀርነውን ፅሁፍ እንዲህ ልናስነብባችሁ ወደናል::

ለዛሬ ያነጋገርናቸው ባለሙያ ዶክተር አበበ ሀይለማሪያም ይባላሉ:: ዶክተር አበበ በዘውዲቱ ሆስፒታል የማህፀንና ፅንስ ሀኪም ናቸው ለመሆኑ በህክምናው ሳይንስ መሀንነት እንዴት ይገለፃል? በቅድሚያ ያነሳንላቸው ጥያቄ ነበር::

“...ሁለት ጥንዶች ምንም አይነት የእርግዝና መከላከያ ሳይወስዱ በተገቢው መጠን የግብረስጋ ግንኙነት እያደረጉ ቢያንስ ለአንድ አመት መውለድ ካልቻሉ መሀንነት ይኖራል ተብሎ ይታሰባል:: ነገር ግን መከላከያ ሳይወስዱ መውለድ አለመቻላቸው የመሀንነት ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል እንጂ መሀንነት ነው ብሎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: መሀንነት መሆኑን ለማረጋገጥ የተለያዩ ምርመራዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ::”

የወር አበባ ኡደት መዛባት፣ ቀደም ሲል ተከስቶ የነበረ የአባላዘር በሽታ በማህጸን ቱቦ ወይንም በህክምናው fallopian tube ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ትቶት የሚያልፈው ቋሚ የሆነ ጠባሳ መሀንነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ይላሉ ዶክተር አበበ:-

“በሴቶች በኩል መሀንነትን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው የእድሜ ጉዳይ ነው:: ምክንያቱ ደግሞ እንቁላል የሚያመነጬት እጢዎች እድሜ እየገፋ በሄደ ቁጥር ቀደም ሲል ያመነጩ የነበረውን ያህል እንቁላል ላያመነጩ ይችላሉ::

ስለዚህ እድሜ ትልቁና ዋነኛው ምክንያት ነው ማለት እንችላለን:: የወር አበባ ኡደት ሲዛባም የሴቷ እንቁላል ላይመነጭ ይችላል ወይም ደግሞ እንዳስፈላጊነቱ ጊዜውን ጠብቆ ላይመጣ ይችላል:: ከዛ ውጪ ከተለያዩ ኢንፌክሽኖች እንዲሁም የአባላዘር በሽታዎች የተነሳ የማህፀን ቱቦ መዘጋት ሊኖር ይችላል ይህም የሴቷን እንቁላልና የወንዱ የዘር ፍሬ በተገቢው መንገድ እንዳይገናኙ ሊያደርግ ስለሚችል ለመሀንነት አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ በተፈጥሮ ለመራባት የሚያስፈልጉ አካላት ላይኖሩ ይችላሉ እሱም ሌላኛው ምክንያት ነው:: ሌሎች እንደ ቲቢ ያሉ በሽታዎችም ማህፀን አካባቢ ከሚፈጥሩት ችግር የተነሳ ፅንስ እንዳይፈጠር ሊያደርግ ይችላል::”

በዝርዝ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪም የተለያዩ መድሀኒቶች ከመውሰድ ለምሳሌ ከአእምሮ ህመም ጋር በተያያዘ ለረዥም ጊዜ መውሰዱ መድሀኒቶች በሴቷ በኩል መሀንነትን ሊያመጡ እንደሚችሉ ዶክተር አበበ ይገልፃሉ::

“...ለመሀንነት የሚያጋልጡ የተለያዩ መድሀኒቶች አሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ የደም ግፊት መድሀኒቶች ለመሀንነት የሚያጋልጡበት ሁኔታ አለ:: ይህ ማለት ሁሉም የደም ግፊት መድሀኒቶች ለመሀንነት ያጋልጣሉ ማለት አይደለም:: ነገር ግን አንዳንዶቹ መድሀኒቶች በውስጣቸው የያዙት ንጥረነገር ለመሀንነት የሚኖረውን ተጋላጭነት የሚጨምሩበት ሁኔታ አለ:: አንዳንድ ለአእምሮ ህመም ለረዥም ጊዜ የሚወሰዱ መድሀኒቶችም በተመሳሳይ ለዚህ ችግር ሊዳርጉ ይችላሉ:: ነገር ግን በአብዛኛው እንደዚህ አይነት መድኒቶች በሀኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ ስለሆኑ ይህን አይነቱን ችግር እንደሚያስከትል ከታወቀ ባለሙያው ሌሎች መድሀኒቶችን ሊያዝ ይችላል::

በተለምዶ በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ የእርግዝና መከላከያ እንክብሎች ወይም መርፌ ለዚህ ይዳርጋል የሚል አስተሳሰብ አለ:: ነገርግን በህክምናው ሳይንስ የዚህ አይነት አመኔታ የለም:: ማለትም ይህን በሚመለከት በተደረጉት የተለያዩ ጥናቶች የዚህ አይነት መድሀኒቶች መሀንነትን እንደማያመጡ ተረጋግጧል::”

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ምክንያቶች በሴቶች በኩል መሀንነትን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ምክንያቶች መካከል ዋነኞቹ ይሁኑ እንጂ ለመሀንነት ሴቷም ሆነች ወንዱ ተመጣጣኝ የሆነ አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል ብለዋል ዶክተር አበበ::

“...በአብዛኛው ከወንዱም ከሴቷም በኩል ተመጣጣኝ የሆነ ምክንያት ሊኖር ይችላል:: ለምሳሌ ወንዱ ከ30-50% ወይም በአማካኝ 40% የወንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: በተመሳሳይ የተቀረው 40% በሴቷ በኩል የሚከሰት ችግር ነው:: ከሁለቱም ምክንያት ሊሆን የሚችልበት 10% ይሄ ነው ተብሎ የማይገለፅ ደግሞ 10% ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ በአጠቃላይ መሀንነት ምክንያቱ በአንድ ወገን ነው ብሎ መደምደም አይቻለም::”

ቀደም ሲል ባለሙያውም እንደ ገለፁት ምንም እንኳን ወንዱ እንዲሁም ሴቷ ለመሀንነት ያላቸው አስተዋፅኦ በመቶኛ ደረጃ ይለያይ እንጂ መሀንነት በሴቶች ብቻ ሳይወሰን በሁለቱም ፆታዎች ላይ ሊከሰት የሚችል ችግር ነው:: ነገር ግን በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ መሀንነት በሴቶች ላይ ብቻ የሚከሰት ችግር አድርጎ የማሰብ የቆየ ልማድ አለ:: ይህም የህክምናው ሳይንስ ከሚለው ፈፅሞ የራቀ ነው እንደ ማብራሪያው::

“...በተለይ እንደኛ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች መሀንነት የሴቷ ችግር ብቻ ተደርጎ ይታሰባል:: ይህ የሆነበት የተለያዩ ባህላዊ እንዲሁም ሀይማኖታዊ አመለካከቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ሌላውና ለዚህ አይነቱ አመለካከት መንስኤ የሚሆነው ደግሞ ችግር ሲኖር ሁለቱም ጥንዶች በጋራ ሆነው ህክምናቸውን ለመከታተል የሚኖራቸው ተነሳሽነት ነው:: በአብዛኛው ይህ የመሀንነት ችግር ሲከሰት ሴቶች ፈጥነው ወደ ህክምና ተቋም ይመጣሉ:: አብዛኞቹ ወንዶች ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ አይሆኑም ስለዚህም ሴቷ እንደ ምክንያትነት ትጠቀሳለች:: ነገር ግን መሀንነት በተመጣጣኝ ሁኔታ በወንዱም ሆነ በሴቷ ላይ ሊከሰት የሚችል ችግር ነው::”

መሀንነት በተፈጥሮ እና በአንዳንድ የጤና ችግሮች የሚከሰት ቢሆንም ከአኗኗር እንዲሁም ከመድሀኒት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ መሀንነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች አሉ::

“...ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ተፈጥሯዊና እንደ አባላዘር ያሉ በሽታዎች ለመሀንነት ሚዳርጉ ዋነኛ ምክንያቶች ይሁኑ እንጂ ከዛ ውጪ ሌሎች ከአመጋገባችን ወይም እለትተለት የምናደርገው እንቅስቃሴ ለመሀንነት የሚኖረንን ተጋላጭነት ከፍ ሊያደርጉት ይችላሉ:: ለምሳሌ አመጋገብን ብንመለከት አንዳንድ ሴቶች የሰውነታቸው ክብደት በጣም ዝቅተኛ ይሆንና ሰውነታቸው የሚፈለገውን ንጥረ ነገሮች በተገቢው መንገድ ላያገኝ ይችላል:: ይህ ደግሞ የወር አበባ መዛባትን አንዳንዴም ጭርሱንም እንዲቀር ሊያደርገው ይችላል:: ስለዚህ ይህ ሁኔታ ልጅ ለመውለድ የሚኖረውን ሁኔታ ሊያዘገይ ወይም መሀንነትን ሊያስከትል ይችላል::”

የሴቷ የሰውነት ክብደት ጤናማ የሚባለው ምን ያህል እንደሆነና የክብደት መቀነስ የሚለው ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የወር አበባ መዛባትን ከማስከተሉ ባለፈ መሀንነትን ሊያስከትል የሚችልባቸውን መንገዶች ዶ/ር አበበ እንደሚከተለው ገልጸዋል::

“..አንዲት ሴት በአማካኝ ሊኖራት የሚገባው የሰውነት ክብደት ሀምሳ ኪሎ እንዲሆን ይጠበቃል:: ነገር ግን ክብደቷ ከዛ በታች ከሆነ ይህ የክብደት ማነስ ለወር አበባ መዛግየት ብቻም ሳይሆን ከአእምሮ የሚመነጩ የተለያዩ ኬሚካሎች በተገቢው መጠን እንዳይመነጩ ሊያደር ይችላል:: ይህም የሴቷ እንቁላል ከዘር ማፍሪያ እጢ ፅንሱ እስከ ሚፈጠርበት የማህፀን ክፍል የሚኖረው መንገድ ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር ስለሚችል በዚህ ሁኔታ መውለድ ሊዘገይ ወይም መሀንነት ሊከሰት ይችላል::”

መሀንነትን በሚመለከት በህብረተሰቡ ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ:: ከእነዚህ ለዘመናት የመሀንነት መንስኤ ናቸው ተብለው በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ነገሮች መካከል መሀንነትን በዘር የሚመጣ ችግር አድርጎ ማሰብ አንዱ ነው:: ለዚህም ነው አንዳንድ ሰዎች ከቤተሰብ አባላት መካከል አንዳቸው ይህ የመሀንነት ችግር ሲገጥማቸው “ኧረ እኛ በዘራችን መሀንነት የለም...” ሲሉ የሚደመጡት:

“..ሁሉም የመሀንነት ችግር በዘር የሚመጣ ነው ብሎ መደምደም ባይቻልም በተወሰነ ደረጃ ከዘር ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ አለ:: ቀደም ሲል ጠቅሼዋለሁ ለመሀንነት ሚያጋልጡ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ:: ነገር ግን አልፎ አልፎ የተለያዩ genetic disorder ወይንም በዘር የሚወረስ የተፈጥሮ መዛባት የምንላቸው ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ::

ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ በተፈጥሮ ለመራባት የሚያስፈልጉት ህዋሶች (Gene) በሰውነታችን ውስጥ ላይገኙ ይችላሉ ወይም ደግሞ ባላስፈላጊ ሁኔታ ተባዝተው ሊገኙ ይችላሉ::

ስለዚህ የዚህ አይነት ምክንያቶች ለመሀንነት የሚዳርጉበት ሁኔታ አለ:: ነገር ግን ከቤተሰብ አባላት ውስጥ የመሀንነት ችግር ተከስቶ ስለማያውቅ ወይም ይህ አይነቱ ችግር ያለበት ሰው የለም ማለት ፈፅሞ መሀንነት ሊያስከትል አይችልም ማለት አይደለም...” እንደ ዶ/ር አበበ ኃ/ማርያም የጽንስና ማህጸን ህክምና እስፔሻሊስት::

**ይህንን አምድ አዘጋጅቶ የሚያቀርብላችሁ ESOG-Ethiopian Society of Obstetricians and Gynecologists (የኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሀኪሞች ማኅበር) ነው::**
**(በፖ.ሣ.ቁ 8731 ስልክ 011-5-506068/69 ልታገኙን ትችላላችሁ)**

ሆሆታ ከገፅ 18 የዞረ

ቢሆን የሚከሰተው ሌሎችም ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ በሚያደርጉት አስተዋጽኦ ነው:: እርግጥ ነው ይህ አመለካከት ብዙዎችን ላያስማማ ይችላል። ነገር ግን ግምገማን የሚፈልጉና በባህሪያቸው እንደወረደ ቢቀርቡ የሚመረጡ ስራዎችን መለየቱ ይመስለኛል አንኳሩ ጉዳይ::

ሌላው የሀገራችን ኪነጥበብ ተግዳሮት፣ ቀድሜ እንዳልኩት ሆሆታ ነው:: ስክነት ማጣት፤ ተቀብሎ ማስተጋባት፤ በቅጡ ተገንዝቦ አለማስገንዘብ:: ልብ ብላችሁ ከሆነ፣ አንድ ስራ ለታዳሚ ሲቀርብ ሆሆታውና ውዳሴው ልክ የለውም:: በእርግጥ ምንም ይሁን ምን አንድ ጥበባዊ ስራ ተሰርቶ ለህዝብ መቅረቡ በራሱ (የጥራትን ጉዳይ ትተን) ቢያንስ ከብዛት አንጻር የሚጨምረው ነገር በመኖሩ “እንኳን ደህና መጣህ” ብሎ በክብር መቀበሉ ጉዳት የለውም:: እየሆነ ያለው ግን እንደሱ አይደለም:: ሳይመዝኑና ለምን? ሳይሉ የስራውን ትልቅነት በደቦ መመስከር፤ መቀባበል ነው:: ስራውን በቅጡ ተረድቶ ከመዳኘት ይልቅ ሆሆታውን ማራገብ::

የሚገርምው ነገር ታዲያ ከዚህ የሆሆታ ተዋናዮች መካከል ምናልባትም ዋነኞቹ በኪነጥበቡ ውስጥ የሚገኙ “ሙያተኞችም” ጭምር መሆናቸው ነው:: አንድን ጥበባዊ ስራ፣ በሙያው የሌለ የሙያው አድናቂ ያልተገባ ደረጃ ቢሰጠው (መስጠቱ የተለመደ ነው) አስገራሚ አይደለም:: ምክንያቱም ታዳሚው ስራውን የሚዳኘው በአብዛኛው በስሜት ላይ ተመስርቶ እንዲሁም ከራሱ ገጠመኝ ጋር አያይዞ ነው:: ስንክናዊ ውበትም በሉት ዘውጉ የግድ የሚላቸው ቴክኒኮች ወዘተ... አይገዱትም:: ደግሞም ላያውቃቸው ይችላል:: የግድ እንዲያውቃቸውም አይጠበቅም::

በመስኩ ውስጥ የሚገኝ ባለሙያ ግን ከሆሆታው ተገልሎ ባለው አቅምም ቢሆን ስራውን ከተለያዩ አንጻሮች ሊፈትሽ ይገባል:: ሲገባኝ ይህንን ማድረግ ሞራላዊም ሆነ ሙያዊ ግዴታው ነው:: እየሆነ ያለው ግን እንደሱ አይደለም:: ባለሙያውና ከሙያው ውጪ ያለውም በአንድ አብሮአል:: የልዩነት መስመሩ ጠፍቶአል:: ሆሆታው በጋራ ነው::

ሒሱም ቢሆን ብዙም ራሱን ከሆሆታው አላገለለም:: ሙያውና የሙያው ስነምግባር የሚጠብቅበትን ከማድረግ ይልቅ ሆሆታው “ታላቅ ነው” ያለውን አጽድቆ ይመሰክራል:: ጥቂት የምር የጥበቡ ተቆርቋሪዎች፣ የተገነዘቡትንና እውነት ነው ያሉትን በማጠየቂያ አስደግፈው በድፍረት ቢናገሩም ሰሚ የላቸውም:: በሆሆታው ይታፈናሉ:: ደግሞም ሆሆታው ቅጥልጥል ነው:: ማቆሚያ የለውም:: ለምን? እንዴት?... ማለትን የማያውቀው ሚዲያውም ሆሆታውን ተቀብሎ፣ አጉልቶና አድምቆ ወደ ህዝቡ ይለቀዋል:: ብቻ ቲፎዞና አራጋቢ አይጥፉ ገለባው ሁሉ መልካም ስንዴ ይሰኛል:: ማን “ህግ” ብሎት!

እነዚህ ሁለት ተግዳሮቶች የሚያመጡት ጥፋት ይህንን ያህል ነው ተብሎ የሚመዘን አይደለም። በአጠቃላይ ጥበቡን “እግር ከወርች” ቀፍድደው ይዘውታል:: ጥድፊያውም ሆነ ሆሆታው ሌላውን ትተን ቢያንስ ሁለት አካላትን በእጅጉ ይጎዳል- ታዳሚውንና በተለይ ደግሞ ራሱን ኪነጥበቡን::

አንድ ኪነ ጥበባዊ ስራ ያለ ስክነትና እውቀት በጥድፊያ ተሰርቶ በመቅረቡ ሊደርስ የሚችልበትና የሚገባው ብቃት ላይ ሳይደርስ ይቀራል:: በዚህም የጥበቡ ታዳሚ ገንዘቡን አውጥቶና ጊዜውን ሰውቶ የተሻለ እርካታ ማግኘት ሲገባው ገለባን እንዲጋበዝ ይገደዳል:: ከሚያከብራቸው ባለሙያዎችም ሆነ ከሚወደው ሙያ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ተነፍጎ ይጭበረበራል::

የራሱ የኪነጥበቡ መጎዳት ደግሞ ይብሳል። በየዘመኑና ዘመኑ በሚፈጥርለት እድሎች (እውቀቶች፣ ቴክኖሎጂዎች፣ ባለሙያዎች...) ማደግ ያለበትን ያህል ማደግ ሲኖርበት እድገቱን ይነፈጋል። ምክንያቱም በጥድፊያ የተሰራ ጥልቀት የለሽ ስራ ጥበቡን ባለበት እንዲረግጥ ያደርገዋል:: ምናልባትም ጭራሽ ወደ ኋላ ይጎትተዋል::

በዚህ መንገድ የተፈበረከውን ስራ በማጀብ ያልተገባ መልክና ደረጃ የሚሰጠው ሆሆታም የሚያደርሰው ኪሳራ እንዲሁ ነው:: ታዳሚን ያደናግራል፤ ያታልላልም:: አሁንም ታዳሚው ማግኘት ያለበትን እውቀትና ተዝናኖት ያጣል::

አሁንም በሆሆታው ከምንምና ከማንም በላይ እጅጉን የሚጎዳው ራሱ ኪነጥበቡ ነው:: ሆሆታ አንድን ስራ በቅጡ በመመርመር የሚገባውን ቦታ ለመስጠት ፍላጎቱም ሆነ ትኩረቱ ስለሌለው ምርትና ገለባውን ማንፈሻው ከእጁ የለም:: በዚህ መካከል ታላላቅ ጥበባዊ ስራዎች ቦታ የላቸውም፤ ወይም እነሱም በሆሆታው ውስጥ አብረው ታጅለው ያልፋሉ- ያላቸው የተለየ ዋጋ ተከልሎ::... ገለባውም የታላላቅ ስራዎችን ክብር ለብሶና ተሸሞንሙኖ ያልፋል:: ምክንያቱም በዚህ ሂደት ውስጥ ሂደቱን ፈትሾ ምርቱንና ገለባውን የሚለይልን ሀቀኛ ሒስ የለም:: በመሆኑም ቢያንስ ኪነጥበቡ የት ጋ ነው ያለው? የሚለውን እንኳን ማወቅ አንችልም::

ተግዳሮቶቹ “ሀይ” ባይ አጥተው ኪነጥበባችንን ወዳሻቸው ከመሩት እነሆ ዓመታት አለፉ:: ይኸውም ኪነጥበባችንን ገለባ ብዙና ደረጃ አልባ... እንዲሁም ትርምስምስ አድርጎታል:: ባለሙያውም፣ ሒሱም፣ ሚዲያውም፣ ታዳሚውም... አውቀውትም ሆነ (ጥቂቶች ዓላማቸው በግል የሚያገኙት የማይገባ ጥቅም ነውና ከተግዳሮቶቹ ያተርፉሉ) ሳያውቁት የተግዳሮቶቹ ጠበቆች በመሆናቸው “እንወደዋለን! እናከብረዋለንም!” የሚሉትን ኪነጥበቡን እየጎዱት ነው:: እስከመቼ የሚለውን ባናውቅም::

መልካም ሰንበት!!

ሸለቆ ከገፅ 10 የዞረ

ይገባኛል:: ለሁሉም ወገን ጠቃሚ መረጃዎች ናቸውና:: ታላቁ የዓባይ ሕዳሴ ግድብ አሁን ዓለማችን ያደረሰበትን የውሃ ግድብ ቴክኖሎጂ በላቀ ሁኔታ እየተጠቀመ ነው:: እጅግ ድንቅ፣ የተመሰከረላቸውና ብቁ ባለሙያዎች እየመሩት ይገኛሉ:: በውሃ ማስተንፈሻ፣ በውሃ ሥርገት አወጋድ፣ በአማራጭ የማስተንፈሻ ግንባታ ብቃት፣ በግንባታው ልንቅጥ ቅይጦች ጥራት፣ ለሁሉም የግንባታ ተግባር ሥራ ላይ በዋሉት ማሽነሪዎች ዘመናዊነትና ትክክለኛነት የዓለም አቀፍ ደረጃዎቹን ስለማሟላቱ የሚያጠራጥር መረጃ ተሰጥቶናል:: በዚህ ግድብ ሥራ ላይ የተሰማሩት መላው ሠራተኞች ከዚህ በኋላ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ለሚሠሩ ተመሳሳይ ግንባታዎች ተፈላጊና ቁልፍ ሠራተኞች ይሆናሉ::

የታላቁ ዓባይ ሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ተሰልፎ ረሃብን ለመዋጋት የደረሰበትን ከፍተኛ ውሳኔ በገሃድ የሚያሳይ ዓይነተኛ ሀብት ነው:: ከ40-50 ዲግሪ ሴሊሸየስ በሚደርሰው በዚህ ዱባ ንዳድ ሸለቆ ውስጥ ሌት ተቀን የሚማስኑት ሠራተኞች ሁላችንም በየተሰለፍንበት የሙያ መስክና ሥራ ላይ መበርታትና መትጋት እንዳለብን ዋቢዎቻችን ናቸው:: ምሳሌነታቸውም በእያንዳንዱ ልብ ማኅተም ሆኖ የሚቀርና ለመንፈሳዊ ሕዳሴም አንድ ግብአት መሆኑ ይሠማኛል:: ከዚህም በላይ ግድቡ በሚጠናቀቅበት ጊዜ የዓባይ ውሃ ወደኋላው እያገፈገ ከ250 ኪ.ሜትር በላይ ርዝመት ይሄዳል:: ይህም ምናልባትም በአፍሪካ ትልቁን ሰው ሠራሽ ሐይቅ ይፈጥራል:: በአጭሩ ከአዲስ አበባ እስከ ሻሸመኔና ሐዋሳ ሊደርስ የሚችል ሐይቅ ነው። ሐይቁ ደግሞ ለቱሪዝም፣ ለዓሳ ማራቢያነትና ለተለያዩ የሀብት ማመንጫነት ይውላል:: የዚህን ሁሉ አቀፍ እንቅስቃሴ ከሃያ ዓመታት በኋላ በዓይነ ሕሊና ማየት ጠቃሚ ነው:: የዚህ ሐይቅ መፈጠር የጐላ ጠቀሜታ ያለው ለታችኛው ተፋሰስ አገሮች እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለኝም:: ይህን ጉዳይ በሁለት አጫጭር ምሳሌዎች መግለጽ ነገሮቹን ሁሉ ያቀላቸዋል::

ግድቡ ሲጠናቀቅና የዓባይ ውሃ በተዘጋጀለት መፍሰሻ በር አልፎ እያንዳንዳቸው 375 ሜጋ ዋት የሚያመነጩትን መዘውሮች (ተርባይኖች) እየገፈተረ ወደታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ይነጉዳል::

ይህ ፈሳሽ ወንዝ ሱዳን ድንበር ላይ ሲደርስ መጠኑ በዘመናዊ መሳሪያ ይለካል:: (አሁንም እየተለካ ነው::) ከግድቡ ፍፃሜ በፊት ይፈስ የነበረው የውሃ መጠን ልክ መሆኑ ይረጋገጣል:: (በየቀኑ) እጅግ ኃይለኛ ጐርፍ ዓባይን ቢያጥለቀልቀው ወደታችኛው ተፋሰስ ሀገሮች የሚለቀቀው ውሃ ፊት ከነበረው እኩል ነው:: በብዛት የጐረፈው ውሃ ትርፉ ወደኋላ እየተመለሰ ሐይቁን ሊያበራክተው ይችላል:

ሸለቆ ወደ ገፅ 23 ዞሯል

# የመጀመርያው አገር አቀፍ የስፖርት ኤግዚቢሽንና ባዛር ተዘጋጅቷል



በስፖርቱ በማርኬቲንግና በኢንቨስትመንት ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለማነቃቃት በሚል ዓላማ 1ኛው የስፖርት ኤግዚቢሽን ባዛር ተዘጋጀ፡፡ በጂኤምኤስ ፕሮሞሽንና በፈለቀ ደምሴ የኮምኒኬሽን ስራዎች የተዘጋጀው ኤግዚብሽንና ባዛር ከመጋቢት 5 እስከ 9 በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ይካሄዳል፡፡ በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ለመሳተፍ በፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ምዝገባ እየተከናወነ ሲሆንን ኮሚሽኑን ጨምሮ፤ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን፣ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴና፣ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሌሎች ፌደሬሽኖችና የስፖርት ተቋማት በአጋርነት ይሰሩበታል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው አገር አቀፍ የስፖርት ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ የስፖርት ክለቦች ማልያዎቻቸውን እንደሚያስተዋውቁ፣ የተለያዩ ስፖርታዊ ቁሳቁሶችንና ማሊያዎችን ለሽያጭ እንደሚያቀርቡ የየክለቦቻቸውን ታሪካዊ ዳራ በፎቶዎችና በቪዲዮ ምስሎች እንደሚያቀርቡበት ታውቋል፡፡

ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ኢትዮጵያ ቡና፤ ደደቢት እና ንግድ ባንክ በዚሁ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ በግንባር ቀደምነት ለመሳተፍ ከተመዘገቡት መካከል ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል የስፖርት እቃ አምራች፣ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅቶች በኤግዚብሽኑና ባዛር ላይ እንደሚሳተፉ ሲታወቅ ምርትና አገልግሎታቸውን የማስተዋወቅና የመሸጥ እድል እንደሚያገኙበት ይጠበቃል፡፡ ከስፖርቱ ጋር በተያያዘ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ መሳተፋቸው በገራ ለመስራት ያሉ ጥረቶችን እንደሚያበረታታ ተገልጿል፡፡

ዋንጫ ከገፅ 24 የዞረ

ታሪኳ 1 ጊዜ ሻምፒዮን(1992)፤ ሁለት ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ(2006, 2012)፤ 4 ጊዜ ሶስተኛ ደረጃ (1965, 1968, 1986, 1994) እንዲሁም 2 ጊዜ አራተኛ ደረጃ (1970, 2008)ነበራት፡፡ በምንግዜም የአፍሪካ ዋንጫ የውጤት ደረጃ አምስተኛ ናት፡፡

### ያያ ቱሬ ከአገሩ ጋር ትልቅ ዋንጫ ይፈልጋል

የኮትዲቯር አምበል ያያ ቱሬ በ10 ዓመቱ ታኬታ ተሰጥቶት በአቢጃን ጎዳናዎች ስሙ የገነነ ታዳጊ ተጨዋች ነበር፡፡ ታላቅ ወንድሙን ኮሎ ቱሬን በመከተል በአዜክ ሚሞሳ አካዳሚ ሰለጠነና አውሮፓ ገባ፡፡ በግሪክ፤ በስፔንና በእንግሊዝ ክለቦች በመጫወት የየአገራቱ ሊጎች ሻምፒዮን ሆኗል፡፡ በተለይ በስፔኑ ክለብ ባርሴሎና 5 ትልልቅ ዋንጫዎችን በአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ፤ በዓለም ክለቦች ዋንጫ፤ በኮፓ ዴላ ሬይ እና በሌሎች ውድድሮች ወስዷል፡፡ በእንግሊዙ ክለብ ማንችስተር ሲቲ የፕሪሚዬር ሊግ ዋንጫ ብቻ ሳይሆን የኤፍኤ ካፕ ዋንጫን አግኝቷል፡፡ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮከብ ተጨዋች ሆኖ ለአራተኛ ጊዜ በመመረጥ ባለክብረወሰን ነው፡፡ ዘንድሮ በአፍሪካ ዋንጫ የተሳተፈው ለ5ኛ ጊዜ ሲሆን በ3 ዓለም ዋንጫዎችም ወርቃማ ትውልድ ከሚባለው የኮትዲቯር ቡድን ጋር በመካፈል የረባ ውጤት አላስመዘገበም፡፡

### አሳሞሃ ጂያን የጋናን የ33 ዓመታት የዋንጫ ረሃብ መታደግ ይፈልጋል


የጋናው አምበል አሳሞሃ ጂያን ደቡብ አፍሪካ ባዘጋጀችው 19ኛው የዓለም ዋንጫ አፍሪካዊ ቡድን ለመጀመርያ ጊዜ ግማሽ ፍፃሜ የሚገባበትን እድል ኢሊጎሬ በመሳቱ ያበላሸ እና በዚያ ታሪክ ዝነኛ የሆነ አጥቂ ነው፡፡ በዓለም ዋንጫ የተሳትፎ ታሪኩ አምስት ጎሎች በማግባት የአፍሪካ ኮከብ ግብ አግቢ የሆነው ጂያን 4ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ መሳተፉ ነው፡፡ የጋና ብሄራዊ ቡድን ከአፍሪካ ዋንጫ ለ33 ዓመታት የራቀበትን ሁኔታ መቀየር ይፈልጋል፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት የነበረበትን የእንግሊዝ ክለብ ሰንደርላንድ በመልቀቅ ለዩናይትድ አረብ ኢምሬትሱ ክለብ አል አሊን አወዛጋቢ ዝውውር ፈፅሞ እየተጫወተ ይገኛል፡፡

### ፈረንሳዊ ሄርቬ ሬናርድ ከእስራኤላዊ አቭራም ግራንት

ለ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ለፍፃሜ የደረሱት ሁለቱ አሰልጣኞች ሄርቬ ሬናርድና አቭራም ግራንት ከአፍሪካ ውጭ የመጡ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ 46 ዓመታቸው የሆኑት ፈረንሳዊው ሄርቬ ሬናርድ በኮትዲቯር ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝነት ለመስራት የሁለት ዓመት ኮንትራት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በ2012 እኤአ ላይ የዛምቢያን ብሄራዊ ቡድን ለሻምፒዮናነት ያበቁበት ታሪክ ትልቁ ስኬታቸው ነው፡፡ ከ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታ በፊት ሬናርድ ስለኮትዲቯር ቡድን ተጠይቀው ለያያ ቱሬ ያላቸውን አድናቆት ከገለፁ በኋላ ‹‹በምሰሶዎቹ ግንባታ ላይ ያለ ብሄራዊ ቡድን ነው፡፡ ወደ አቢጃን ዋንጫውን ይዘን ለመመለስ ተስፋ አድርገናል፡፡›› ብለዋል፡፡



ሄርቬ ሬናርድ



አቭራም ግራንት

አቭራም ግራንት 60 ዓመታቸውን ሊደፍኑ ሲሆን በጋና ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝነት የሁለት ዓመት ውል አላቸው፡፡ የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የፖላንድ ዜግነት ያላቸው አቭራም ግራንት ጋና በአገር ደረጃ ለማሰልጠን ሃላፊነት ያገኙበት የመጀመርያው ብሄራዊ ቡድናቸው ነው፡፡ ከዚሁ ሃላፊነት በፊት በአውሮፓ እግር ኳስ ያካበቱት ልምድ አለ፡፡ በእንግሊዙ ክለብ ቼልሲ በዳይሬክተርነት ተቀጥረው ከዚያም በአሰልጣኝነት ሰርተዋል፡፡

በ2008 እኤአ በማንችስተር ዩናይትድ የተነጠቁት የአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ የማይረሳ ታሪካቸው ነው፡፡ ከቼልሲ በኋላ የፖርትስማውዝ፤ የዌስትሃምና የፓርቴዝያን ቤልግሬድ አሰልጣኝ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በገና ብሄራዊ ቡድን ዙርያ አቭራም ግራንት አስተያየት ተጠይቀው ‹‹በየጨዋታው ከፍተኛ መሻሻል አሳይተናል፡፡ ጋናውያን ከፈቀዱ ዋንጫውን ባሸንፍም ባላሸንፍም በሃላፊነት ብቆይ ደስ ይለኛል፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ከተሳተፉት 16 ቡድኖች ሶስቱ ብቻ በአፍሪካውያን አሰልጣኝ የተመሩ መሆናቸው የአህጉሪቱ እግር ኳስ አንድ ተዳካሚ ሁኔታን የሚያመለክት ሆኗል፡፡ አንዳንድ ዘገባዎች ይህ የአፍሪካውያን አሰልጣኞች ዝቅተኛ ተሳትፎ ከ1996 እኤአ በኋላ የወረደ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ከ3ቱ የአፍሪካ አሰልጣኞች እስከ ግማሽ ፍፃሜ በመድረስ ከፍተኛውን ውጤት ያስመዘገቡት የዲሪ ኮንጎው ፍሎረን አቤንጊ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ሁለት አፍሪካዊ አሰልጣኞች በምድብ ማጣርያ ከእነ ብሄራዊ ቡድናቸው የተሰናበቱት የደቡብ አፍሪካው ኤፍሪዬም ሼክስ ማሻባ ከደቡብ አፍሪካ እና ሆን ጃንዛ ከዛምቢያ ናቸው፡፡ በ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ከተሳተፉ 16 ብሄራዊ ቡድኖች አራት ፈረንሳዊ አሰልጣኞች መወከላቸው ከፍተኛው ነው፡፡ የአልጄርያው ክርስትያን ጉርኩፍ፤ የኮትዲቯሩ ሄርቬ ሬናርድ፤ የኮንጎው ክላውድ ዲለሮይና የሴኔጋሉ ኤቴን ግሬሲ ናቸው፡፡ ሁለት ፖርቱጋላዊያን ጆርጌ ኮስታ በጋቦንና ራውል አኑዋስ በኬፕ ቬርዴ ሁለት ቤልጅማውያን ፖል ፑት በቡርኪናፋሶና ጆርጅ ዚኮንስ በቱኒዚያ የሰሩ አሰልጣኞች ናቸው፡፡ ካሜሮን በጀርመናዊው ቮልከር ፊንኬ፤ ጋና በእስራኤላዊው አቭራም ግራንት፤ ኢኳቶርያል ጊኒ በአርጀንቲናዊው ኤስቴበን ቤከር እንዲሁም ማሊ በፖላንዳዊው ሄነሪክ ካስፐርዣክ አሰልጣኝነት የአፍሪካ ዋንጫውን ተሳትፈዋል፡፡

ባለፉት 29 የአፍሪካ ዋንጫዎች አሸናፊ አሰልጣኞች 18 ከአፍሪካ ውጭ ካሉ አገራት የተገኙ ሲሆን ሻምፒዮን መሆን የቻሉት 11 አፍሪካውያን አሰልጣኞች ናቸው፡፡ ከውጭ አገር አሰልጣኞቹ 5 ፈረንሳውያን፤ 4 ዩጎስላቪያውያን፤ እንዲሁም አራት ሃንጋራዊያን ሲሆኑ 6 ሻምፒዮንአሰልጣኞች ከብራዚል፤ ከቼክ፤ ከሆላንድ ከሮማንያ፤ከጀርመንና ከዌልስ ከእያንዳንዳቸው የተገኙ ናቸው፡፡ ከነገው የ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታ በኋላ ሻምፒዮን ለመሆን የተሳካላቸው የውጭ አገር አሰልጣኞች ብዛት 19 ይደርሳል፡፡

### ቦነስና ሽልማት

በ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የኢኳቶርያል ጊኒ ተጨዋቾች በተከፈላቸው የውጤት ቦነስ የሚስተካከላቸው አልነበረም፡፡ ሩብ ፍፃሜ በመድረሳቸው ለእያንዳንዳቸው 30 ሺ ዶላር ነበር የተከፈላቸው፡፡

ጋናን አሸንፈው ለፍፃሜ ቢደርሱ 50 ሺ ዋንጫውን ከወሰዱ ደግሞ እስከ 150ሺ ዶላር ቦነስ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶ ነበር፡፡ በዓለም ዋንጫ እና በአፍሪካ ዋንጫ በየጊዜው በቦነስ ክፍያ የሚጨቃጨቁት የጋና ብሄራዊ ቡድን ጥቋቁር ክዋክብቶች በአንድ ጨዋታ በአማካይ 5ሺ ዶላር የውጤት ቦነስ እንዲታሰብላቸው ተደራድረዋል፡፡ ዋንጫውን ካሸነፉ ለእያንዳንዳቸው 60ሺህ ዶላር እንደሚከፍል ፌደሬሽኑ ቃል ገብቷል፡፡

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ለአፍሪካ ዋንጫው በድምሩ 10 ሚሊዮን ዶላር ለሽልማት አቅርቧል፡፡ ሻምፒዮኑ 1.5 ሚሊዮን ዶላር ሲሸለም፤ ሁለተኛ ደረጃ የሚያገኘው 1 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ለደረጃ የሚጫወቱት ሁለት ቡድኖች እያንዳንዳቸው 750ሺ ዶላር ይበረከትላቸዋል፡፡ በሩብ ፍፃሜ የቀሩት አራት ቡድኖች እያንዳንዳቸው 600ሺ ዶላር በነፍስ ወከፍ ሲያገኙ፤ በምድብ ማጣርያ ሶስተኛ ደረጃ የሚያገኙት አራት ቡድኖች እያንዳንዳቸው 500ሺ ዶላር እንዲሁም በየምድባቸው የመጨረሻ ደረጃ የሚያገኙት እያንዳንዳቸው 400ሺ ዶላር ይታሰብላቸዋል፡፡

ሽለቆ ከገፅ 22 የዞረ

፡ ይህም ሱዳንና ግብፅን በሀገሬ ወጭና ጉልበት ከጐርፍ የመታደግ ቋሚ ተግባር ሆነ ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መቼም መቼም ክፉን ያርቅ እንጂ በሁለቱም ወይም በአንዱ ሀገር እንደ ዳግማዊ አፄ ዳዊት ዘመን ያለ ድርቅ ለተከታታይ ዓመታት ቢከሰትባቸውና ቢጠቁ ከተጠራቀመው ሐይቃችን ውሃቸው ሳይጓደል እንደነበር ይፈስላቸዋል፡፡ ይኸኛው ደግሞ ምናልባትም የላቀ የሚባል መታደግ ነው፡፡ በሐይቃችን እየቀነሰ የመሄድ ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን የእኛን ጥቅም ለሁለቱ አገሮች ወንድሞቻችን መልካም ኑሮ ልንሰዋ ዝግጁ እንደሆንን ዛሬ አሸጋግሮ በማየት ወሰን የሌለው ድጋፋቸውን ማድረግ ይጠቅማል፡፡ “የዓባይ ስጦታነትም መገለጫው ይኸው ነው፡፡”በአጠቃላይ ዛሬም ሆነ ነገ የዓባይ ታላቁ ሕዳሴ ግድብ ለእኛም ሆነ ለጐረቤቶቻችን የማይነጥፍ እንቋችን መሆኑን በጥልቀት ተገንዝቤአለሁ፡፡ በዚህ ታላቅ ጉዞና ጉብኝት የቤንሻንጉል ክልላዊ መንግሥት፣ እንዲሁም የማንኩሻ ከተማ አስተዳደር ተጉዘን በማስተናገድ የማይረሳ ትብብር አድርገዋል። በተለይም የማንኩሻ ከተማ አስተዳደር እራት በመጋበዝ መቀበላቸው የላቀ ፍቅራቸውን ያላበሰ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ፡፡ በጉዞው የተከታቱት የኪነጥበቡ ሰዎችና ጉዞውን ያቀናጁት የአዲስ አበባ የሕዳሴው ግድብ አስተባባሪ ም/ቤት ሠራተኞች በሚያስደንቅ ሥነ ምግባር የተመሩና ጉብኝታቸውንም በስኬት ያጠናቀቁ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላም መንፈሳቸው በመራቸውና በጫረባቸው አቅጣጫ ሁሉ ለግድቡ ሥራና መጠናቀቅ የሕዝብ የሞቀ ወይም የጋለ ስሜት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይናገራሉ፡፡ ያውጃሉ፡፡ ይደመጣሉና ውጤቱ እንደሚያምር አይጠረጠርም፡፡ እየገነባነው ያለው የኤሌክትሪክ ማመንጫ ኃያል ግድብ የጥንት ማንነታችን በምናፈላልግበት የዓባይ አንዱና የሥልጣኔ ኃያልነታችን በዓለም ላይ የበላይ ሆኖ በከሰመበት ሸለቆ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ወደፊት ደግሞ በዱባ ዙሪያ ያለው ጓዳና ጐድጓዳ በቅሪተ አካል ተመራማሪ ኢትዮጵየውያን ይወረራል፡፡ ገናናው የካምና የኩሽ ሥልጣኔ ታሪካዊ ቅሪቶች ይገኙና ከሃያሉ የአክሱማይት ሥልጣኔአችን ጥንታዊ ታሪክ ጋር ተመጋቢ የሚገባንን ቦታና ደረጃ መያዛችን አይቀሬ ነው፡፡ ዛሬ ለምንገነባው የማንነታችን ፋር ቀዳጅ ግድብ የቻልነውን ሁሉ ማድረግ የዚያ የጥንቱና የአሁኑ ጀግኖች ልጆች ሆኖ መገኘትን ያህል ትልቅ ክብር ያጐናጽፋል፡፡

ማመቅመቅ ወይም ማፈግፈግ እራስን ለውርደት ማቅ መሸፈን ይመስለኛል፡፡ የዚህ ግንባታ ታሪካዊ ባለአሻራነት መሆንም ለዝንተ ዓለም ታላቅ ሐውልት ማቆም ነው! የቡድኑ አውቶቡስ ሾፌርና ረዳቶቻቸው እንዲሁም የታላቁ ሕዳሴ ግድብ መላው ሠራተኞችን ማመስገን ይገባኛል፡፡ የአዲስ አበባ የሕዳሴ ግድብ አስተባባሪ ም/ቤት መላው ሠራተኞችና አብረውን የተጋዙት በተለይ፣ ደህንነታችንን የተንከባከቡት ሁለት የፖሊስ አባላትና አንዱ የጤና ባለሙያም ከልብ ይመሰገናሉ፡፡ በየሥራ ዘርፋችን ለሊቱ ቀን፣ ቀኑም ቀን ይሁንልን፡፡

ግሩም ሠይፉ

# 30ኛዋ የአፍሪካ ዋንጫ ዝሆኖቹን ከጥቋቁር ክዋክብት ታፋጥጣለች


30ኛው አፍሪካ ዋንጫ ዛሬና ነገ ለደረጃ እና ለዋንጫ በሚደረጉ ጨዋታዎች ይፈፀማል፡፡ ዛሬ በደረጃ ጨዋታ አዘጋጇ አገር ኢኳቶርያል ጊኒ ከዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ሲጫወቱ ነገ ደግሞ ኮትዲቯርና ጋና በዋንጫ ፍልሚያ ይፋጠጣሉ፡፡ የምእራብ አፍሪካ ጎረቤታሞች የሆኑት ኮትዲቯርና ጋና በአፍሪካ ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታ ሲገናኙ ሁለተኛቸው ሲሆን በሁሉም ውድድሮች ደግሞ ለ40ኛ ጊዜ መጋጠማቸው ነው፡፡ ሁለቱ የምእራብ አፍሪካ ብሄራዊ ቡድኖች በፕሮፌሽናል ተጨዋቾች ሙሉ በሙሉ መገንባታቸው፤ በአፍሪካ ዋንጫ እና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ባላቸው ከፈትኛ ልምድ እና የውጤት ታሪክ ተመጣጣኝ በሚባል አቋም ላይ ናቸው፡፡ ኮትዲቯርና ጋና በሁሉም ዓለም አቀፍ ውድድሮች 39 ጊዜ ተገናኝተው፤ 14 እኩል ሲሸናነፉ በ11 አቻ ተለያይተዋል፡፡


በ1992 እኤአ ኮትዲቯር እና ጋና በአፍሪካ ዋንጫ ለፍፃሜ በተገናኙበት ወቅት አሸናፊው የተለየው በመለያ ምቶች ነበረ፡፡ ኮትዲቯር ብቸኛውን የአፍሪካ ሻምፒዮናነት ክብር ተቀዳጅታበታለች፡፡ በነገራችን ላይ ኮትዲቯር በአፍሪካ ሁለት ሌሎች የዋንጫ ጨዋታዎች አሳዛኝ ተሸናፊ ነበረች፡፡ በ2002 እኤአ በግብፅ እንዲሁም በ2006 እኤአ በዛምቢያ በመለያ ምቶች ተሸንፋ ሁለት ዋንጫዎችን ተነጥቃለች፡፡ በአፍሪካ ዋንጫ የ56 ዓመታት ታሪክ በተካሄዱት 29 የፍፃሜ ጨዋታዎች አራቱ አሸናፊዎች በተጨማሪ ሰዓት ሲታወቁ፤ 7 የዋንጫ ፍልሚያዎች ደግሞ በመለያ ምቶች ሻምፒዮኖቹ ተለይተዋል፡፡

ከዛሬው የደረጃ እና ከነገው የዋንጫ ጨዋታዎች በፊት በ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ እስከ ግማሽ ፍፃሜ 30 ግጥሚያዎች ተካሂደው 72 ጎሎች ከመረብ ተዋህደዋል፡፡ እስከ ሩብ ፍፃሜ በመጓዝ ባስመዘገቡት ውጤት ደግሞ ከ5 እስከ 16ኛ ያለውን ደረጃ ኮንጎ ፤አልጄርያ፤ ቱኒዚያ፤ ጊኒ ፤ሴኔጋል ፤ማሊ ፤ኬፕቨርዴ ጋቦን ፤ካሜሮን ፤ዛምቢያ ፤ደቡብ አፍሪካና ቡርኪናፋሶ ያገኛሉ፡፡

በ30 የአፍሪካ ዋንጫዎች ሻምፒዮንነት በ5 ዞኖች ሲከፋፈል ሰሜን አፍሪካ በ10 ዋንጫዎች (7 የግብፅ እንዲሁም እያንዳንዳቸው አንድ ቱኒዚያ፤ አልጄርያ እና ሞሮኮ ) በማግኘት ይመራል፡፡ የምእራብ አፍሪካ ዞን ከ30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ጋር በ9 ዋንጫዎች (የጋና 4 ወይም 5 ፤ የናይጄርያ 3 እንዲሁም የኮትዲቯር 1 ወይም 2) ፤ መካከለኛው አፍሪካ በ7 ዋንጫዎች (4 የካሜሮን፤ 2 የዲ ሪ ኮንጎ 1 የኮንጎ ኪንሻሳ)፤ ምስራቅ አፍሪካ በ2 ዋንጫዎች (የኢትዮጵያ እና የሱዳን) እና ደቡብ አፍሪካ በ2 ዋንጫዎች (የደቡብ አፍሪካ እና የዛምቢያ) ተከታታይ ደረጃ ያገኛሉ፡፡




ያያ ቱሬ


አሳሞሃ ጂያን

## የኢኳቶርያል ጊኒ ብሄራዊ መብረቅ

ብሄራዊ መብረቅ በሚል ቅፅል ስም የምትጠራው ኢኳቶርያል ጊኒ 2ኛዋን የአፍሪካ ዋንጫን መሳተፏ ነበር፡፡ ሁለቱንም ደግሞ በአዘጋጅነት ነው፡፡ በ2012 እኤአ 28ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ከጋቦን ጋር በጣምራ አዘጋጅነት ለመጀመርያ ጊዜ በመካፈል ሩብ ፍፃሜ ደረሰች፡፡ 30ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ ደግሞ በምትክ አዘጋጅነት ተረክባ በ64 ቀናት በማዘጋጀት በታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ ግማሽ ፍፃሜ ደርሳለች፡፡

## የጋና ጥቋቁር ከዋክብት

- አማካይ እድሜ 24.9 ዓመት
- የአንድ ተጨዋች አማካይ ዋጋ እስከ 4 ሚሊዮን ዶላር
- የእግር ኳስ ደረጃ በዓለም 37 በአፍሪካ 4
- የቡድን ዋጋ ግምት $150,743,365

ጋና በ19 የአፍሪካ ዋንጫዎች ስትሳተፍ 4 ጊዜ ሻምፒዮን (1963, 1965, 1978, 1982)፤ 4 ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ(1968, 1970, 1992, 2010)፤ 1 ጊዜ ሶስተኛ ደረጃን (2008) እንዲሁም ለሶስት ጊዜያት በአራተኛ ደረጃ (1996, 2012, 2013) ጨርሳለች፡፡ በእነዚህ አፍሪካ ዋንጫዎች ባስመዘገበችው 154 ነጥብ በምንግዜም የውጤት ደረጃ ሶስትኛ ናት፡፡

## የኮትዲቯር ዝሆኖቹ

- አማካይ እድሜ 26.4 ዓመት
- የአንድ ተጨዋች አማካይ ዋጋ እስከ 8 ሚሊዮን ዶላር
- የእግር ኳስ ደረጃ በዓለም 28 በአፍሪካ 3
- አጠቃላይ የቡድን ዋጋ ግምት $207,628,902

ኮትዲቯር በ20 የአፍሪካ ዋንጫዎች የተሳትፎ

ዋንጫ ወደ ገፅ 23 ዞሯል

